# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

## የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ

(በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ)


አሳታሚ
በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
የሕዝብ ግንኙነትና የልማታዊ ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት



የመጀመሪያ እትም
ሚያዚያ 2007
አዲስ አበባ

መግቢያ......1
ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ......4
1. የምግብ ዋስትና ምንነት፣ የተጋላጭነት መንስኤዎች እና ተጋላጮች......4
1.1 የምግብ ዋስትና ምንነት......4
1.2 የምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጭነት መንስኤዎች......5
1.2.1 በስራ ላይ ያለው የታታሪነት መጓደል......5
1.2.2 የልማታዊ መልካም አስተዳደር ጉድለት......7
1.2.3 የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት ያለመጠናከር......9
1.2.4 ከገቢ ጋር ያልተጣጣመ የቤተሰብ ምጣኔ እና የቤተሰብ መላላት......10
1.2.5 ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው የህዝብ ፍልሰት......10
1.2.6 የአመጋገብ ባህላችን ያስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ......11
1.2.7 ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ ያለመጠናከሩ......11
1.2.8 የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ያለመጠናከርና የከተማ ግብርና ለምርት አቅርቦት እያበረከተ ያለው አዎንታዊ አስተዋፅኦ የተጠናከረ ያለመሆኑ......12
1.2.9 የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተጋላጭነት......13
1.3 በከተሞች የምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጮች......14
1.3.1 አነስተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች......15
1.3.2 ጎዳና ተዳዳሪዎችና ለምኖ አዳሪዎች......16
1.3.3. ሴተኛ አዳሪዎች......16
1.3.4 ሥራ ፈት ዜጎች......17
1.3.5 ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች......18
1.3.6. የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎችና ወጣት ጥፋተኞች......18
2. የስትራቴጂው መነሻ ሁኔታዎችና አስፈላጊነት......19
2.1 የሃገር ውስጥና የውጭ ሀገር የሁኔታዎች ትንተና እና ምርጥ ተሞክሮዎች......19
2.1.1 ከከተሞች ምግብ ዋስትና ጋር በቀጥታ የተያያዙ የመነሻ ሁኔታዎች ትንተና......19
2.1.2. የምርጥ ተሞክሮ ትንተና......24
2.2 የስትራቴጂው መነሻ ሁኔታዎች......31
2.2.1. ፈጣን ልማታችንና የህዝብ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ተልዕኮ......31
2.2.2. ፈጣን ልማትና የከተሞች ሚና......32
2.2.3 የኢንዱስትሪ ልማትና የህዝብ ተጠቃሚነት......33
2.2.4 የምግብ ዋስትናና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዶቻችን ተያያዥነት......34
2.3 የስትራቴጂው አስፈላጊነት......35

ክፍል ሁለት፡- ከተሞች ምግብ ዋስትና ዓላማና ስትራቴጂዎች........................................................36
3 ጥቅል ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች........................................................36
3.1 ጥቅል ዓላማ........................................................36
3.2 ዝርዝር ዓላማዎች........................................................37
4 የስትራቴጂው ግቦች........................................................37
4.1 ጥቅል ግብ........................................................37
4.2 ዋና ዋና ግቦች........................................................38
5. የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች........................................................38
5.1 በከተሞች ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር ፍትሃዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ........38
5.2 ከተሞች ከገጠሮች እንዲሁም ከተሞች ከከተሞች ጠንካራ ልማታዊ ትስስር መፍጠር.............41
5.3 የአመጋገብ ባህላችን የሚቀየርበትን ስትራቴጂ ቀይሶ መተግበር........................................41
5.4 ዘመናዊ የምግብ የአቅርቦትና የግብይት ስርዓት በአስተማማኝ ሁኔታ መፍጠር......................41
5.5 የአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ........................................................42
5.6 ግልፅነት፣ ተጠያቂነት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በመተግበር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ........................................................43
5.7 ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር ተልዕኮውን በቅንጅት ማስፈጸም........................................44
5.8. የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ..............................45
5.9 የማስፈጸም አቅም መገንባት........................................................47
5.10 የሀብት ምንጭና አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት........................................................47
5.11. ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ማስፋፋት........................................................48
5.12 የአህዘቦትና የተግባቦት ዝርዝር እቅድ አዘጋጅቶ የማስፈጸም አቅጣጫ መከተል....................50
ክፍል ሶስት፡- የባለድርሻ አካላት ሚናና የአፈጻጸም ስልቶች........................................................51
6. የአስፈጻሚዎች የተዋረድ ተልዕኮ........................................................51
6.1 ተጠቃሚዎች........................................................51
6.2. ህብረተሰቡ........................................................51
6.3 የመንግስት ሚና........................................................52
6.4 የልማት አጋሮች........................................................53
6.5 የግሉ ዘርፍ ሚና........................................................54
6.6 የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች........................................................54
7. የአፈጻጸም አቅጣጫዎች........................................................55
7.1 የከተማ ምግብ ዋስትና ለማስፈጸም የልማት ሰራዊት ግንባታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት አቅጣጫ መከተል........................................................55

7.2 የሚመለከታቸው ባለ ሚናዎች በተሟላ አኳኃን የማሳተፍ አቅጣጫ መከተል ........................ 56
7.3 የሥራ ውጤትን የሁሉም ነገር ማጠንጠኛ የማድረግ አቅጣጫ መከተል ................................ 57
7.4 በግልጽ ቅደም ተከተል የመምራት አቅጣጫ መከተል ............................................................ 58
7.5 የእርስ በእርስ የመማማር ሥርዓት የመዘርጋትና የመተግባር አቅጣጫ መከተል .................... 59
8. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ........................................................................................ 60
8.1 የገጠር ምግብ ዋስትና ተሞክሯችን ወደ ከተማ ማስፋፋት ..................................................... 60
8.2 ለክትትልና ግምገማው ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን መጠቀም .................................................... 60
8.3 የተጠናከረ የፋይናንስ ሥርዓት ከጅምሩ መገንባት ................................................................ 60
9. ማጠቃለያ ..................................................................................................................... 61
አባሪዎች፡- የሴክተር መ/ቤቶች የተግባርና ሃላፊነት መግለጫ ..................................................... 63

# መግቢያ

ሀገራችን ዋና ጠላታችን የሆነውን ድህነት ለማስወገድ የህዳሴ ጉዞ ቀይሳ መሰረታዊ ለውጥ በሚያመጣ አኳኋን እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች። ይህንንም እውን ለማድረግ ሁሉም የሃገሪቱ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች በሃገር አቀፍ ደረጃ የወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማስፈጸም ድህነትን ማስወገድ እንደ ዋና አጀንዳቸው አድርገው በመረባረባቸው ተጨባጭ ለውጦች እየተመዘገቡ ይገኛሉ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከምግብ ጥገኝነት ለመላቀቅና በሚቀጥሉት ሁለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን መርሃ-ግብሮች ሃገራችንን የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገሮች ተርታ ለማሰለፍ የሚያስችል የመጀመሪያ ምዕራፍ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን ላለፉት ተከታታይ አሥራ ሁለት ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል፡፡

የሃገራችን ኢኮኖሚ ፖሊሲ የገጠርና የከተማ ልማት አቀናጅቶና አስተሳስሮ ሁሉን አቀፍ ልማት ማፋጠን እና ለህዝቡ ተደራሽ መሆን እንዲያስችል ተደርጎ የተቀረጸ ነው፡፡ በመሆኑም በገጠር የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ በገበያ የሚመራ ክፍለ-ኢኮኖሚ በመፍጠር ላይ ያተኮረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በከተሞች ደግሞ ሰፊ መሰረት ያለው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂን ማሳካት ቁልፍ አጀንዳ ተደርጎ በመወሰዱ፣ የቤቶች ልማት ኘሮግራም ቀርጾ በመተግበር፣ የከተሞች የአካባቢ ልማት ኘሮግራም ቀርጾ በመተግበር …ወዘተ ከተሞች የአንዱስትሪና የአገልግሎት ማዕከላት በማድረግ ላይ ውጤት ማስመዝገብ ጀምሯል፡፡ እነዚህ ስራዎች በመከናወናቸው ተጨባጭ ውጤቶች እየተገኙ ነው፡፡ በአንዳንድ ዜጎቻችን ላይ ባለው በስራ ላይ የተዛባ አመለካከት ምክንያት እየተፈጠረ ያለውን የስራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ በተደረገው ከፍተኛ ጥረት ጉልህ መሻሻል ቢኖርም በቀጣይነት ትኩረት ሰጥቶ የሥራ ባህላችን በማሻሻል ዜጎች የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥና ድህነትን በዘላቂነት ከማስወገድ አኳያ ገና ብዙ መስራት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡

በገጠር አካባቢዎች በተደጋጋሚ የሚከሰተውን የምግብ ዋስትና ችግር ለመቅረፍና የችግሩ ተጠቂ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል በዘላቂነት የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ እንዲችል የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ በመደረጉ በአጠቃላይ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ስኬት ላይ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ይህ ውጤት የተገኘው በገጠሩ ማህበረሰብ ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በመሰራታቸውና አርሶ አደሩ የልማት ሰራዊት በመሆን ለተጋረጡ ችግሮች የመፍትሄ አካል ሆኖ በባለቤትነት በመሳተፉ ነው፡፡ በተፈጠረው የልማት ሰራዊት ከፍተኛ የአካባቢ

ጥበቃ ስራዎች በመከናወናቸው የአካባቢው ስነ-ምህዳር እንዲስተካከል በማስቻሉና ለአዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ተጨባጭ ለውጦች እየተመዘገቡ ይገኛሉ።

ይሁን እንጂ የዚህ የሀገራዊ ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ትኩረቱ ገጠር ላይ በመሆኑ በከተሞች ያለውን የምግብ ዋስትና ችግር በተዘዋዋሪ መንገድ ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ ማቃለል አልቻለም። በአንጻሩ ከተሞች ያላቸውንም ዕምቅ ሀብት ባለመጠቀማቸውና በአብዛኛው ሊባል በሚችል ደረጃ ከገጠር በሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ላይ ጥገኛ በመሆናቸው የምግብ ዋስትና ችግሮችን በመሠረታዊነት ማቃለል አልቻሉም። በከተሞች በተለያዩ አካላት እየተካሄዱ ያሉ በመንግስት የሚቀርቡ መሠረታዊ ሸቀጦችና ሌሎች የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ስራዎችም ለድሃ ተብለው የተቀረፁ ቢሆኑም በአፈፃፀም ረገድ ግን ለታለመለት የማህበራዊ መሰረት የማይደርሱ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ስራዎቹ ያልተቀናጁና ያልተናበቡ በመሆናቸው የሀብት ብክነትና የጥገኝነት ስሜት ከማስፈናቸውም ሌላ ዘላቂ ውጤት ማምጣት ላይ ክፍተት ይስተዋልባቸዋል።

የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ባለመኖሩ ምክንያት የክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደሮች የየራሳቸውን ፕሮግራምና ፕሮጀክት በመቅረፅ በየአካባቢያቸው ያለውን የምግብ ዋስትና ችግር ተገቢው ትኩረት ሰጥተው ለመፍታት ጥረት ሲያደርጉ አይታይም። ስለዚህ የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ በማዘጋጀትና በዚህም መነሻ ፕሮግራምና የተለያዩ ፕሮጀክቶች በመንደፍ የከተሞቻችን አነስተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል በዝርዝር ለይቶ በጊዜ ገደብ የምግብ ዋስትና ችግር መቅረፍ ያስፈልጋል። በመሆኑም በከተሞች ያለውን የምግብ ዋስትና እጦት ለማቃለልና በዘላቂነት ለማስወገድ ይህን የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ስትራቴጂ በከተሞች የተነደፉትን የከተሞችን ዕድገት በማፋጠን የሚስተዋለውን ድህነትና የምግብ ዋስትና ችግሮች ለማቃለል አልመው የተቀረጹ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኘሮግራም፣ የቤቶች ልማት ኘሮግራም፣ የከተሞች የአካባቢ ልማት ኘሮግራም፣.....ወዘተ ጋር ሳይቀላቀል በእነዚህ ኘሮግራሞች ችግራቸው ሊፈታ የማይችል የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ ተጠቃሚ ለማድረግ አልሞ የተዘጋጀ ስትራቴጂ ነው። በመሆኑም የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂውን መሠረት ተደርጎ የሚቀረጸው ኘሮግራም ድሆችን ብቻ በዝርዝር ለይቶ በተለየ አኳኋን ተጠቃሚ የሚያደርግ ኘሮግራም ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ሃገራችን ካጸደቀቻቸው የድህነት ቅነሳና የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች መካከል በ2007 ዓ.ም የጸደቀው የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ አንዱ ነው። ፖሊሲው ከሚያተኩርባቸው ምሰሶዎች መካከል ሰፊ ስራ እድል በመፍጠርና ቀጥታ ድጋፍ በማድረግ

የዜጎችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ዋንኛው በመሆኑ ፖሊሲው የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ መነሻ ሆኗል፡፡

ሰነዱ ሶስት ክፍሎችን እንዲይዝ ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን ክፍል አንድ ጠቅላላ ይዘቶችን ማለትም የምግብ ዋስትና ምንነት፣ የከተማ ምግብ ዋስትና እጦት ተገላጭነት መንስኤዎች፣ ተጋላጮች፣ የስትራቴጂው መነሻ ሁኔታዎች እና አስፈላጊነት የተገለፀበት ነው፡፡ ክፍል ሁለት የከተሞች ምግብ ዋስትና ዓላማ፣ ግብና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች የተተነተነበት ሲሆን ክፍል ሶስት የባለድርሻ አካላት ሚናና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች የቀረበበት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዚያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም ባካሄደው 84ኛ መደበኛ ስብሰባ በከተሞች ምግብ ዋስትና ረቂቅ ስትራቴጂ ላይ በዝርዝር ተወያይቶ አንዳንድ ማሻሻዎችን በማከል ስትራቴጂው የመጨረሻ ቅርጹን ይዞ እንዲታተምና በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

# ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ

## 1. የምግብ ዋስትና ምንነት፣ የተጋላጭነት መንስኤዎች እና ተጋላጮች

### 1.1 የምግብ ዋስትና ምንነት

የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ማለት እያንዳንዱ ዜጋ መጠንና ጥራትን ባማከለ መልኩ በዘላቂነትና ባልተቆራረጠ ሁኔታ ምግብ በማግኘት የነፍስ ወከፍ የዕለት ፍጆታን 2,200 ካሎሪ እንዲደርስ በማድረግ ጤናማና አምራች እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

የምግብ ዋስትና እጦት ስር የሰደደ እና ጊዜያዊ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና እጦት በአብዛኛው በቤተሰብ ደረጃ የጥሪት መመናመንን የሚያመላክት ሲሆን ጊዜያዊ የምግብ ዋሰትና ችግር ደግሞ ድንገተኛ በሆኑ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች የሚከሰት የምግብ አቅርቦት ችግር ነው፡፡

የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ የሰው ልጅ የሚያስፈልጉትን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት የአጭር ጊዜ የምግብ አቅርቦት ችግርን በማቃለል ዜጎችን በቀጣይ ከከፋ ድህነትና ከተመጣጠነ ምግብ ዕጦት ችግር በራሳቸው ጥረት ደረጃ በደረጃ በማላቀቅ ዘላቂነት ባለው መልኩ እንዲቋቋሙና የተሻለ ኑሮን እንዲመሩ የተመቻቸ ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡ ስትራቴጂው ዝቅተኛ የገቢ ምንጭ ያላቸውንና የመስራት አቅም ያላቸው ዜጎች ከህብረተሰቡ ጋር ሆኖ በጥንቃቄ ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር በፀዳ አኳኋን በመለየት ጉልበት፣ ሀብት፣ ክህሎት እና ዕውቀታቸውን አቀናጅተው ኑሯቸውን በዘላቂነት ለመምራት የሚያግዙ እሴትን የሚጨምሩ የአካባቢ ልማት ስራዎችን በስፋት በመስራት በተያያዥነትም ቀጣዩን ኑሯቸውን ሊመሩበት የሚያስችላቸውን ጥሪት በማፍራት መቆጠብ የሚያስችል እና በተደራራቢ የአካል ጉዳት፣ በዕድሜ በጤና ወዘተ ምክንያት በስራ ላይ መሰማራት ለማይችሉ ዜጎች የቀጥታ ድጋፍ የሚሰጥበት ሲሆን ይህም በመንግስት፣ በልማት አጋሮችና በህብረተሰቡ ጥምር ተሳትፎ የሚተገበር ነው፡፡

በከተማ ልማት የተለያዩ ኘሮግራሞች ተሳትፈው ከችግሮቻቸው ለመውጣት የሚቸገሩ የድሃ ድሃ የሚባሉ ዜጎች በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ለምሳሌ በከተማ ግብርና፣ በአረንጓዴ ልማት፣ በከተማ ዕዳትና ውበት፣ በውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ በወንዝ ዳርቻ ልማት፣ በጎርፍ መከላከያ ልማት፣ በተቀናጀ ተፋሰስ ልማት፣ በማህበራዊና የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ስራዎች ላይ

ተሰማርተው በሚከፈላቸው ክፍያ ከመደበኛው የተሻለ የዕለት ገቢ በማግኘት ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉና ጥሪት እንዲያፈሩ ያስችላቸዋል፡፡ ይህ ፕሮግራም ከሌሎች ፕሮግራሞች ጋር እንዳይጣረስ የአፈፃፀም ስትራቴጂ ይዘጋጅለታል፡፡ በዚም ረገድ ከድህነት ወለል በታች ያሉ የከተማ ነዋሪዎች የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ከማስቻል ባሻገር በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ላይ ተደማሪ ውጤት እንዲመዘገብ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ በቀጣይነት እንዲያበረክቱ ይረዳል፡፡ በመሆኑም የልማታዊ ሴፍቲኔት ስራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል በከተሞች እየታየ ያለውን የምግብ ዋስትና እጦት ለማቃለል ብሎም ለማስወገድ ሁሉንም ባለድርሻና ተባባሪ አካላት አቀናጅቶ መምራት ያስፈልጋል፡፡

ይህንን ስትራቴጂ ተከትሎ በሚዘጋጀው ኘሮግራም መሠረት ተጠቃሚ ዜጎች በየከተሞቹ እየተካሄዱ ባሉ የልማት ኘሮግራሞች ተጠቃሚ ሆነው ከችግራቸው መላቀቅ የማይችሉና በተለያየ ምክንያት ተጠቃሚም ያልሆኑ የድሃ ድሃ የሚባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ በአንጻሩ በከተሞች ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በዚህ ኘሮግራም በትክክል ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ወይም ዜጎች በአግባቡ መለየትና በሚፈለገው አቅጣጫ መሠረት ማስተዳደር አንዱ ፈታኝ ሁኔታ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ ከወዲሁ ሥራው በሠራዊት አግባብ የሚፈጸምበት ጋይድ ላይን አስቀምጦ ለማስፈጸም ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይገባል፡፡ በከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂና ፕሮግራም ተግባራዊ በማድረግ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ከስትራቴጂና ፕሮግራም ዝግጅት ጀምሮ እስከ ትግበራና የአፈጻጸም ግምገማ ድረስ በየደረጃው ካሉ የመንግስት አካላት፣ የልማት አጋሮች፣ የህብረተሰብ አደረጃጀቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር መስተጋብር በመፍጠር ቀጣይነት ያለው የክትትል፣ ድጋፍና ግብረ መልስ ስርዓት መዘርጋት ተገቢ ይሆናል፡፡ አፈጻጸሙን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በተደገፈና እያንዳንዱን ተጠቃሚ በትክክል በስም፣ በቤተሰብ እና በአካባቢ በመለየት ገንዘብ የሚተላለፍበት፣ ሪፖርት በጊዜና በጥራት የሚቀርብበት ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል፡፡

## 1.2 የምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጭነት መንስኤዎች

### 1.2.1 በስራ ላይ ያለው የታታሪነት መጓደል

በከተሞች እየተስፋፋ የመጣውን የስራ አጥነት ችግር ለመፍታት መንግስት በርካታ ፕሮግራሞች ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣው ሥራን የማማረጥ

አመለካከት ምክንያት የሚሰራ ጉልበትና የሚያስብ አእምሮ ይዘው በሌሎች ጥገኝነት የሚኖሩ ስራ ፈቶች መኖር በከተሞች እየተከሰተ ላለው የምግብ ዋስትና ያለመረጋገጥ አንዱ ምክንያት ነው፡፡

በተለያዩ ኋላቀርና በተሣሣቱ ምክንያቶች አምራች ሊሆን የሚችል ኃይል የተገኘውን ማንኛውንም ሥራ ከመስራት ይልቅ ጎዳና ወጥቶ መለመንን አማራጭ አድርጎ የሚያይ ዜጋ ማስቀረት አልተቻለም፡፡ ይህ አዝማሚያ ደግሞ በዚሁ ከቀጠለ ውሎ አድሮ በህብረተሰቡ ሰላማዊ አኗኗር እና የሃገር ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው፡፡

ከመረዳዳት ባህላችን ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ስናይ ህብረተሰቡ አንድም ከሰብአዊነት በሌላ በኩል ደግሞ ከሃይማኖት ጋር በማያያዝ መስራት ለሚችለውም ለማይችለውም ያገኘውን ሲለግስ ይስተዋላል፡፡ በሥራ ታታሪነት የማያምነው ደግሞ ይህን በጎ እሴት በተዛባ አኳኋን ሲጠቀምበት ይስተዋላል፡፡ በዚህም ምክንያት በስራ ላይ ቢሰማራ ለራሱና ለሀገሩ ዕሴት በመፍጠር ለውጥ ሊያመጣ ይችል የነበረ የሰው ሀብት ሲባክን ይታያል፡፡

በሃገራችን ያለው የተቋጥሮ ዝምድና ገደብ የለሽ በመሆኑ ተወላጆች ቢሰሩም ባይሰሩም ዕድሜ ልካቸውን በቤተዘመድ የኑሮ ዋስትና (Family net-work life insurance) እንዲኖሩ የሚፈቅድ መሆኑ ቤተሰብ እና የቤተዘመድም የቤተሰቡ አባላት በተወሰነ የዕድሜ ገደብ ራሳቸውን እንዲችሉ የሚያዘጋጁበት የአኗኗር ሥርዓት ያለመኖሩ አንዳንድ ዜጎች ለሥራ ትኩረት እንዳይሰጡ የበኩሉን አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡

እየታየ ባለው የታታሪነት መጓደል እና በስራ ላይ ካለው የተዛባ አመለካከት ባሻገር  አንዳንድ ዜጎች በማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ተጋላጮችና የጠንቆቹ ሰለባዎች ደግሞ በህብረተሰቡ ላይ ያላቸው አመለካከት በትክክለኛ ዕይታ ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ሁለቱም ወገኖች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በአንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያየ ምክንያት ለማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች የተጋለጡ ዜጎች አመለካከታቸውን ቀይሮ ሰርተው ሊለወጡ የማይችሉ አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያዎች ይስተዋላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የልማታዊ መንግስታችን በነደፈው ፖሊሲ ምክንያት ሰፊ አማራጭ የስራ ዕድል ቢፈጠርላቸውም በዝግጁነት መጓደል ምክንያት ዕድሉን ሳይጠቀሙ የሚቀሩ እንዳሉ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጎዳና ተዳዳሪዎች ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ልምድ እና ከሌሎቹም መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሃገር ውስጥ ባሉ አማራጮች በመጠቀም ራሱን መለወጥ የሚችል አምራቹ ኃይል ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍሎች መሰደድን  አማራጭ አድርገው እንደሚያዩ ይታወቃል፡፡ ይህም በዜጎቻችን ህልውናና በሃገር ገጽታ ላይ የማይሽር ጠባሳ እየጣለ ይገኛል፡፡

ነባራዊ ሁኔታዎችን በዝርዝር ገምግሞ የሥራና የታታሪነትን ባህል በማጎልበት በከተሞች ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መቀየር በየደረጃው ያለው አመራር ኃላፊነት መሆኑን በመረዳት በሚገባው የትኩረት መጠን በአጣዳፊነት መንፈስ ባለመሰራቱ ለችግሩ መባባስ የበኩሉን አስተዋፅዖ እያደረገ መሆኑን የጋራ ግንዛቤ መያዝ ለቀጣይ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

### 1.2.2 የልማታዊ መልካም አስተዳደር ጉድለት

በ1999 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሠረት በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር 11.9 ሚሊዮን (16.1 በመቶ) የደረሰ ሲሆን በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ትንበያ መሰረት በ2007 ዓ.ም ወደ 18.7 ሚሊዮን (20%) ይደርሳል ተብሎ ተገምቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው በከተሞቻችን እየታየ ያለው አጠቃላይ የሕዝብ እድገት ምጣኔ በአማካይ 5.2 በመቶ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ከአጠቃላይ የሃገሪቱ ዓመታዊ የ2.6 በመቶ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ ጋር ሲነጻጸር የከተማው ሕዝብ ቁጥር እድገት በእጥፍ እያደገ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህ ከፍተኛ የከተማ ሕዝብ መጨመር የማሕበራዊ እና ኢኮኖሚዊ አገልግሎቶችን ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅና አገልግሎቶቹ በዚሁ ልክ ካልሆነ የልማታዊ መልካም አስተዳደር ጉድለት መሆናቸው የማይቀር ነው፡፡ አሁንም መሆን ጀምሯል፡፡

የልማታዊ መልካም አስተዳደር ጉድለት ለምግብ ዋስትና ችግር እንደ አንድ መንስኤ ሲነሳ ስራው የከተማ አስተዳደሮችን ባለቤትነትና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡ ከተሞች ካላቸው የአስተዳደር ባህርይና የነዋሪዎቻቸው የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ፍላጎት ልዩነት ምክንያት ችግሮቹ ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ያደርጋቸዋል፡፡ በከተሞች የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ የበላይነት መያዝ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር በተሟላ አኳኋን ከላይ እስከ ታች ድረስ ያለመዘርጋት፣ የሙስናና ብልሹ አሰራር መገለጫዎች መኖር፣ በሚካሄዱ የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች የህዝብ ተሳትፎ ውስንነት፣ እንዲሁም ለስራ አጥ ዜጎች በሚደረግ የብድር አቅርቦት እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚታዩት ክፍተቶች… ወዘተ የከተሞቻችን ዋና ዋና የልማታዊ መልካም አስተዳደር ጉድለቶች ናቸው፡፡

ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በርካታ የስራ ዕድሎች እየተፈጠሩ ቢሆንም በከተሞች ካለው ድህነትና የስራ አጥነት ስፋት አኳያ ሲታይ ገና ብዙ ርቀት መሄድ እንደሚጠይቅ መረዳት ይቻላል፡፡ በአመራሩ በኩል ስትራቴጂውን በቁርጠኝነት ከማስፈጸም ጋር በተያያዘ የጥቃቅንና

አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሀገራችን ለምትከተለው የኢንዱስትሪያሊስቶች መፍለቂያና ለልማታዊ ትራንስፎርሜሽን መሰረት መሆናቸውን በእምነትና በእውቀት ይዞ ከመምራት ይልቅ በተለያዩ አሳማኝ ባልሆኑ ሰበቦች የብድር አገልግሎትን፣ የሼድ ዝግጅትና አቅርቦትን፣ የአቅም ግንባታ ስራዎችንና የአደረጃጀት ስራውን በቅርብ ተከታትሎ ማነቆዎቹን በመፍታት ረገድ መዘግየት ይታያል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተዋናዮቹ በኩል ተደራጅቶ በመስራት ሊገኝ የሚችለውን ለውጥ በአግባቡ ባለመረዳት እና በኢንተርፕራይዞቹ ውስጥ ከግብር ከፋይነት ጋር በተያያዘ ባለው የተዛባ አስተሳሰብ ምክንያት ተደራጅቶ መስራትን ያለመፈለግ አዝማሚያ ይስተዋላል፡፡ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕይዞች በኩል ጥራት ያለውን ምርት አምርቶ በገበያው ላይ ተወዳዳሪ ከመሆን ይልቅ ጥራቱን ያልጠበቀ ምርት ገበያ ላይ አቅርቦ ጥቅም የማግኘት ፍላጎት፣ አቅማቸውን በመገንባት አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን ያለመስራትና የጠባቂነት ስሜት ዝንባሌ ይስተዋልባቸዋል፡፡

በከተሞች ያሉ የስራ አማራጮች በጥናት ላይ በተመሰረተ መረጃ አሟጦ ያለመጠቀም፣ በተወሰኑ የስራ መስኮች ላይ ብቻ በማተኮር የከተማ ግብርና እና ሌሎችንም የስራ መስኮችን በበቂ ሁኔታ ያለመጠቀም፣ በስትራቴጂው ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ራሱን የቻለ ፓኬጅ አዘጋጅቶ ያለመንቀሳቀስ፣ አሁን ያሉትን የግብርና ውጤቶች የአግሮፕሮሰሲንግ ተቋማት በማደራጀትና እሴት በመጨመር ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ዕድገት ዕገዛ ማድረግ ያለመቻሉ…ወዘተ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ውጤት ላለመምጣቱ በአመራሩ በኩል ከሚታዩ ጉድለቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በከተሞች አካባቢ የምግብ ዋስትና ችግር በአብዛኛው የሚታየው ዝቅተኛ የገቢ ምንጭ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ላይ ነው፡፡ ይህ የህብረተሰብ ክፍል በአብዛኛው ጉልበቱን በመተዳደሪያነት የሚጠቀም ሲሆን የስራ ዋስትናው አስተማማኝ ባለመሆኑ እና በየጊዜው በሚከሰተው የዋጋ ግሽበትና መዋዠቅ በቀላሉ ለአደጋ የተጋለጠ ነው፡፡ አማራጭ የገቢ ምንጭ ባለመኖሩ ምክንያት የስራ ዋስትና በሚያጣበት ወቅት ችግሩን ለመቋቋም የአመጋገብ መጠኑን ስለሚቀንስ በዚህም ሳቢያ በቀላሉ ለተለያዩ በሽታዎች በመጋለጥ ለተጨማሪ የህክምና ወጪ ይዳረጋል፡፡

መንግስት በከተሞች የሚታየውን የቤት እጥረት ለመቅረፍ የተለያዩ የቤት ልማት ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ በመንቀሳቀሱ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ያስመዘገበ ቢሆንም አቅርቦቱ ከፍላጎቱ ጋር ገና አልተጣጣመም፡፡ በከተሞች የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል ከሚያገኘዉ ገቢ ውስጥ አብዛኛው ገቢውን ባላገናዘበ መልኩ ለቤት ኪራይ ወጪ የሚያውል በመሆኑ ለምግብ መዋል የሚገባውን የገንዘብ መጠን አነስተኛ ስለሚሆን በከተሞች የሚገኘው በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል የምግብ ዋስትናውን በማረጋገጥ ረገድ ፈተናዎች እያጋጠሙት ነው፡፡

በከተሞች ብዛት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በየጎዳናው በንግድና በማምረት ስራ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ ለመሸጫና ለማምረቻ የሚሆን ቦታ ለማቅረብ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም ፍላጎቱን ሙሉ ለሙሉ ማሟላት ባለመቻሉ በምርታማነታቸው ላይ የበኩሉን አሉታዊ ተፅኖ እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክንያት በቀን ማግኘት የሚገባቸውን ገቢ እንዳያገኙ ስለሚሆንና ከሚያገኙት ገቢ ውስጥ ደግሞ አብዛኛውን የሚያውሉት ምግብ ነክ ላልሆኑ ወጪዎች በመሆኑ ለምግብ ፍጆታ የሚያውሉት ወጪ እንዲቀንስ በማድረግ የምግብ ዋስትናቸው እንዳይረጋገጥ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ዜጎች መሸጫ እና ማምረቻ ቦታ አግኝተው ወደ ህጋዊ የንግድ ስርዓቱ እንዲገቡ ቢደረግ ራሳቸውን ከመጥቀም አልፈው ለከተሞቹ ገቢ በማስገኘት ሊያበረክቱ የሚችሉት አዎንታዊ አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘው ህብረተሰብ በቤተሰብ ምጣኔ በበቂ ሁኔታ ባለመጠቀሙ ምክንያት የቤተሰብ ቁጥር መጨመርና የገቢ ምንጩም በቂ ባለመሆኑ ለተወለዱ ልጆች የትምህርትና የህክምና እንዲሁም የመሰረታዊ ፍላጎቶች ወጪ የመሸፈን በተለይም የሴት ዕማወራዎች አቅም ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ቤተሰብ በአግባቡ ማስተዳደር ስለማይችሉ ቤተሰቡ አባላት ለተለያዩ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች የመጋለጥ ዕድላቸው የሰፋ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ጉድለቶች ለመቅረፍ የመንግስት አገልግሎቶችን በበቂ ደረጃ፣ በግልጽነት፣ በአሳታፊነት እና በተጠያቂነት መርህ ማቅረብ የማይተካ ሚና ያለው ሲሆን፣ ህብረተሰቡ በባለቤትነት እንዲፈጽመው በማድረግ መልካም አስተዳደርን ማስፈን የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ይሆናል፡፡

### 1.2.3 የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት ያለመጠናከር

በሃገሪቱ ያለውን ድህነት ለመቀነስና ለማስወገድ የሚያግዝ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ አውጥቷል፡፡ ፖሊሲውን ወደ ተግባር ለመቀየር ብዙ ባለድርሻ አካለት ተሳትፎ ያስፈልጋል፡፡ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ መገንዘብ እንደሚቻለው የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም በህብረተሰቡ እየተደረገ ያለው ጥረት በተደራጀ መረጃ ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ፣ እንዲሁም አገር አቀፍ የተጠቃሚዎች ምዝገባ ስርዓት ባለመኖሩ ምክንያት ያለአግባብ የሚደገፉና መደገፍ ሲገባቸው የማይደገፉ ዜጎች ያለበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በመረጃ እጥረት ምክንያት የሚከሰተው ፍትሃዊ ያልሆነ የሀብት ተጠቃሚነት መኖር እንዳለ ሆኖ ባልተናበበ አኳኋን የሚደረግ ድጋፍ የጥገኝነት ስሜት ከመፍጠር ያለፈ ዘላቂነት ያለው ዕድገት ሊያመጣ እንደማይችል እሙን ነው፡፡

የህብረተሰቡ የመረዳዳት ባህል በበጎ ጎኑ ሊጠቀስ የሚችል እና በልማታዊ አኳኋን ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ባህላዊ የማህበራዊ ጥበቃ ቢሆንም ህብረተሰቡ እየደገፈ ያለው ተጎጅዎችን ብቻ ሳይሆን ከሃይማኖት ጋር በማያያዝ ሊያመርት የሚችለውን ኃይልም ጭምር በመሆኑ ማምረት የሚችለውን ወደ ሥራ የማስገባት ባህል መዳበር ይኖርበታል፡፡ በልመና መኖር እንደ አንድ አማራጭ ስራ ተቆጥሮ ስምሪት የሚደረግበት ሁኔታ እንዳለም ይታወቃል፡፡ ይህ ደግሞ በበጎ ባህላችንና በመልካም ገጽታችን ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ በተለያዩ አካላት የሚደረጉ ድጋፎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት አካል በመሆን የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ አስተዋፅዖ የሚያደረጉ ቢሆንም እነዚህን አካላት አቀናጅቶና አስተባብሮ የሚመራ ተቋም ባለመኖሩ ምክንያት ችግሩን በዘላቂነት ሊፈታ አልተቻለም፡፡

### 1.2.4 ከገቢ ጋር ያልተጣጣመ የቤተሰብ ምጣኔ እና የቤተሰብ መላላት

የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ባለመተግበሩ ምክንያት የቤተሰብ ቁጥር እየጨመረ በመሆኑንና ይህ ደግሞ ከቤተሰብ ገቢ ጋር ባለመጣጣሙ ምክንያት በርካታ የቤተሰብ አባላት ለምግብ ዋስትና ማጣት ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዜጎች መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን አሟልተው መኖር ካልቻሉ ለጎዳና ኑሮ፣ ለስደት፣ ለለምኖ አዳሪነት፣ ለሴተኛ አዳሪነት እንዲሁም ለተለያዩ ጎጂ ልማዶች ተጋላጭ የመሆናቸው ዕድል የሰፋ ነው፡፡

በቤተሰብ መካከል ያለመግባባት ሲፈጠር እና በተለያዩ ምክንያቶች እናትና አባት ሲለያዩ በአብዛኛው ሕጻናት ከእናቶቻቸው ጋር ስለሚሆኑ ህፃናት ለምግብ ዕጥረት ተጠቂዎች መሆናቸው የማይቀር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀል፣ የአልኮልና አደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚነት እና የቤተሰብ መላላት የገቢ መቀነስን ስለሚያስከትል ለምግብ ዋስትና ዕጦት ተጋላጭነት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

### 1.2.5 ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው የህዝብ ፍልሰት

በከተሞች ለነዋሪዎች ቁጥር መጨመር የተፈጥሮ የህዝብ እድገትና ፍልሰት ሲሆን ከገጠር ወደ ከተሞች የሚፈልሰው የህዝብ ቁጥር ከፍተኛውን አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህም በከተሞች በአንጻራዊ መልኩ የኢንቨስትመንት እያደገ መምጣት የሰው ኃይልን የመሳብ

አቅም ያለው በመሆኑ፣ አርሶ አደሩ ወደ ዘመናዊ አስተራረስና ገበያ መር እየሆነ መሄድ፣ የገጠሩ መሬት በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን ህዝብ መሸከም ባለመቻሉ…ወዘተ ምክንያቶች የገጠሩን ህዝብ ወደ ከተሞች በአማራጭነት ስለሚሄድ ጭምር ነው፡፡ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች መሬታቸውን አከራይተው የሚፈልሱ እና የተወሰነ ጊዜ በገጠር የተወሰነ ጊዜ በከተማ የመኖር ልምድ እንደ የኑሮ አማራጭ የሚወሰዱ ዜጎችም መኖራቸው በቋሚነት አንዱ ቦታ ላይ ስለማይሆኑ አምራች ሆነው የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ መቸገራቸው የማይቀር ነው፡፡

በአጠቃላይ ከገጠር ወደ ከተሞች የሚደረገው ፍልሰት ከከተሞች የተፈጥሮ ሕዝብ ዕድገት ጋር ተዳምሮ የቤትና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚፈልገውን ሕዝብ ቁጥር እንዲጨምር ያደረጉት ሲሆን በሌላ በኩል የህዝቡ አቅምም ይህን ፍላጎት ከማሟላት አልፎ የምግብ ወጪውን የመሸፈን አቅሙ ስለሚፈታተን በከተሞቹ የምግብ ዋስትና እጥረት እንዲኖር አድርጎታል፡፡

### 1.2.6 የአመጋገብ ባህላችን ያስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ

ከአመጋገብ ባህላችን ጋር ተያይዞ በተወሰኑ የእህል ዓይነቶች ላይ ጥገኛ መሆን ለምግብ ዋስትና እጦት የራሱ የሆነ ተፅዕኖ በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ጤፍን ብቻ ተመራጭ የምግብ ሰብል አድርጎ የማየት ሁኔታ መኖሩ፣ የጤፍ ምርታማነት ከሌሎች ሰብሎች አንፃር አነስተኛ መሆኑና ዋጋውም ከሌሎች የምግብ ሰብሎች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚገኘውን ህዝብ ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ማሟላት እየተፈታተነን መሄዱ የማይቀር ነው፡፡

በአገራችን አንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ ከፍተኛ ካሎሪና ምርታማነት ያላቸው አገር በቀል ስራስር፣ ፍራፍሬና ሌሎች የተሻለ የምርታማነት ደረጃ ያላቸው የሰብል ዓይነቶችን በአግባቡ መጠቀም ቢቻል የምግብ ዋስትና ችግር ከመቅረፍ አኳያ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይችሉ ነበር፡፡

### 1.2.7 ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ ያለመጠናከሩ

የምርት ግብይት ሰንሰለት ውጤታማነት የሚለካው ከአምራቹና ከሸማቹ እንዲሁም በሰንሰለቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ምክንያታዊና ለሥራው አዎንታዊ አስተዋፅኦ ባደረጉት መጠን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሲያገኙ ነው፡፡ በመሆኑም የግብይት ሰንሰለቱ ውጤታማ ከማድረግ አኳያ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት አማካይነት በቅባት እህሎች፣ ቡናና ሌሎች የኤክስፖርት ምርቶቻችን ላይ ጥሩ ጅምር ቢኖርም በአሁኑ ወቅት በምግብ ሰብሎች ላይ አምራቹና ሸማቹ እያገኘ ያለው

ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለውጤቱ በአበረከተው አስተዋፅኦ ልክ ነው ብሎ ማስቀመጥ በሚቻልበት ደረጃ አልደረስንም፡፡ ይህም በአምራቹ አካባቢ የዋጋ ያለመመጣጠንና በሸማቹ አካባቢ ያለው ያላግባብ የሆነ የዋጋ ንረት መኖሩን ጉዳዩን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር በግብይት ሰንሰለቱ የተሰማሩ ደላሎች መበራከትና ምርቱን በሸያጭ መልክ ለተጠቃሚው ህብረተስብ የሚያቀርቡ አካላት ጥቂት በመሆናቸው ምክንያት የሰላ የገበያ ውድድር ባለመኖሩ የዋጋ ወሳኝነት ሚናቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎላና የሸማቹን የመግዛት አቅም አንዳንድ ሸቀጦች ላይ ሲፈታተኑት ይስተዋላል፡፡ ይህም ለምግብ ዋስትና ችግር መባባስ በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች አንዱ መሆኑ አልቀረም፡፡ ነጋዴው የነፃ ገበያ መርሆዎችን አንድም በአግባቡ ባለመረዳት አሊያም ለግል ጥቅም በሚያመች መልኩ ትርጉሙን በማዛባት የግብይት ስርዓቱ ተግዳሮት እንዲባባስ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም በተለይ ሥራ ለሌላቸውና አነስተኛ ገቢ ካላቸው የከተማ ነዋሪዎች ጋር ተያይዞ የከተሞች የምግብ አቅርቦት ሰንሰለት ችግር ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የገጠር የፍራፍሬና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርትን ከአምራቾች ተቀብሎ እሴት በመጨመር ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር የሚያቀርቡ የተጠናከሩ ማህበራትና ባለሀብቶች ባለመጠናከራቸው በገጠሩ አምራች የተፈጠረውን ተነሳሽነት ቀጣይ በማድረግ በኩል ክፍተት እንዳይፈጥር ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

### 1.2.8 የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ያለመጠናከርና የከተማ ግብርና ለምርት አቅርቦት እያበረከተ ያለው አዎንታዊ አስተዋፅኦ የተጠናከረ ያለመሆኑ

የከተማ ግብርና በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ፍላጎትን ከሟሟላት ባሻገር ገቢ በማስገኘት ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዳለው ይታወቃል፡፡ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የከተማ ነዋሪዎች በአነስተኛ መሬት ከፍተኛ ገቢ በሚያስገኙ በከተማ የግብርና ልማት ስራዎች ላይ በመሰማራት የምግብ ፍጆታቸውን ከመሸፈን አልፈው የገቢ ምንጭና ሰፊ የስራ እድል መፍጠር ይችላሉ፡፡

በትምህርት ቤቶች፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በፋብሪካዎች፣ በማረሚያ ቤቶች፣ በወንዝ ዳርቻዎች፣ በተራራዎች፣ በአረንጓዴ ቦታዎች፣ በፓርኮች፣ በህንፃዎች፣ በመንገድ አካፋዮች፣ በግለሰብ ይዞታዎች... ወዘተ ስር ያሉ መሬቶች ለከተማ ግብርና ስራ እንዲውሉ ለማድረግ ያለው ዝግጁነትና ተነሳሽነት ክፍተት ያለበት በመሆኑ ከዘርፉ የሚጠበቀው ውጤት ሊገኝ አልቻለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የከተማ ግብርና በተለያዩ ጊዜ የሚከሰተውን የዋጋ ንረትና መዋዠቅ ለመቋቋም የበኩሉን አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት እሙን ነው፡፡ የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ይህንኑ እውነታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለከተማ ልማትና ግብርና ትስስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡ የከተማ ልማት ፖሊሲውም የከተማና ገጠር ትስስርን በጉልህ አብራርቷል፡፡ እነዚህን አቅጣጫዎች ይዞ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ አመራሩ ባለመረባረቡ የሚፈለገውን ያህል ውጤት አልተመዘገበም፡፡ በመሆኑም በከተሞች አካባቢ ያለውን እምቅ የግብርና አቅም አሟጦ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ያሳያል ፡፡

ዘመናዊና የተደራጀ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ያለመጠናከር ከተሞች ጽዱና አረንጓዴ ልማትን በሚፈለገው ደረጃ ማረጋገጥ ሳይችሉ ከመቅረታቸውም በላይ ለአየር ብክለትና ለቆሻሻ ወለድ በሽታዎች መከሰትና ለከተማ ግብርና ያለመስፋፋት የራሱን ድርሻ አበርክቷል፡፡ የአረንጓዴ ልማት በሚገባ ያለመስፋፋት ነዋሪዎች ጤንነታቸው ተጠብቆና የመኖሪያ አካባቢያቸው ለኑሮ ምቹ ከማድረግም አኳያ ክፍተት የሚታይበት ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ አነስተኛ ገቢ ያለው የከተማ ነዋሪ በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ከዕለት ፍጆታው የሚያልፍ ጥሪት አይኖረውም፡፡ በዚህም ምክንያት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በጊዜያዊነትም ይሁን በዘላቂነት ሲያጋጥመው ራሱንና ቤተሰቡን የማስተዳደር አቅም ውስንነት ያጋጥመዋል፡፡

### 1.2.9 የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተጋላጭነት

በኢትዮጵያ በልዩ ልዩ የአደጋ መንስኤዎች ሳቢያ የሚፈጠር የአደጋ ክስተት የተለመደ ነው፡፡ አደጋ በህብረተሰቡ ህይወትና በሃገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅዕኖ በማድረስ የብዙ ዓመታት ጥሪትን ያወድማል፣ ከፍተኛ የልማት መዋዕለ ንዋይን ያባክናል፣ድህነትንም ያባብሳል፡፡

በተጨማሪም መሰረተ ልማትና የተፈጥሮ ሀብትን ያወድማል፣ ህብረተሰቡን ያደኸያል፣ ብሔራዊ ትኩረትና የልማት መዋዕለ ንዋይ ወደ አስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች እንዲዞር አስገዳጅ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ዘርፈ ብዙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የአደጋ መንስዔዎች ከሃገሪቱ የተለያዩ መልክዓ ምድራዊና የአየር ፀባይ እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ጋር የተሳሰሩ ናቸው፡፡ በአንዳንዶቹ መንስዔዎች የሚከሰቱት አደጋዎች ሰፋ ያለ ጉዳትና ጥፋት የሚያደርሱ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ስጋት እንደሆኑ የሚቆዩ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ በዋናነት የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች እንደ ድርቅ፣ ጎርፍ፣ የሰው እና የእንስሳት በሽታዎች፣ ፀረ-ሰብል ተባዮች፣ ርዕደ መሬትና እሳተ ገሞራ ፍንዳታን ከብዙ በጥቂቱ ያካትታል፡፡ ከታሪክ መረዳት እንደሚቻለው በዋናነት የድርቅ ክስተት በሰው ህይወት ላይም ሆነ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ ላይ ጉዳት በማድረስ ለፖለቲካ አለመረጋጋት መንስዔ ይሆናል፡፡ የሰው ሰራሽ አደጋ በዋናነት በሃብት ክፍፍል እና ሌሎች ምክንያቶች የሚከሰት የእርስ በእርስ ግጭት፣ ጦርነት፣ እሳት (የደንና የከተማ) በኮንስትራክሽንና በፋብሪካ ላይ የሚከሰት የሥራ ላይ አደጋ፣ ቴክኖሎጅካል ሀዛርድ፣ በየዕለቱ የሚከሰቱ የአካባቢ ጤና ብክለቶች፣ የተደራጁ ወንጀሎች እንዲሁም የትራፊክ አደጋን...ወዘተ ያካትታል፡፡ እነዚህ አደጋዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ መጥተዋል፡፡

እነዚህን የአደጋ ተጋላጭነት ከሚያፋጥኑ ሁኔታዎች መካከል ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትና ፈጣን የህዝብ ዕድገት፣ የከተሞች አሰፋፈር ዘይቤውን ለመለየት የሚያስቸግር መሆኑ፣ ኑሮው ከገጠርና ከውጭ በሚመጡ ግብዓቶች ግዥ ላይ ያተኮረ መሆኑ፣ የከተሞች ድህነት በአንድ የተለየ ቦታ ላይ የሚከሰት አለመሆኑ፣ ድህነትና የምግብ እጦት በከተሞች በተለያዩ ቦታዎች የተበታተኑ መሆኑ፣ የህገ ወጥ ግንባታዎችና የቆሸሹ ሰፈሮች መስፋፋት፣ የተሟላ የፅዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት አለመኖር፣ የመረጃ እጦት እንዲሁም ባልተጠበቀ ሁኔታ የሚለዋወጥ የአየር ሁኔታ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከተሞች የአደጋ ተጋላጭነታቸው ከገጠሩ ጋር ሲነፃፀር የከፋ የሚያደርገው የመጀመሪያው አደጋ ተጋላጭነት ለሁለተኛ አደጋ ተጋላጭነት መንስኤ በመሆኑ ዜጎች ለጊዜያዊና የዘለቄታ ምግብ ዋስትና ዕጦት ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ በማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ እንደተቀመጠው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ከደረሱ በኋላ ቁስሉን ለማከም ከመረባረብ ይልቅ ቀድሞ መከላከል ስለሚያስፈልግ በዚህ ስትራቴጂ የመከላከሉ ስራ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 1.3 በከተሞች የምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጮች

የከተሞቻችን ችግሮች ደረጃ በደረጃ መፈታት ያለባቸው እና በባህሪያቸውም እርስ በርስ የሚተሳሰሩ ፈርጀ ብዙ ክስተቶችን ያካተተ ነው፡፡ በከተሞች የሚታዩት የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆችና ችግሮች ከከተማ ሕዝብ ዕድገትና ኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር በመጠንም በዓይነትም እየበዙ የሚሄዱ ሲሆኑ ዋና ዋና የምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጮች የሚከተሉት እንደሆኑ ተለይተዋል፡፡

### 1.3.1 አነስተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች

ለአነስተኛ ገቢ መኖር የተለያዩ ምክንያቶች ቢጠቀሱም ዋነኛዎቹ በከተሞች በሚገኘው የሥራ አጥነት ችግር የሚጠቀስ ሲሆን ቁጥሩ ቀላል የማይባል የከተማ ነዋሪ መደበኛ ባልሆኑ ሥራዎች በመሰማራቱ ገቢው ከእጅ ወደ አፍ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በተለያዩ መደበኛ ያልሆኑ የስራ መስኮች ለተሰማሩ ዜጎች ሥራቸውን በሚገባ ሊያከናውኑባቸው የሚያስችሉ ለምሳሌ የመብራት፣ የውሃ፣ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ፣ ትራንስፖርት እና የመሳሰሉት አገልግሎቶችን በአግባቡ መስጠት ባለመቻላችን ለምግብ ዋስትና ዕጦት ተጋላጭነት ይዳረጋሉ፡፡ በአነስተኛ ገቢ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ህጻናት ለዕለት የሚያስፈልጋቸውን የምግብ ፍጆታ ማግኘት ስለማይችሉ ከትምህርት ቤቱና ከማህበረሰብ ካላገኙ ትምህርታቸውን ለማቋረጥና በዚህም ምክንያት የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ሰለባ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በከተሞች ከሚገኘው አብዛኛው ነዋሪ የቤተሰብ ገቢ ከፍተኛው ድርሻ ማለትም 50 በመቶ የሚደርሰውን በምግብ-ነክ እና በመሳሰሉት የፍጆታ ወጪዎች ላይ የሚያውለው በመሆኑ እና እ.ኤ.አ በ2010-11 በተደረገው ጥናት መሠረት 25.7 በመቶ የሚሆነው ነዋሪ ከአጠቃላይ ድህነት ወለል በታች ያለ በመሆኑ የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ ያለው አቅም አናሳ ሆኖ ይገኛል፡፡

የከተማው ህዝብ በተፈጥሯዊ ዕድገትና ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረግ ፍልሰት ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚመጣ ቢሆንም የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕድገት ግን ከህዝቡ እድገት ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑ ምክንያት የከተማ ነዋሪ በሙሉ በቀን በአማካይ ማግኘት የሚገባውን 2200 ካሎሪ ፍጆታ ማግኘት የሚያስችል ቋሚ የገቢ ምንጭ መፍጠር አዳጋች እየሆነ መጥቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከ29 በመቶ ያላነሰው ቤተሰብ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከአማካይ በታች በመሆኑና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች በርካታ ዜጎች በድህነት ሽክርክሪት ቀለበት ስር መሆናቸው መገንዘብ አያዳግትም፡፡ በመሆኑም አሁን ስኬታማነቱ በተግባር እያሳየ የመጣው የከተማ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የማስፋፋት ሥራ በተጠናከረ አኳኋን ከቀጠልን እና መደበኛ ባልሆነ ስራ ላይ በተሰማሩ ዜጎች ስራዎቻቸው እንዳይስተጓጎሉ የሚያስፈልጉ ድጋፍና ግብዓቶች ሳይቆራረጡ ማቅረብ ከቻልን ይህ ችግር ሩቅ በማይባል ጊዜ መፍታት እንደሚቻል እሙን ነው፡፡ እስከዚያ ግን በተደራጀና በተቀናጀ አኳኋን መንግስት ችግሩን ለመፍታት ጣልቃ መግባት ይጠበቅበታል፡፡

### 1.3.2 ጎዳና ተዳዳሪዎችና ለምኖ አዳሪዎች

በሃገራችን የተለያዩ ከተሞች በቤተሰብ መላላት፣ መለያየት፣ ፍቺና ሞት፣ የገቢ ማነስ፣ በጓደኛ ግፊት፣ በተለያዩ ሱሶች በመጠመድ ...ወዘተ ምክንያቶች በርካታ ዜጎች በየአካባያቸው የተፈጠረውን መልካም ዕድል አሟጠው ከመጠቀም ይልቅ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ሲያደርጉ ይስተዋላል።

አብዛኞቹ እነዚህ የጎዳና ተዳዳሪዎች የስነ ልቦናና የክህሎት ስልጠና ቢሰጣቸው ሀገር ገንቢ እና አምራች ኃይል ሊሆኑ የሚችሉ ቢሆንም ተቋማዊና ቀጣይነት ባለው አኳኋን የተሃድሶና የመከላከል ስራዎች የተመቻቹ ባለመሆኑ ምክንያት ህይወታቸውን ጎዳና ላይ በማድረግ ለራሳቸው ስብዕና መጓደልና ለደህንነታቸው አደጋ ከመጋለጣቸውም በላይ በህብረተሰቡና በሃገር ገጽታ ላይ የራሱ ተፅዕኖ መፍጠሩ አልቀረም። ይህ ማህበራዊ ቀውስ በጨመረ ቁጥር ለሃገር ሠላምና ደህንነት መረጋገጥ ማነቆ መሆኑ አይቀርም።

ከዚህ በተጨማሪ የሀገራችን ህብረተሰብ ልመናን እንደ አፀያፊ ተግባር የሚቆጥር የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በተለይም ዋና አምራችና ትኩስ ሀይል የሆነው ወጣት ከመስራት ይልቅ የጎዳና ልመናን እንደ አንድ የገቢ ምንጭ አማራጭ ሲጠቀምበት ይታያል። በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች ልመናን እንደ አንድ የስራ ዘርፍ በማድረግ ስምሪት የሚደረግበት ደረጃ ላይ መደረሱ በየከተሞቹ የሚካሄዱ አንዳንድ ጥናቶች ያረጋግጣሉ።

ልመና የጥገኝነት መንፈስ ከመፍጠሩም ባሻገር በአገራችን የቱሪዝም መስህብነትና መልካም ገፅታ ላይ አሉታዊ ተፅኖ እየፈጠረ ያለ፣ ከሀገራችን የህዳሴ ጉዞ እና ፖሊሲዎቻችን ህዝቡ ለልማቱ ባበረከተው አስተዋጽኦ ልክ ተጠቃሚ እንዲሆን ከተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ጋር የሚሄድ ጉዳይ አይደለም። ከሰብዓዊነትና ከእምነት ጋር በተያያዘ በእምነት ተቋማትና በህብረተሰቡ ያለው የመረዳዳት ባህል ትክክለኛ ተጎጂውን የለየ ባለመሆኑ ለለመነ ሁሉ መስጠቱ ለልመና መስፋፋት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ስለዚህ መንግስት፣ ህብረተሰቡና የሃይማኖት ተቋማት በዚህ ዘርፍ የተሰማራውን ህብረተሰብ አመለካከት በመለወጥ እነዚህ ዜጎች አምራች እንዲሆኑ በማድረግ ለልማቱ የበኩላቸውን አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ የማድረግ ስራ መስራት ያስፈልጋል።

### 1.3.3. ሴተኛ አዳሪዎች

በቤተሰብ ገቢ ማነስ፣ በአስገድዶ መደፈር፣ አላቻ ጋብቻ፣ በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈርስ ትዳርና ስደት፣ የጓደኛ ግፊት፣ የግንዛቤ ችግር፣ ስራ በመምረጥ እንዲሁም በሌሎች ሳቢና ገፊ ምክንያቶች

በርካታ ዜጎች ሴተኛ አዳሪነትን የህይወታቸው አንዱ ማቆያና የምግብ ዋስትናቸው ማረጋገጫ መንገድ አድርገዋል፡፡ ይህ ክስተት በአምራች ዜጋ ጤና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያስከትል ከመሆኑም ባሻገር አምራቹን ሀይል የሚቀንስና የጥገኛውን ቁጥር የሚጨምር የከተሞቻችን አንዱ ማህበራዊ ጠንቅ ነው፡፡

### 1.3.4 ሥራ ፈት ዜጎች

ሀገራችን ባለፉት አሥራ ሁለት አመታት ባስመዘገበችው ባለሁለት አሃዝ ሁለንተናዊ እድገት ምክንያት በርካታ የስራ ዕድሎች እየተፈጠረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአንጻሩ በከተሞች የኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካል ኢኮኖሚ በአመለካከትና በተግባር የበላይነት የያዘበት ሁኔታ በመኖሩ እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ ሁሉም የተማረ ሰው ተቀጥሮ መስራት እንዳለበት የመፈለግ አስተሳሰብ ቀላል ባለመሆኑ በተፈጠሩ የስራ መስኮች ተሰማርቶ ገቢ ለማግኘት የዝግጁነት መጓደል ይስተዋላል፡፡ መንግስት ይህንን አስተሳሰብ ለመቀየር ሰፊ ሥራ በመስራቱ ከፍተኛ መሻሻል ቢኖርም አስተሳሰቡ ግን አሁንም በተሟላ አኳኋን ተስተካክሏል ማለት አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ህብረተሰቡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ በመጣው የተወሰኑ የስራ መስኮችን በፆታ የመመደብ እና ለተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተፈጥሮ የተሰጣቸው የማስመሰል አስተሳሰብ ስራውንና በስራው ላይ የተሰማሩትን የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን የማበረታታት ልምድ ያለመዳበር ይታያል፡፡ ይህም ወቅቱ በፈጠራቸው የስራ ዕድሎች ተጠቅሞ የቤተሰብና የነፍስ ወከፍ ገቢን ከፍ በማድረግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንቅፋት ሆኗል፡፡ በዚህም ምክንያት ስራ ሳያጡ ስራ ፈት እየሆኑ የቤተሰብና የህብረተሰብ ጥገኛ የሆኑ ዜጎች ቁጥራቸው በርካታ ነው፡፡

በመሆኑም በርካታ ወጣቶች መስራት የሚችል ጉልበትና የአዕምሮ ብቃት እያላቸው በሀገር ውስጥ ያለውን የስራ ዕድል ተጠቅመው ራሳቸውን እና ሀገራቸውን በጉልበትና በእውቀታቸው መገንባት ሲችሉ በሃገራቸው እያሉ የማይሰሯቸውን ስራዎች በሰው ሀገር በመስራት የተሻለ ገቢ ለማግኘት በሚል በህገ-ወጥ መንገድ በሚደረግ ስደት ለአካላዊና ለስነ-ልቦናዊ ጥቃት እየተዳረጉ ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለሞትና ዕንግልት ሲዳረጉ እየተስተዋለ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በቤተሰብ፣ በህብረተሰብ እና በሀገር ደህንነትና ገጽታ ላይ ትክክለኛ ያልሆነ ተፅዕኖ እየፈጠረ ነው፡፡

### 1.3.5 ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች

በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት፣ ተደራራቢ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እና ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያን ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በሀገራችን ባልተቀናጀ መልኩ በተለያዩ አካላት የሚደረግ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ልምዶች ቢኖሩም የተቀናጀና ግልጽ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት ባለመኖሩ ምክንያት በርካታ የህብረተስብ ክፍሎች መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን የማሟላት ፈተና ያጋጥማቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት እነዚህ ዜጎች በየጎዳናው፣ በየእምነት ተቋማቱና በቱሪስት መስህብ ቦታዎች ለመለመን መገደዳቸው በራሳቸው ስብዕናና በሀገር መልካም ገጽታ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ ነው፡፡

### 1.3.6. የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎችና ወጣት ጥፋተኞች

ሃገሩን ለማልማት በአበረከተው አስተዋፅኦ ልክ ለመጠቀም ያልፈለገ አካል በየመንገዱ የነዋሪውንና የከተሞቻችን እንግዶች እያስጨነቀና አልፎ አልፎም ለሰዎች ህይወት አደጋ እየሆነም ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ ከአልኮልና አደንዛዥ ዕጽ ጋር ተዳምሮ ለፍተው ለመኖር የሚጣጣሩ ዜጎች የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ በሚያደርጉት ጥረት ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ የሚፈጥር ሲሆን የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎችም የማምረት አቅም ስለሚደክም ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ መሆናቸው አይቀርም፡፡ ከዚህም ባሻገር በጫት፣ አልኮልና በሌሎች አደንዛዥ ዕፆች ምክንያት የአእምሮ ጤና ህመምተኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እጨመረ መጥቷል፡፡ እነዚህ ዜጎች ተደራራቢ ችግር ያለባቸው ስለሆኑ የስነ ልቦና እና የህክምና ተሃድሶ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ አደንዛዥ ዕፆች የተጠመዱ አካላት ለተለያዩ በሽታዎች የተጋለጡ ከመሆናቸውም በላይ ለማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች መስፋፋት እና የሴቶችን የጥቃት ሰለባነት በመጨመር ረገድ የራሳቸውን አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠሩ ነው፡፡

# 2. የስትራቴጂው መነሻ ሁኔታዎችና አስፈላጊነት

## 2.1 የሃገር ውስጥና የውጭ ሀገር የሁኔታዎች ትንተና እና ምርጥ ተሞክሮዎች

### 2.1.1 ከከተሞች ምግብ ዋስትና ጋር በቀጥታ የተያያዙ የመነሻ ሁኔታዎች ትንተና

#### ሀ. የከተሞች የምግብ ዋስትና አለም አቀፋዊ ገጽታ

የምግብ ዋስትና ያለመረጋገጥ በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚታይ ክስተት ቢሆንም በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ችግሩ የሰፋ ሆኖ ይታያል፡፡ ለዚህ ችግር መስፋፋት በምክንያትነት ሊጠቀሱ የሚችሉት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች የየራሳቸው አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖራቸው እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

በዓለም ካለው ሕዝብ ውስጥ 870 ሚሊዮን የሚሆነው በቂ ምግብ የማያገኝ ሲሆን በዚህ ስሌት ሲታይ ከስምንቱ የሰው ልጅ አንዱ የዚህ ችግር ተጠቂ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የችግሩ ተጋላጮች በታዳጊ ሀገሮች የሚኖሩ ሲሆኑ በተለይ ችግሩ ከሰሃራ በታች በሚገኙ ሀገሮች ላይ የበለጠ ጎልቶ እንደሚታይ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ በከተሞች ለሚስተዋለው የምግብ ዋስትና ያለመረጋገጥ ተጠቃሽ ከሆኑ የችግሮቹ መገለጫዎች መካከል በየቀኑ በሚደረግ የግብይት ስርዓት ላይ ጥገኛ መሆን፣ ለእርሻና ተፈጥሮአዊ ሀብት ትኩረት ያለመስጠት፣ ቀጣይነት በሌለዉ አነስተኛ ገቢ በሚያስገኝ የቀን ስራ ላይ መሰማራት፣ ከመሬት ይዞታ ዋስትና ጋር የተያያዙ የህግ ማዕቀፎች ያለመኖር፣ በቂ የሚጠጣ ንጹህ ውሃ ያለማግኘት፣ በቂ መጸዳጃና የጤና ተቋማት ያለመኖር እንዲሁም ደካማ የማህበረሰብ የእርስ በርስ ግንኙነት መረቦች እና ሌሎችም ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም መንግስታት ህጋዊነት በሌለውና በተበታተነ መንገድ ለሚኖሩ እና በድህነት አረንቋ ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች የሴፍትኔት ፕሮግራም በመዘርጋት ማገዝ ያለመቻላቸው ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎች በሚከሰተው የኢኮኖሚ ግሽበት በከፍተኛ ደረጃ ተጠቂ እንደሚሆኑ የተለያዩ የጥናት ሠነዶች ያረጋግጣሉ፡፡

በዓለም የምግብ ፕሮግራም መረጃ መሰረት እ.ኤ.አ ከ2008 ጀምሮ በዓለም ላይ በተፈጠረው የምግብ ዋጋ ግሽበት ሳቢያ ከመቶ ሚሊዮን ህዝብ በላይ ተቀባይነት በሌለው የምግብ እጥረት ተጋላጭ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 75 ከመቶ የሚሆነው ሽምቶ አዳሪው የከተማ ነዋሪ ነው፡፡

## ለ. የኢትዮጵያ ከተሞች ምግብ ዋስትና ነባራዊ ሁኔታ

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በዚህ ዓመት በሃገራችን የከተሞች ህዝብ ቁጥር 18.7 ሚሊዮን እንደደረሰ እና ይህም ቁጥር በየአመቱ 5.2 በመቶ እያደገ እንደሚሄድ የተገመተ በመሆኑ የከተሞች ህዝብ ወደፊት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚጨምር የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ ያመለክታል፡፡ የከተሞቹ የዕድገት ደረጃ የተለያየ ሲሆን በውስጣቸው ያለው ውስብስብ ችግር አይነትና መጠን እንደ ከተሞች የእድገት ደረጃ የሚለያይ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በሀገራችን ያለው የምግብ ዋስትና ችግር በአብዛኛው ስር የሰደደ ሲሆን መንስኤውም የታታሪነት ማነስ፣ ደካማ የግብይት ሰንሰለት፣ የልማታዊ መልካም አስተዳደር መጓደል፣ የአመጋገብ ባህል ፣ በስራና በመረዳዳት ባህላችን ላይ ያለው አመለካከት፣ የቤተሰብ ምጣኔ በበቂ ሁኔታ አለመጠቀም…..ወዘተ ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡


የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ እ.ኤ.አ በ2010/11 ባደረገው የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት መሰረት የምግብ ድህነት ወለል የሚባለው ለአንድ አዋቂ ሰው በዓመት ብር 1985 ሲሆን አጠቃላይ የድህነት ወለል ደግሞ ብር 3781 እና ከዚያ በታች ገቢ ማግኘት ነው፡፡ በጥናቱ መሰረትም በሀገር አቀፍ ደረጃ 29.6 በመቶ በከተሞች ደግሞ 25.7 በመቶ የሚሆነው ህዝብ የሚኖረው ከአጠቃላይ የድህነት ወለል በታች ወይም መሰረታዊ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ነገሮችን የመግዛት አቅም ውስንነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡

### i. የምግብ ድህነት ወለል ሁኔታ በኢትዮጵያ ከተሞች

ባለፉት ተከታታይ አመታት በሃገራችን የተከናወኑት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የድህንነት መጠን በተለይም የምግብ ድህነትም ሆነ ከድህነት ወለል በታች ያለው የህዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመቀነስ ላይ እንደሚገኝ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እንደ አውሮፓዊያን ዘመን አቆጣር ከ1999/00 እስከ 2010/11 በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተካሄዱት ጥናቶች መረጃ መሰረት በከተሞች ያለው የምግብ ድህነት ከነበረበት 36.5 በመቶ ወደ 27.9 በመቶ መቀነሱን ያሳያሉ፡፡ ለዚህም መንግስት

ድህነትን ለመቀነስ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ያከናወናቸው በርካታ ስራዎች ውጤታማ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

**ግራፍ-1፡-** በከተሞች የምግብ ድህነት መጠን ኢንዴክስ




### ii. በከተሞች የድህነት ወለል መጠን

በ2003 የተካሄደው የቤተሰብ ገቢና ፍጆታ ጥናት እንደሚያመለክተው በሃገር አቀፍ ደረጃ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ሰዎች ምጣኔ 29.6 በመቶ ሲሆን በከተሞች ደግሞ ከድህነት ወለል በታች ያለው ህዝብ ምጣኔ 25.7 በመቶ መሆኑን ያሣያል፡፡ በሃገራችን ያለውን የከፋ ምግብ ድህነት ኢንዴክስ ስንመለከት በሃገር አቀፍ ደረጃ 0.031 ሲሆን በገጠር 0.032 እንዲሁም በከተማ 0.027 መሆኑን በ2010/11 የተደረገው ጥናት ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በ1997 እና በ2003 በተደረገው የቤተሰብ ገቢና ፍጆታ ጥናት ውጤት መሰረት በዜጎች መካከል ያለውን የገቢ ክፍፍል ሁኔታ በገጠርና በከተማ ስንመለከት፣ በገጠር በ2004/05 ከነበረበት 0.26 በ2010/11 ወደ 0.27 ከፍ ያለ ሆኖ በከተማ በ2004/05 ከነበረበት 0.44 በ2010/11 ወደ 0.37 መቀነሱን ያሣያል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው በከተሞች ያለው የገቢ አለመመጣጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም በገጠር ካለው የገቢ አለመመጣጠን ጋር ሲነጻጸር የተወሰነ ብልጫ ያለው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይነት በከተሞች በዜጎች መካከል ያለውን የገቢ አለመመጣጠን ለማጣጣም ፈርጀ ብዙ ስራ መስራት እንዳለብን ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

**ሠንጠረዥ-1፡-** የገቢ ክፍፍል በገጠርና በከተማ

| ዓ.ም | Gini Coefficient | | |
|---|---|---|---|
| | ሃገርአቀፍ | ገጠር | ከተማ |
| 1997 | 0.3 | 0.26 | 0.44 |
| 2003 | 0.298 | 0.27 | 0.37 |

**ምንጭ፡** ማስሌ 2003 የቤተሰብ ገቢና ፍጆታ ጥናት

በከተማና በገጠር የሚኖረው ህብረተሰብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያገናኛቸው በርካታ የህይወት ዘርፎች ቢኖሩም የከተማው ህይወት ከገጠሩ የሚለይባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የከተማው ህብረተሰብ በቋንቋ፣ በባህል፣ በአስተሳሰብ እና በትምህርት የሚለያዩ ዜጎች በአንድ አካባቢ ተጠጋግተው የሚሰፍሩበት ሲሆኑ በአንድ አካባቢ የሚገኝ የገጠሩ ህብረተሰብ ከነዚህ መለኪያዎች አንፃር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በሌላ በኩል በገጠር የተቋጥሮ ዝምድና እንደ ዋነኛ የማህበረሰብ ጥበቃ ተቋም የሚያገለግል ሲሆን በከተሞች ደግሞ የላላ ነው፡፡ በተመሳሳይ የከተማው ማህበረሰብ አሰፋፈር በጣም የተቀራረበ፣ የገቢ ማግኛ ዘዴውም በንግድ እና በተለያዩ የስራ ዘርፎች በመሰማራት ሲሆን የገጠሩ ደግሞ አሰፋፈሩ የተበታተነና በቀጥታ በግብርና ምርት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

የከተሞች የህዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየጨመረ በመምጣቱ ከዕድገት ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮች የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ አንጻር አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳዳራቸው የማይቀር ነው፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በአብዛኛው በዝናብ ጥገኝነት የግብርና ስራቸውን ለሚያካሄዱ ሀገራት ወደፊት አደገኛ ሁኔታዎች ሊፈጥር እንደሚችል ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እስከ አሁን የተዘረጉ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች በአብዛኛው ማዕከል ያደረጉት የገጠሩን የህብረተሰብ ክፍል ሲሆን በከተማ አካባቢም ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሰፊ የስራ ዕድሎችን በመፍጠር የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ እንቅስቃሴ የማስፋፋት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመንግስት በኩል የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲስፋፋና ተጨማሪ የስራ እድል መፍጠር እንዲችል እየተደረገ ያለው ጥረትና መሰረታዊ ለሆኑ የፍጆታ እቃዎች እየተደረገ ያለው ድጎማ ድህነትን ለመቀነስ ከሚደረጉ ጥረቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ለአብነት ያህል ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ንግድ ሚኒስቴር በተገኘው መረጃ መሰረት ከ2001 እስከ 2006 ዓ.ም መንግስት 28.6 ሚሊየን ኩንታል በላይ ስንዴ ያሰራጨ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 25,465,757.8 ኩንታል ስንዴ ከውጭ በድጎማ ያስገባው ነው፡፡ ለዚህም 3,771,269,011.8 ብር ድጎማ አድርጓል፡፡ ከ2003-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 625,440 ሜትሪክ ቶን መጠን ያለው ስኳር ከውጪ ሀገር ገዝቶ ያስገባ ሲሆን ለዚህም ከ3.2 ቢሊየን ብር በላይ ድጎማ አድርጓል፡፡ ከ2003-2004 ዓ.ም ባለው ጊዜ ብቻ 365 ሚሊየን ሊትር ዘይት ከውጪ በማስገባት 1.84 ቢሊየን ብር በላይ ድጎማ አድርጓል፡፡ በጠቅላላው ባለፉት አራትና አምስት ዓመታት ለከተማ ነዋሪው የመሠረታዊና የፍጆታ ዕቃዎች አቅርቦት ብር 8.9 ቢሊዮን ያህል ድጎማ ማድረጉን ያስገነዝበናል፡፡

ምንም እንኳን እስከ አሁን በተደረጉ ጥረቶች አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ ቢሆንም በከተሞች ካለው ችግር ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም ውስብስብነት አንፃር ከዚህ በበለጠ መሰራት እንዳለበት ይታመናል፡፡ በተለይ ከከተሞች ዕድገት ጋር ተያያዞ የሚመጡ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ለምግብ ዋስትና እጦት የመጋለጥ እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ተጋላጭ የሆኑ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ በልመና የሚተዳደሩ ዜጎች፣ ሴተኛ አዳሪዎች እና ጧሪ የሌላቸው አረጋውያን እንዲሁም ቀላል የማይባል የህብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ በጣም አስቸጋሪ በሆነ የድህነት ሽክርክሪት ቀለበት ውስጥ እየኖሩ ለከፍተኛ የኑሮ ጫና የተዳረጉ መሆናቸውን ከፍ ብሎ በቀረበው ትንታኔ ተገልጿል፡፡

ህብረተሰቡን ለድህነት ከሚያጋልጡት ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል በከተሞች አካባቢ ያለው የልማታዊ መልካም አስተዳደር ጉድለትና የሥራ አጥነት አንዱ ነው፡፡ በሌላ በኩል የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ስለስራ ያለው የተዛባ አመለካከት ከዚሁ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነው፡፡ በተጨማሪም ህብረተሰባችን በጐ የመረዳዳት ባህል ያለው ቢሆንም እርዳታ አሰጣጡ የተቀናጀ አለመሆን፣ መረዳት የሚገባውና የማይገባው የለየ ያለመሆኑ፣ በዘላቂነት ራስን ለማስቻል ሳይሆን በህይወት ለመቆየት የሚያስችል ምፅዋት ብቻ በመሆኑ የበለጠ የጥገኝነት ስሜት እንዲዳብር ማድረጉ ችግሩ በዘላቂነት እንዳይፈታ እንቅፋት ከሆኑት ምክንያቶች ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡

### 2.1.2. የምርጥ ተሞክሮ ትንተና

#### *ሀ. ዓለም አቀፋዊ የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ተሞክሮዎች*

የምግብ ዋስትና ችግር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትልቅ አለም አቀፋዊ አጀንዳ እየሆነ በመምጣቱ ሃገራት ችግሩን ለማቃለል የተለያዩ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎትና የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችን በተናጠልና በጋራ በመተግበራቸው እንደየ ሃገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ ውጤቶች እየተመዘገቡ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የረሃብ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በኬንያ፣ ቦልሳ ፋሚልያ በብራዚል እና ፕሮግረሳ አፓርችኒታደስ በሜክሲኮ…ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመቅስም ይቻል ዘንድ በሃገርና በከተማ ደረጃ የብራዚል አቅጣጫዎችና የአፈጻጸም ልምዶች እንደሚከተለው ልምዱ ተቀምሮ ቀርቧል፡፡

#### i. የብራዚል የዜሮ ረሃብ ስትራቴጂ

የዜሮ ረሃብ ስትራቴጂ በብራዚል በይፋ የተጀመረው እ.ኤ.አ በ2003 ሲሆን ስትራቴጂው በመርህ ደረጃ ይዞ የተነሳው ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞችን በማቀናጀትና በማስተባበር በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የምግብ ዋስትና ችግርን ለማቃለልና ለማስወገድ ሲሆን በዚህም ሃገሪቱ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣችበት ስትራቴጂ ነው፡፡

የስትራቴጂው ዋና ትኩረት ለችግር የተጋለጡ ዜጎች የምግብ ዕጥረታቸውን በማቃለል ከረሃብ፣ ከድህነትና ከኢኮኖሚያዊ መገለል የሚወጡበት መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ለዚህም ስራውን ከላይ እስከ ታች የሚያስፈጽም መዋቅራዊ አደረጃጀት በሚኒስቴር ደረጃ የተደራጀ ሲሆን ይህም ተቋም ከ10 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ የክልል መንግስታትና የከተማ አስተዳደሮች ጋር አጋርነት በመመስረት 30 ያህል ፕሮግራሞችን አስተባብሮ ወደ ተግባር በመቀየር ተጨባጭ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሴክሬታሪያቱን የሚደግፍና የሚያማክር ሌላ 20 አባላት ያሉት ከተለያዩ ተቋማትና ከህብረተሰቡ የተውጣጣ አማካሪ ካውንስል ነበረው፡፡

እ.ኤ.አ ከ2003 እስከ 2008 ባሉ ስድስት ዓመታት ውስጥ በድህነት ወለል ሲኖሩ የነበሩ ዜጎች በ27 በመቶ (ከ15.4 ሚሊዮን ወደ 11.5 ሚሊዮን) ሲቀንስ ከምግብ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎች ደግሞ በ48 በመቶ ቀንሷል፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ ከተነደፈው የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ስትራቴጂ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ቤሎ ሆሪዞንቴ ተብላ የምትጠራ ከተማ የነዋሪዎቿን የምግብ

ዋስትና ችግሮች ለማስወገድ ፕሮጀክት ቀርፃ ተግባራዊ በማድረግ ጥሩ ውጤት በማስመዝገብዋ ተሞክሮዋ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

### ii. የብራዚልዋ የቤሎ ሆሪዞንቴ ከተማ ተሞክሮ

ቤሎሆሪዞንቴ ከተማ የብራዚል አራተኛ ትልቋ ከተማ ስትሆን እ.ኤ.አ በ1990 2.4 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ይኖርባት ነበር፡፡ በከተማዋ ይኖሩ ከነበሩት 38 በመቶ ቤተሰቦች ከድህነት ወለል በታች፣ 44 በመቶ ህፃናት በድህነት ውስጥ ይገኙ የነበረና ከ0-3 ዓመት ዕድሜ ከነበራቸው ውስጥ 20 በመቶ የሚሆኑት ያልተመጣጠነ ምግብ የሚያገኙ እንደነበር የተለያዩ የጥናት ሠነዶች ያረጋግጣሉ፡፡

እ.ኤ.አ በ1990 ወደ ስልጣን የመጣው አስተዳደር የከተማዋን የምግብ ዋስትና ችግር ለማቃለል አዲስ ፕሮግራም በመቅረጽ ከአካባቢ ማህበረሰብ፣ ከባለሙያዎች፣ ከትምህርት ተቋማት እና ከሌሎች ባለድርሻና ተባባሪ አካላት ተወካዮች ጋር ስምምነት የተደረሰበት የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በከተማዋ የነበረው የረሃብና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ችግሮች ለማቃለል እርብርብ አድርጓል፡፡

ከተማዋ ሴክሬታሪያት በማቋቋምና ሶስት የትግበራ አቅጣጫዎች በመከተል በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠቃሽ የሆነ ለውጥ አምጥታለች፡፡ እነሱም በአስቸጋሪ ሁኔታ ላሉ ዜጎች የሚደረግ ዘላቂና ሁለንተናዊ ድጋፍ፣ የንግድ ስርዓቱን በገጠሩ አምራችና በከተማ ሸማች መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት በመፍጠር የምግብ አቅርቦት ከዋጋ ንረት ጋር እንዲጣጣም የማድረግ ስራዎች እና ማህበረሰብ ተኮር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና ሌሎች የከተማ ግብርና ስራዎችን በማሳደግ ምርትና ምርታማነትን መጨመርና አቅርቦትን ማሻሻል የሚሉ የትግበራ አቅጣጫዎች ነበሩ፡፡ የከተማዋ የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ውጤታማነት ምስጢሮች ከተለያዩ ሰነዶች የሚከተሉት መሆናቸው ተለይተዋል፡-

### 1) የፖለቲካ ቁርጠኝነት

ምግብ የማግኘት መብትን የማስጠበቅ ቁርጠኝነት በብዙ አገሮች ባይታይም በቤሎ ሆሪዞንቴ ከተማ የተወሰደው ምግብ የማግኘት ሰብዓዊ መብት ተፈፃሚ የማድረግ የፖለቲካ ቁርጠኝነት በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ገዢው የሰራተኞች ፓርቲና የዜጎች የፀረ ረሃብ ዘመቻ ንቅናቄ በጋራ በመሆን

ህዝቡ ከረሃብ ለመላቀቅ ፕሮግራሞቹን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ንቅናቄ ፈጥሯል፡፡ የፌዴራል መንግስትም በዚህ መሰረት ከዜጎች የፀረ ረሃብ ንቅናቄና ከገዢው ፓርቲ የተቀመጠውን ተልዕኮ በማስተናገድ አንድነት፣ አጋርነትና ያልተማከለ የምግብ ዋስትና አስተዳደር እንዲኖር አድርጓል፡፡ በአካባቢ ደረጃ ደግሞ ሴክሬተሪያቱ ሁሉንም የከተማ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ወደ አንድ አቅጣጫ በማምጣትና በማስተባበር ውጤታማ ሆኗል፡፡

## 2) አጋርነትና የህዝብ ተሳትፎ

ለሰክሬታሪያቱ ስራዎች ውጤታማነት ሌላው ምክንያት በፕሮጀክቶች ዕቅድና ትግበራ ወቅት የተፈጠረው ቁርጠኝነትና የማህበረሰብ ተኮር ቡድኖችና ተቋማት ሙሉ ተሳትፎ አንዱ ነው፡፡ ሁሉም መያዶች፣ ማህበረሰብ ተኮር ተቋማትና ድርጅቶች ፕሮግራሙን አምነውበት እንዲንቀሳቀሱ ተደርጓል፡፡

## 3) ትምህርት

ለፕሮግራሙ ቀጣይነትና ውጤታማነት አስተዋጽኦ ያደረገው ሌላው ጉዳይ ተከታታይ ትምህርት በመሰጠቱ ነው፡፡ በተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት፣ በአመጋገብ ባህል፣ በምግብ ደህንነት፣ በምግብ አቀራረብና አያያዝ፣ በአካባቢ ጥበቃና ምግብ የማግኘት ሰብዓዊ መብት ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ተከታታይ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡

## 4) ያልተማከለ አስተዳደር

ፕሮግራሙን ውጤታማ እንዲሆን ያደረገው ሌላው ጉዳይ ፕሮጀክቶችን እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ በማውረድ መስራታቸው ነው፡፡ በዚህ አሰራር መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ህብረተሰቡ ስራዎችን በግልጽ አቅጣጫና ተጠያቂነት ባለው አሰራር በመምራታቸው ነው፡፡

## 5) የአካባቢ አስተዳደር ቁርጠኝነትና አመራር

የአካባቢ የፖለቲካ አመራር ቁርጠኝነት በማሳየት የዜጎች ምግብ የማግኘት መብትን ለማረጋገጥ እንደ ዋነኛው አጀንዳው አድርጎ መውሰዱ ለስኬቱ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

ቁጥራቸው የተወሰነ የአመራር ቡድኖች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦችና የህዝብ አደረጃጀቶች ቁርጠኛና እልህ የተሞላበት ስራ በመስራታቸው የከተማዋ ችግር እንዲቀረፍ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

### iii. የሌሎች ሃገሮች ተሞክሮ

በርካታ አገሮች የከተሞቻቸውን የምግብ ዋስትና ችግር ለማቃለል የከተማ ግብርናን እንደ አንድ አማራጭ በመውሰድ ተጨባጭ ለውጥ አምጥተዋል፡፡ የከተማ ግብርናን በአማራጭነት የወሰዱበት ምክንያት አነስተኛ ገቢ ያላቸው የከተማ ነዋሪዎች የምግብ ፍላጎታቸውን ገዝተው ማሟላት ባለመቻላቸው እንዲሁም እነሱን ቀጥተኛ አምራች በማድረግ በአንድ በኩል የምግብ ፍላጎታቸውን እንዲያሳኩ ማገዝ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለተቀረው የከተማ ነዋሪ በተመጣጣኝ ዋጋ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶቻቸውን እንዲያቀርቡ ስለሚያስችላቸውም ጭምር ነው፡፡

ይህን አቅጣጫ በመከተል ለከተሞቻቸው የምግብ ዋስትና ችግር አዎንታዊ አስተዋፅኦ በማድረግ ከተሳካላቸው አገሮች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡- የሃኖይ ከተማ 80 በመቶ ትኩስ አትክልትና 50 በመቶ የእንስሳት እርባታ ውጤት፣ የሻንጋይ ከተማ 60 በመቶ ትኩስ አትክልት፣ 100 በመቶ የወተትና 50 በመቶ የእንስሳት ዕርባታ ውጤት፣ የዳካር ከተማ 60 በመቶ ትኩስ አትክልት፣ 60 በመቶ የወተትና 65 በመቶ የእንስሳት ዕርባታ ውጤት እና የአክራ ከተማ 90 በመቶ የትኩስ አትክልት ፍላጎታቸው ከከተማ ግብርና እያሟሉ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሃቫና ከተማ በ24,387 ሄክታር መሬት 26,000 ህዝባዊ የአትክልት ቦታዎች በመሸፈን በዓመት 25,000 ቶን ምግብ በማምረት የምግብ ፍላጎታቸውን ከከተማ ግብርና ያሟላሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት መልካም ተሞክሮዎች መረዳት የሚቻለው የእነዚህ አገሮች የስኬት ሚስጥር የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ አጋርነትና የህዝብ ተሳትፎ፣ ትምህርት፣ ያልተማከለ አስተዳደር፣ የአካባቢ አስተዳደር ቁርጠኝነትና አመራር ስልቶችን ነድፈው በመተግበራቸው ስለሆነ ሃገራችንም እነዚህን የስኬት ሚስጥሮች ከነባራዊ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ በመተግበር የከተሞችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## ለ. የአገር ውስጥ ተሞክሮዎች

### i. የገጠር ምግብ ዋስትና ተሞክሮ

በ1996 ዓ.ም የጸደቀውና ሥራ ላይ የዋለው የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ አብይ የትኩረት አቅጣጫ በርጥበት አጠር ደጋማና እንዲሁም ቆላማ የአርብቶ አደር አካባቢ በተደጋጋሚ የሚያጋጥመውን ስር የሰደደ የምግብ እጦት ልማታዊና ቀጣይነት ባለው መንገድ ለማቃለል ነው፡፡ በዋናነትም አራት ያህል ፕሮግራሞች ተቀርጸው ሥራ ላይ የዋሉ ሲሆን እነዚህም፡- በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሠፈራ መርሃ-ግብር፣ ልማታዊ የሴፍቲኔት ፕሮግራም፣ የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ፕሮግራም እና የማህበረሰብ ልማት መዋዕለ ነዋይ ፕሮግራም ናቸው፡፡ የሰፈራ እቅድ ለማሳካት የተመረጡ ቦታዎችን የመለየትና የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ማጠናቀቅ የሰፈራ ፕሮግራሙ ስኬታማነት መሰረቶች ነበሩ፡፡ የማህበረሰብ ልማት መዋዕለ ነዋይ ፕሮግራም በአብዛኛው በአርብቶ አደሩ አካባቢ የመስኖ ልማትን ከሌሎች የግብርና ቴክኖሎጂ ጋር በማጣመርና በማስፋፋት ወደ ከፊል አርብቶ አደር የማሸጋገር አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የገጠር የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ፕሮግራም የሚያተኩረው ግብርናን መሠረት ባደረጉ ስራዎች (ከብት ማድለብ፣ በግና ፍየል እንዲሁም ዶሮ እርባታ) እና አነስተኛ የንግድ ስራዎች ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ገበሬዎች የብድር ተጠቃሚዎች አገልግሎት በማቅረብ የቤተሰባቸውን ጥሪት እንዲገነቡና በዚህም ለዘለቄታው የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ነው፡፡ በፕሮግራሙ የሚቀርበው ብድር ተበዳሪዎች በተራ የሚደርሳቸውና በተወሰነ ጊዜም የወሰዱትን ገንዘብ ሰርተውበት መመለስ እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ የተቀመጠ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰቡ ገንዘቦች ተበዳሪዎች ዘንድ የሚገኙ በመሆኑ ፕሮግራሙ የሚፈለገውን ያህል ውጤት ከማስመዝገብ አኳያ እንደተግዳሮት የተለየ ነው፡፡

የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች የቤተሰብ ጥሪት ግንባታም የብድር አገልግሎት ቅድሚያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግና በተለያዩ የግብርናና ከግብርና ውጭም ባሉ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በመሣተፍ ጥሪት እንዲያፈሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ እንደ ዋና ተግባር በመውሰድ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ክልሎች ከ2005 በጀት ዓመት ጀምሮ የክልላቸውን ካቢኔ በማስፈቀድ ለቤተሠብ ጥሪት ግንባታ ፕሮግራም የሚውል የብድር ገንዘብ እንዲመደብ የአሠራር አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

ፕሮግራሙ በመጀመሪያ በአማራ፣ በትግራይ፣ በደቡብና ኦሮሚያ ክልሎች በተዘዋዋሪ ብድር ላይ በተመሠረተ መርሃ ግብር ላይ በማተኮር ለ5 ዓመታት የዘለቀ ፕሮጀክት ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ ፕሮግራሙን በማስፋት የሐረሪን፣ የሶማሌንና የአፋር ክልላዊ መንግስታትና የድሬደዋ ከተማ መስተዳድርን እንዲያቅፍ ተደርጓል፡፡

በአሁኑ ወቅት በ319 ወረዳዎች በአብዛኛው በልማት ተሳታፊ ለሆኑ ለ8.3 ሚሊዮን ወገኖች ድጋፍ እየተደረገ ሲሆን ፕሮግራሙን ከብድር አገልግሎት ጋር በማቀናጀት ተሳታፊዎች በቀጣይ ራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ሥራ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ባለፉት የፕሮግራሙ ዓመታት 2 ሚሊዮን የሚጠጉ ተጠቃሚዎች ራሳቸውን እንዲችሉ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራዎች፣ የትምህርትና ጤና ተቋማት እንዲሁም የገጠር መንገድ ግንባታዎችን በማካሄድ ከፍተኛ የልማት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በመሆኑም ምርትና ምርታማነት፣ የተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት፣ የአካባቢ ስነ - ምህዳር መሻሻል…ወዘተ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

ፕሮግራሙን ለመተግበር የተለያዩ የማስፈጸሚያ መመሪያዎች የተቀረጹና በተከታታይ ወቅታዊነታቸውን ለማረጋገጥ የክለሳ ሥራዎችም በማካሄድ ሥራ ላይ እንዲውሉ የተደረጉ ሲሆን የአፈጻጸም ልምዶችንም በመቀመር ውጤታማ ሥራዎችን በበጎ ተሞክሮነት እንዲስፋፉ ተደርገዋል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ላላቸው ሙያተኞች የቴክኒኩን ሥራ ለመምራት እንዲችሉ ከፕሮግራሙ የዕድገት ደረጃ ጋር የተጣጣሙ ሥልጠናዎች እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተዋረድ የፕሮገራሙን የበላይ አመራር አካላት ማዕከል ያደረገ የአፈጻጸም ግምገማዎች በማካሄድና ዓመታዊ ዕቅዶችን በመንደፍ ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

በፕሮግራሙ አፈጻጸም ወቅት ካጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች መካከል ስንመለከት በተከሰተው የአየር ንብረት መዛባት ተጠቃሚዎቹ ቀድሞ ወደ ነበሩበት ችግር የመንሸራተት ተጽእኖ መፈጠሩ፣ የበጀት ውስንነት፣ የሰው ኃይል እጥረትና የማስፈፀም አቅም ማነስ፣ በማህበረሰቡ አካባቢ ፕሮግራሙን ከመሠረታዊ ችግር መላቀቂያነት ይልቅ እንደ ከመንግስት የተሰጠ ችሮታ በመቁጠር የጥገኝነት ስሜት መፈጠሩና የነበረውን በፈቃደኝነት የተመሰረተ የህብረተሰብ ተሳትፎ ላይ የበኩሉን ተፅዕኖ መፍጠሩና የአመራርና የፋይናንስ አስተዳደሩ የላላ መሆኑ ላይ የነበሩ ክፍተቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ተግዳሮቶች ለመፍታት የተለያዩ የአቅም ግንባታ፣ ክትትልና ግምገማ ሥራዎች በመስራትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ በአካባቢ የልማት ሥራዎች ላይ ውጤት ማምጣት ተችሏል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለዉ በገጠር ተግባራዊ እየሆነ ያለዉ የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ

የበርካታ ዜጎችን ህይወት እና የአካባቢ ገጽታ እየቀየረ ያለ ፕሮግራም ነው፡፡ ፕሮግራሙ ውጤታማ ካደረጉት ሚስጥሮች አንዱ ከዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ድረስ የመንግስት፣የልማት አጋሮችና የህብረተሰቡ ቅንጅት የነበረ መሆኑ ነው፡፡ ከዚሁ አኳያ በአፈፃጸም ወቅት የታዩ ችግሮችን ከግምት ውስጥ በማስገባትና ከዚህ ፕሮግራም ተሞክሮ በመዉሰድ ከከተሞች ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የከተማ ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

### ii. የማህበራዊ ተሃድሶ ልማት ፈንድ ተሞክሮ

የኢትዮጵያ ማህበራዊ ልማት ፈንድ በመላ አገራችን በተለይም ተደራሽ ያልሆኑ የገጠር አካባቢዎች ያለውን ድህነት ለመቀነስ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ቀርፆ እንዲሰራ የተቋቋመ የመንግስት ተቋም ነው፡፡ ፈንዱ በዋናነት የተከተላቸው አቅጣጫዎች ማህበራዊ መሰረት ያለው የህብረተሰቡን ፍላጎትና ጥያቄ ማዕከል ያደረገ፣ አሳታፊ፣ ግልፅና የተጠያቂነትን መርህ ተከትሎ መስራት ሲሆን ተቋሙ አራት ዋና ዋና ዓላማዎችን ይዞ የተነሳ ነው፡፡ እነሱም፦ መሰረታዊ አገልግሎቶችን በማጠናከር የደሃውን ማህበረሰብ ኑሮ ማሻሻል፣ ኢኮኖሚያዊ አቅምን የሚያሳድጉ ጥሪቶች በመፍጠር የደሃውን ህብረተሰብ  የገቢ አቅም ማሳደግ፣ ፕሮጀክቶች በማህበረሰቡ በራሱ እንዲለዩ፣ እንዲዘጋጁ፣ እንዲተገበሩና እንዲተዳደሩ በማድረግ ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎች ጥቅም ላይ ማዋል እና የህብረተሰብ ተኮር ተቋማትን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ አቅም በስልጠና ማጠናከር ናቸው፡፡ አደረጃጀቱም በማህበረሰቡ የተመረጡ ፕሮጀክቶችን የሚከታተል የራሱ የግምገማ ኮሚቴ ያለው ሲሆን የኮሚቴው ዋናው ስራ የተጠቃሚዎች ጥያቄና ፍላጎት በቅደም ተከተል በመለየት ከኢትዮጵያ ማህበራዊ ተሃድሶ ልማት ፈንድ ባለሙያዎች ጋር በመሆን የፕሮጀክቱን ተግባራዊነት መከታተል ነው፡፡

የፈንዱ ዋና ዋና ስራዎች በክልልና በሁሉም የከተማ አስተዳደሮች በተወከሉ ኮሚቴዎች አማካኝነት ክትትል እየተደረገባቸው መፈጸም ሲሆን አገራዊ ቦርዱ በፌዴራል ደረጃ ያለውን ፈንድ ማስተዳደርና መቆጣጠር ነው፡፡ ከልማት ፈንዱ የተገኙት ዋና ዋና ውጤቶችም፦-

1) የልማት ፈንዱ ተግባራዊ በተደረገባቸው አካባቢዎች የማህበረሰቡ አመለካከት፣ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ አቅም አሳድጓል፡፡
2) ከበርካታ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የመስራት አቅም ከማደጉም በላይ ዘርፈ ብዙ ከሆኑት ሴክተሮችና የልማት አጋሮች በጋራ በመስራት ጥሩ ተሞክሮዎች ተገኝቷል፡፡
3) በከፍተኛ አመራር እንዲሁም በክልሎች በተሰጠው ተከታታይ ስልጠና የህብረተሰቡ፣ የባለ ድርሻ አካላትና የልማት ፈንዱ የጋራ የአፈፃፀም ብቃት እንዲያድግ ተደርጓል፡፡

4) በአካባቢ ደረጃ የግል ተቋራጮች አቅም በማደጉ በሚፈጠሩ የግንባታ ስራዎች በርካታ የስራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ አስችሏል የሚሉ ናቸው፡፡

በልማት ፈንዱ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ለአብነት ለመጥቀስ ያህል፡- የማህበረሰቡና የባለድርሻ አካላት የማስፈጸም አቅም አነስተኛ መሆን፣ በውሃና በመስኖ ሴክተሮች የኮንትራክተሮች ዕጥረት ማጋጠሙ እና ልምድ ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል የማግኘትና የማቆየት ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከልማት ፈንዱ ተሞክሮ መማር የሚቻለው ከላይ እስከ ታች የተዘረጋው ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው መዋቅርና የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ መኖር እንዲሁም ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መኖሩ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የልማት አጋሮች፣ የልማት ፈንዱ አመራሮችና ባለሙያዎች፣ የህብረተሰቡ ተወካዮችና ሌሎች ተባባሪ አካላትን ባሳተፈ መልኩ በየዓመቱ በፎረም መልክ የምክክርና የግምገማ መድረክ በመፍጠር ማከናወን መቻሉ በከተሞች ምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ስራችን ላይ እንደ መልካም ተሞክሮ የሚወሰዱ ናቸው፡፡

## 2.2 የስትራቴጂው መነሻ ሁኔታዎች

### 2.2.1. ፈጣን ልማታችንና የህዝብ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ተልዕኮ

የልማታዊ መንግስታችን ተልዕኮ የልማታዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ እና አስተሳሰቡ በሂደት የበላይነት እንዲይዙ ማድረግ ነው፡፡ መንግስት ልማት የህልውና ጉዳይ መሆኑን ተገንዝቦ ለልማት አጀንዳው ልዩ ትኩረት በመስጠት ሁሉንም ያሳተፈ እንዲሆን እና የኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካል ኢኮኖሚን በመናድ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት እየተረባረበ ነው፡፡ ከተሃድሶው ማግስት ጀምሮ መንግስት ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ ህዝቡ ተስፋ እንዲሰንቅ በማድረግ ድህነትን ለማስወገድ እና የልማታዊ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ባደረገው ጥረት የተሳካ ውጤት ማስመዝገብ ጀምሯል፡፡ ሀገራችን ከተዘፈቀችበት ድህነትና ከዚሁ ለመውጣት ከሰነቅነው ራዕይ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ መንግስት ለልማት ያለውን ቁርጠኝነት ከመቼውም በላይ በማሳደግ እርብርቡ ቀጣይ መሆን አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት የማህበራዊ ነክ አላማዎች በሚዘረዝረው  አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ  የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማኅበራዊ

ዋስትና ሊኖረው እንደሚገባ በግልፅ ደንግጓል፡፡ በህገ መንግስቱ  አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት መንግስት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንንና ያለ ወላጅ ወይም ያለ አሳዳጊ የቀሩ ሕጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ እንደሚያደርግ አስቀምጧ፡፡  በንዑስ አንቀጽ 6 ለሥራ አጦችና ችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ በመቅረጽ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ማካሄድ፣ በንዑስ አንቀጽ 7 ለዜጎች የሥራ ዕድሎች እንዲስፋፉ መንግስት አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባው እንዲሁም በአንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የልማታዊ መንግስታችን የልማት እንቅስቃሴ ዓላማ የዜጎችን ዕድገትና መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት መሆን እንደሚገባው አስምሮበታል፡፡ በጥቅሉ የህገ መንግስቱ በኢኮኖሚ ልማት መሠረታዊ ትኩረቱ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዋስትና ማረጋገጥ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ከዚህ አንፃር የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ጉዳይ ህገ መንግስታችን ከአቅም ጋር እየተገናዘበ መሟላት ያለበት መብት መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል፡፡

በዚህ መነሻነት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መንግስት ከህግ ማዕቀፍ ዝግጅት ጀምሮ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን  በማውጣትና ለተግባራዊነታቸውም ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የተለያዩ አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ ይህንኑ ልምድ አጠናክሮ በመቀጠል ከድህነት ወጥመድ እስክንወጣ ርብርቡ በዚሁ አኳኋን መቀጠል ይኖርበታል፡፡

### 2.2.2. ፈጣን ልማትና የከተሞች ሚና

በሃገራችን የከተሞች ልማት ፈጣን የሚሆነው የገጠር ልማትን መሠረት በማድረግ እንዲሁም የከተማና ከተማ ትስስርን በማጠናከር ከተሞች በቀጣይነት የገበያ፣ የአገልግሎትና የኢንዱስትሪ ማዕከል መሆን ሲችሉ መሆኑ በከተማ ልማት ፖሊሲው በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ከከተማ ልማት ዓበይት ሥራዎች መካከል የዜጎች ፍትሃዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማትን ማስፋፋት፣ የቤት ልማት፣ የሕዝብና የአስተዳደር አቅም ማጎልበት፣ የመሬትና የመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ የትምህርትና ሥልጠና ማስፋፋት፣ የጤናና የመዝናኛ አገልግሎት ማስፋፋት፣ የኢንዱስትሪ ልማት፣ የአካባቢ ጥበቃና የከተማ ኘላን ሥራዎች ዋና ዋና ጉዳዮች መሆናቸው በዚሁ ፖሊሲ ላይ አፅንዖት ተሰጥቷቸዋል፡፡

ፈጣንና ፍትሃዊ ልማት በከተሞች ማረጋገጥ ሲባል የመሰረተ ልማት አውታሮች ዝርጋታና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን ለነዋሪው ምቹና ተወዳዳሪነት ያለው ነባራዊ ሁኔታ በከተሞች ማመቻቸት ሲቻል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ከላይ የተዘረዘሩት ዓበይት ተግባራት በተናጠል ሳይሆን በቅንጅት መሰራት ሲችሉ ነው፡፡ ለቅንጅታዊ

አሰራር መሳካትና መልካም ተሞክሮዎችን ለማስፋት እንደ መልካም አጋጣሚ የሚወሰዱት የከተማ ነዋሪው አኗኗር የተጠጋጋ መሆኑን፣ ለሚድያ ተደራሽ መሆኑና የሚሰጡት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ለመቀበል የተሻለ የትምህርት ደረጃ ያለው መሆኑንና የተጠናከረ የሴቶችና ወጣቶች አደረጃጀት መኖሩ…ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው፡፡  እነዚህን ስራዎች በቅንጅት እንዲሰሩ በማድረግ በከተሞች እየታየ ያለውን ሰፊ የስራ አጥነት ችግርና አስከፊ የማኀበራዊ ኑሮ ጠንቅ መቀነስና ብሎም ማስወገድ የዜጎች የምግብ ዋስትና ከማረጋገጡም ባሻገር የሀገሪቱን ራዕይ ለማሳካት የማይተካ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

## 2.2.3 የኢንዱስትሪ ልማትና የህዝብ ተጠቃሚነት

ኢንዱስትሪውን ለማጎልበትና የህዝብ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ከተማንና ገጠርን ባገናዘበ መልኩ ሰፊ ጉልበት የሚጠቀሙና ሰፊ ገበያ ላላቸው መስኮች፣ የማምረቻ መሳሪያዎች፣ የመሸጫና ማምረቻ ቦታና የብድር አቅርቦት ድጋፍ በማድረግና ፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግር ለሚያመጡና ሰፊውን የከተማ ነዋሪ የበለጠ ተጠቃሚ ለሚያደርጉ ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ገቢን ለማሳደግ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡
በተለይም አብዛኛውን ህብረተሰብ የበለጠ ተጠቃሚ እንደሚያደርጉና በሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ከመፍጠር በዘለለ ታላላቅ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪያሊስቶች መፍለቂያ እንደሚሆኑ የታመነባቸው በተለይም ለጥቃቅንና አነስተኛ፣ ጉልበትን በስፋትና ካፒታልን በቁጠባ ለሚጠቀሙ መካከለኛና ትላልቅ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ልዩ ትኩረት በማድረግ ከቴክኖሎጂ፣ በመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ በፋይናንስ፣ መረጃና ሌሎች ግብዓት አቅርቦት እስከ ቴክኒካዊ ልማታዊ ድጋፍ እየተሰጣቸው ነው፡፡
በሃገር ውስጥ የሚመረቱ የኢንዱስትሪ ውጤቶች ከውጭ ወደ ሃገር ለማስገባት የሚጠይቀው የውጭ ምንዛሪ በማስቀረት እና ይልቁንም ኤክስፖርትን በማፋጠን ከሚገኘው ገቢ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከሚኖራቸው ሚና ባሻገር ፈርጀ ብዙ ልማት ቀጣይ እንዲሆን ኃይል ይፈጥራል፡፡ ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ ለማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት፣ ለልማታዊ መልካም አስተዳደር ግንባታና አጠቃላይ ሀገራዊ ኢኮኖሚን በማሳደግና ሰፊ ጉልበትን በመጠቀም የበለፀገ ማህበረሰብና ሀገር ለመፍጠር የኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ በሌላ ሊተካ የማይችል ነው፡፡ በከተሞች የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ፕሮግራሞች ሊሳተፍ ይችል የነበረ ዜጋ በአቅራቢያው የሚቋቋሙ ኢንቨስትመንቶችና ኢንዱስትሪዎች ሲኖሩ ወደ ሥራ በመሰማራት ከችግሩ ሊወጣ የሚችልበት ሰፊ ዕድል ስለሚያገኝ መንግስት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እያደረገ ያለውን ጥረት የሚያግዝ ይሆናል፡፡

### 2.2.4 የምግብ ዋስትናና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዶቻችን ተያያዥነት

መንግስት ድህነትን ለመቀነስ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አዘጋጅቶ በሁሉም አቅጣጫ በመረባረብ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት መንግስት የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ በመቅረፅ አርሶ አደሩ ዘመናዊ የግብርና ልማት ቴክኖሎጂዎችን በብቃት እንዲጠቀም በማስቻልና ለአርሶ አደሩ አዳዲስ የግብርና አሰራሮችን በማላመድ ምርትና ምርታማነትን እንዲያድግ እያደረገ ነው፡፡ የግል ባለሀብቶችን በግብርና ልማት ዘርፍ የሚኖራቸውን ድርሻ ከፍ እንዲል በማድረግ ሃገሪቱን ከድህነት ለማውጣት መጠነ ሰፊ እርብርብ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በተመሳሳይ መንገድ በከተሞች የሚኖረውን ማህበረሰብ የምግብ ዋስትና ችግር ለማቃለል ገቢን ለማሳደግ እና ፍትሐዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እንዲኖር ለማድረግ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እንደዋነኛ አቅጣጫ አስቀምጦ ድህነትን ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑም ግልጽ ነው፡፡ በከተሞች ሥራ አጥነትን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ በጨርቃ ጨርቅ፣ በቆዳ፣ በብረታ ብረትና እንጨት፣ በኮንስትራክሽን፣ በከተማ ግብርና እንዲሁም በተዛማጅ ሥራዎች ለሚሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ ትኩረትና ሁለንተናዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት በተለይ የሴቶችንና ወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ የዘርፉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረታዊ አቅጣጫ ተደርጎ ተቀርጿል፡፡

በተጨማሪም በከተሞች የሚታየውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ማቃለል፣ የከተሞች የአካባቢና መሠረተ ልማት ማፋጠን፣ የከተሞችን የቆሻሻ አያያዝ ማሻሻልና አረንጓዴነታቸውን መጠበቅ፣ የከተማ መሬት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለልማት ማዋል፣ ደረጃውን የጠበቀና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መፍጠር፣ የልማታዊ መልካም አስተዳደር ማስፈን እንዲሁም የነዋሪዎች የምግብ ዋስትና ችግር ማቃለልና ማስወገድ በትኩረት ከሚሰሩ ስራዎች መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና አቅጣጫዎች በመከተል መንግስት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም ፕሮግራሞች በመቅረጽና በመተግበር የምግብ ዋስትናዋ የተረጋገጠ እና መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚያሳካ ራዕይ ሰንቆ ይህንኑ ለማሳካት እየተረባረበ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

## 2.3 የስትራቴጂው አስፈላጊነት

ከነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳው ለመረዳት እንደሚቻለው በከተሞቻችን ከተንሰራፉት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ውስጥ አንዱና ዋንኛው የምግብ ዋስትና እጥረት ሲሆን ይህንንም ማቃለልና ማስወገድ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ምንም እንኳን ቀደም ሲል የሀገራዊ ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ተቀርፆ በሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም የአፈፃፀም ቅኝቱ ገጠር ላይ ያተኮረ በመሆኑ የከተሞችን ልዩ የምግብ ዋስትና እጦት መንስኤዎችና ችግሮችን የቃኘ አይደለም፡፡

በሃገሪቱ ከተሞች እየተካሄደ ያለው የዕድገት እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ሲታይ የምግብ ዋስትናን በተቀናጀ እና ወጥ በሆነ የሥራ አመራር ሥርዓት፣ ተቋማዊና ሕጋዊ ማዕቀፍ የተደገፈ ባለመሆኑ ከምግብ ዋስትና ጋር በተያያዘ ያሉት አሰራሮች በተቀናጀ፣ ወጥና ግልጽ በሆነ አቅጣጫ እየተመሩ አይደለም:: ከተሞች እያደገ ለመጣው የግብርና ምርት አስተማማኝ የአገልግሎትና የገበያ ማዕከል በመሆን ከማገዝ ባሻገር በተመሳሳይ ሁኔታም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ እያስመዘገበ ያለው እና ወደፊት የሚመጣውን እድገት በከተሞች ያሉ አገልግሎቶች እና የምግብ አቅርቦት በቂ ያለመሆን ምክንያት እንዳይጓተት ከተሞች ራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በተጨማሪም የከተሞች የምግብ ዋስትና የሚወሰነው በገጠር ልማትና ዕድገት በመሆኑ የገጠር ልማቱ ዕድገት በከተሞች የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ላይ የጎላ ተፅዕኖ አለው፡፡ በሌላ በኩል ከተሞች የገጠሩን ምርት በመቀበልና ለገጠሩ አስፈላጊ የሆነውን ግብዓት በማቅረብ ጉልህ ሚና ያላቸው በመሆኑ ከተሞች የምግብ ዋስትናቸው ካልተረጋገጠ የገጠሩ ልማት የሚጓተት መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ በመሆኑም የገጠርና የከተማ እንዲሁም የከተማና ከተማ ትስስር በማጠናከር የከተሞችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ ከተሞችም በራሳቸው ጥረት የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተቀናጀና የተደራጀ አሰራር ለመፍጠር እና በየደረጃው ያለውንም አስተዳደር በአግባቡ ለመምራት እንዲችል የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡

# ክፍል ሁለት፡- ከተሞች ምግብ ዋስትና ዓላማና ስትራቴጂዎች

የልማታዊ ሴፍቲኔት ስርዓት በመዘርጋት የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ሰለባ የሆኑት እና በከፋ የድህነት ችግር ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ አካላት የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት በመስጠት፣ የስራ ዕድል በመፍጠር፣ የክህሎት ስልጠና በመስጠትና የብድርና መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ በማድረግ አምራች ዜጋ አድርጎ የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ እና ለፈጣን ልማቱ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ባደረጉት መጠን ተጠቃሚ የሚሆኑበት የዜግነት መብትና ከሃገር ክብርና ገጽታ አንፃርም ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ጉዳይ ስለሆነ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የተሃድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የድሃ ድሃ የሆኑና የተለያየ ድጋፍ ቢደረግላቸውም ወደ ማምረት ተግባር ሊገቡ የማይችሉ፣ ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያን፣ ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እና ለትምህርት መከታተል ችግር የሚያጋጥማቸው ህፃናት የተቋም አገልግሎት እንደ መጨረሻ አማራጭ እንዲያገኙ ከፍተኛ ጥንቃቄና የማጣሪያ ሥርዓት ተዘርግቶ እና ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን ከተለዩ በኂላ በሚመለከታቸው አካላት አማካይነት አማራጭ ይዘጋጅላቸዋል፡፡ በተለያየ ምክንያት ከቤተሰቦቻቸው በመለያየት ለማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ሰለባ የሆኑትም ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲቀላቀሉ ይደረጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በከፋ የድህነት ችግር ውስጥ እንደግለሰብና እንደቤተሰብ የሆኑ እና በሥራ እጦት ምክንያት ወደ ጎዳና ለመውጣት በማኮብኮብ ላይ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ባሉበት ተረጋግተውና የምግብ ዋስትናቸው ተረጋግጦ እንዲኖሩ የቤተሰብና የነፍስ ወከፍ ገቢ ሊያሳድጉ የሚችሉ የገቢ ማስገኛ ፓኬጆች ለዚሁ ኘሮግራም በሚያመች አኳኋን በዝርዝር ተቀርፀው እና ከየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

# 3 ጥቅል ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች

## 3.1 ጥቅል ዓላማ

ለዜጎች በቂ የስራ ዕድል በየአካባቢያቸው በመፍጠር ከድህነት ወለል በታች ያለውን የዜጎች አኗኗር በቀጣይነት እየቀነሱ በመሄድ ማስወገድ ነው፡፡

### 3.2 ዝርዝር ዓላማዎች

1) በከተሞች በስራ ስምሪት ያለውን የተዛባ አመለካከት በማስተካከልና የኢንተርፕሪነር አስተሳሰብ በመገንባት የድሃ ድሃ የሚባሉትን ለይቶ ተጠቃሚ በማድረግ ዕለታዊ ገቢያቸው እንዲጨምርና አስተማማኝ እንዲሆን በማድረግ ምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ፣
2) በስራ ላይ ያልተሰማሩ ወደ ተለያዩ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ተጋላጭ ለመሆን በማኮብኮብ ላይ ያሉ የድሃ ድሃ የሆኑ ስራ አጦችን ባሉበት አካባቢ አምራች ሆነው ራሳቸውን እንዲችሉ እና ለሀገር ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግ፣
3) የሚያገኙት ገቢ ከድህነት ወለል በታች የሆኑ እና ልጆቻቸውን ማስተማር ያልቻሉ ዜጎች እንዲሁም ወላጅ አልባ ሕፃናት በምግብ እጥረት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የሚያስችል ሥርዓት ለመገንባት፣
4) የመስራት አቅም የሌላቸውና ለማህበራዊ ኑሮ ችግርና ጠንቅ የተጋለጡ ዜጎች የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ለማመቻቸት፣
5) ለከተሞች ምግብ ዋስትና መረጋገጥ አቅም የሚሆን የጥናት፣ ምርምር፣ መረጃና ሀብት እንዲሰባሰብ ለማድረግና፣ ተነባቢና ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አሰራርና አደረጃጀት በመፍጠር ተልዕኮውን በመገንባት በአግባቡ መወጣት የሚቻልበት ሥርዓትና አቅም የድህነት ቅነሣ ብሎም ማስወገድ በአስተማማኝ አኳኋን ለመምራት ነው፡፡

# 4 የስትራቴጂው ግቦች

### 4.1 ጥቅል ግብ

ስራ አጦች፣ ሥራ ፈቶች እንዲሁም የምግብ ዋስትና ችግር የሚያጋጥማቸው የድሃ ድሃ የሆኑትን በመለየትና ለማህበራዊ ኑሮ ችግርና ጠንቅ የተጋለጡ ዜጎች ወደ ስራ እንዲሰማሩና የመስራት አቅም የሌላቸው የማህበራዊ ጠንቅ ተጠቂዎች የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ አሁን ያለውን የድህነት መጠን ደረጃ በደረጃ እንዲቀንስ ማድረግና በመጨረሻም ማስወገድ ነው፡፡

### 4.2 ዋና ዋና ግቦች

4.2.1 ኘሮግራሙ ሲነደፍ ጀምሮ በተጠቃሚው፣ በአስፈጻሚው፣ በፈጻሚው እና በህብረተሰቡ ጥምር ጥረት ከከተማ ነዋሪዎች 80 ከመቶዎቹ ስለፕሮግራሙ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

4.2.2. ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት መንግስት፣ ህብረተሰቡና ተጠቃሚዎች ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

4.2.3 በየከተሞቹ በየዓመቱ ለመስራት ከሚታቀዱ መሰረተ ልማቶች ቢያንስ 15 በመቶ የሚሆኑት ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ፓኬጅ ተለይተው ይቀመጣሉ፡፡

4.2.4 ይህ ኢኒሼቲቭ ቀደም ሲል ከተጀመሩ የከተማ ልማት ኘሮግራሞች ጋር በተናበበ አግባብ እንዲቀናጅ በማድረግ የድሃ ድሃ የህብረተሰብ ክፍሎችና ቤተሰቦች በቀጣይነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

4.2.5 የድሃ ድሃ የሆኑ ቤተሰቦች በትክክል ተለይተው በፕሮግራሙ ታቅፈው የሶስት ዓመት ቆይታ ካላቸው ውስጥ ቢያንስ 80% በየዓመቱ እንዲመረቁ ይደረጋል፡፡

# 5. የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

## 5.1 በከተሞች ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር ፍትሃዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ግቡ ዜጎች የመስራት አቅማቸውና ለመስራት ሚያስችላቸው ዕድል ማስፋት፣አስተሳሰብ ለውጥ ማምጣትና ክህሎት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ስትራቴጂ ቀርጾ ተግባራዊ በማድረጉ አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች የሚደረገው ድጋፍ በማሳደግና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያሳትፍ የሥራ ዘርፎችን በመለየት ቀጣይነት ያለው የስራ ዕድል እንዲፈጠር ቢደረግም ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እና የተመቻቸ ማድረጉ ላይ ክፍተቶች ስለሚስተዋሉ የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥ አንዱ መንስኤ ሆኗል፡፡

የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የአመለካከት ለውጥ በማምጣት በርካታ አካባቢን የሚቀይሩና ለሌላ ስራ መፈጠር መሰረት የሚጥሉ የስራ ዕድሎች በስፋት ማመቻቸት አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው፡፡ ይህ የአመለካከት ለውጥ የማምጣትና በርካታ የስራ ዕድሎች የመፍጠር እንቅስቃሴ

ውጤቱ ለኑሮ መሻሻልና ለሀገር ልማት ወሳኝ ቢሆንም ሂደቱ ግን ውስብስብና የበርካታ ባለድርሻ አካላት አጋርነት፣ ትስስርና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

የከተሞችን ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተግባራዊ ያደረጉ ሀገሮች ተሞክሮ የሚያሳየውም ይህንኑ እውነታ ነው፡፡ ለምሳሌ የብራዚልን ተሞክሮ ለመቅሰም በተደረገው ጉብኝት ለመረዳት እንደተቻለው በርካታ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ባለድርሻ አካላት በመቀናጀት ከ30 በላይ ፕሮግራሞች በየመዋቅሩ እንዲፈፀሙ እያደረጉ ነው፡፡ የቦልሳ ፋሚሊያ የምግብ አቅርቦት፣ የቤተሰብ ምግብ አቅርቦትና የቤተሰብ ግብርና ፕሮግራም፣ የወተት ፕሮግራም፣ ብሔራዊ የቤተሰብ ግብርና ፕሮግራም፣ የትምህርት ቤት የምሳ ፕሮግራም እና የተቀናጀ የቤተሰብ ፕሮግራም...ወዘተ በቅንጅት ከሚሰሩ ስራዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የቦልሳ ፋሚሊያ የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ተግባራዊ ሲሆን ብቻውን ተነጥሎ ሳይሆን ከሌሎች ዘርፎች ጋር በመቀናጀት ነው፡፡ የህዝብ ምግብ ቤትም ተግባራዊ ሲሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ቅንጅት እውን በማድረግ እየፈጸሙት ነው፡፡

በመሆኑም በከተሞች ለዚህ ኘሮግራም አፈጻጸም ምቹ የሆኑ የስራ አማራጮች በጥናት ላይ በተመሰረተ መረጃ በተለየ ትኩረት በመለየት ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ በከተማ ግብርና፣ በተቀናጀ ተፋሰስ ልማት፣ በኮምፖስት ዝግጅት፣ በጽዳትና ውበት፣ በአረንጓዴ ልማት፣ በከተማ ውስጥ ያሉ ወንዞች ፅዳትና ልማት እና ሌሎች የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎች የራሳቸው ዝርዝር ፓኬጅ ተቀርፆላቸው በርካታ የስራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል፡፡ በከተሞች ያሉ በከፋ ድህነት ውስጥ ያሉ እና የደሃ ድሃ የሆኑ ዜጎች በጥንቃቄ ተለይተው እንደ አቅማቸውና የሥራ ዝንባሌያቸው በአማራጭ የሥራ መስኮች እንዲሰማሩ ሰፊ ጥናት እየተካሄደ የጠራ መረጃ በመሰብሰብ ከፌዴራል እስከ የታችኛው ባለድርሻ አካል ድረስ የተናበበ የተዋረድ የመረጃ ቋት ይዘረጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር ሊጣጣም የሚችል የስራ መስክ በማዘጋጀት ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙና በተቀመጠው መርሃ-ግብር መሠረት ከድህነት የሚወጡበትና የሚመረቁበት ሁኔታ ይመቻችላቸዋል፡፡

በከተሞች አካባቢ የምግብ ዋስትና ችግር በአብዛኛው የሚታየው አነስተኛ የገቢ ምንጭ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ላይ ነው፡፡ እነዚህ ዜጎች በአብዛኛው ጉልበታቸውን በመተዳደሪያነት የሚጠቀሙ ሲሆን ራሳቸው በመረጡት የስራ መስክ ውጤታማ ሆነው የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ሁለንተናዊ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

የመንግስት ዋና አቅጣጫ ዜጎች በሀገር ውስጥ እየተመዘገበ ባለው ፈጣን ልማት አማካይነት በሚፈጠረው ሰፊ የስራ ዕድል ተጠቅመው የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሌሎች አገሮች ያሉ የስራ ዕድሎችን በህብረተሰባችንና የአገር ገፅታን በማይጎዳ ሁኔታ ዜጎች የክህሎት ስልጠና አግኝተውና የሙያ ብቃታቸው በምዘና ተረጋግጦ ዕድሉን በአግባቡ እንድንጠቀምበት መንግስት ከአሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች እና የየሀገራቱ ዲፕሎማቶች ጋር በመሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአገር ውስጥ ያሉ ልማታዊ ባለሀብቶች ለሚፈጥሩት የስራ ዕድል መንግስት  ድጋፉን አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በዚሁ መሰረት አሁን እየለሙ ባሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ አማካኝነት የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

በሀገራችን ያለውን የሰውና የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም ሊፈጠሩ የሚችሉ የስራ መስኮች ከሌሎች በፈጣን ዕድገት ላይ ካሉና የከተማ ምግብ ዋስትና ካረጋገጡ ሃገሮች ተሞክሮ በመቀመር የማስፋት ስራ ይሰራል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ልዩ የፈጠራ ችሎታ ላላቸው ወገኖች የአእምሮ ሀብት ንብረትነት መብት እንዲያገኙ በማድረግ በፈጠራ ለሚገኙ የስራ መስኮች ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ የማበረታታት ስራ ተጠናክሮ ይተገበራል፡፡ በየጎዳና ላይ ህጋዊ መሠረት በሌለው ንግድ የተሰማሩ ዜጎች ምቹ ሁኔታ እየተመቻቸላቸው የማምረቻና የመሸጫ ቦታ በሕጋዊ አኳኋን አግኝተውና ህጋዊ ፍቃድ አውጥተው እንዲንቀሳቀሱ መንግስት አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

ዘመናዊና የተደራጀ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ከስራ ፈጠራ ጋር በማቃናጀት ከተሞች ጽዱና አረንጓዴ ልማትን በማረጋገጥ የአየር ብክለትና ቆሻሻ ወለድ በሽታዎችን በማስወገድ የነዋሪዎች የጤና ችግር እንዲቃለል ይደረጋል፡፡ የአረንጓዴ ልማት ስራን በሚገባ በማስፋፋት ነዋሪዎች ጤንነታቸው ተጠብቆ ንጹህ አየር አግኝተው እንዲኖሩ ማድረግ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ከማድረጉም ሌላ ለከተማ ግብርና ስራ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በወንዞች፣ ተራሮችና ተዳፋት ቦታዎች የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት በማካሄድ ፈርጀ ብዙ ውጤት እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡ ቦታዎቹ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምቹ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ጐርፍ በአካባቢው እንዲሰርግ በማድረግ ለውሃ ልማት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ተሰብስቦ ወደ ኮምፖስት መቀየር የሚቻለው ተቀይሮ ለግብርና እና ለአረንጓዴ ልማቱ እንዲውል የሚያስችል ሥርዓት ይገነባል፡፡

ለሥራ ዕድል ፈጠራ ምቹ የሆኑ ፕሮጀክቶች ለምሳሌ የውስጥ ለውስጥ መንገድ በጌጠኛ ድንጋይ መገንባት፣ የጎርፍ መሄጃ ቦዮች መስራት፣ የሕዝብ ንጽህና እና መናፈሻ አካባቢዎች ማልማትና መንከባከብ…ወዘተ በተለየ አኳኋን ፓኬጅ ተዘጋጅቶላቸው እና ለዚህ ሥራ እንዲመቻቹ ተደርጎ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

## 5.2 ከተሞች ከገጠሮች እንዲሁም ከተሞች ከከተሞች ጠንካራ ልማታዊ ትስስር መፍጠር

በአገራችን የከተሞች ልማት ፈጣን እና ተከታታይ የሚሆነው የግብርና ልማትን መሰረት በማድረግ የገጠርና ከተማ እንዲሁም የከተማ ከተማ ትስስርን በማጠናከር ከተሞች በቀጣይነት የገበያ፣ የአገልግሎትና የኢንዱስትሪ ማዕከል መሆን ሲችሉ ነው፡፡ የገጠር ምርት ከአምራቹ ወደ ሸማቹ በቀጥታ እንዲደርስና በአምራቹና በሸማቹ መካከል ያሉ ህገወጥ ነጋዴዎችንና የተንዛዛውን የገበያ ስርዓት በማስተካከል ጠንካራ ግንኙነት ይፈጠራል፡፡

በአንጻሩ ደግሞ የከተማ-ከተማ እና የከተሞች-ገጠር በማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ግንኙነት የተጠናከረ በማድረግ  ስትራቴጂው ተግባራዊ በሚደረግባቸው ከተሞች የተሃድሶና የመከላከል ዕቅዶች ዘላቂ ውጤት እንዲያመጡ የሚያስችል ከባለድርሻና ተባባሪ አካላት ጋር ትስስርና አጋርነት ይፈጠራል፡፡ በሚፈጠረውም አጋርነት በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ሰለባዎች ከአካባቢያቸውና ከቤተሰቦቻቸው እንዲቀላቀሉና የተሃድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በአካባቢያቸውም ምቹ የስራ ዕድል ይፈጠርላቸዋል፡፡

## 5.3 የአመጋገብ ባህላችን የሚቀየርበትን ስትራቴጂ ቀይሶ መተግበር

የአመጋገብ ባህላችን ለማሻሻል የጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲሁም የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ የተለያዩ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ነገር ግን ለምግብ ዋስትና መረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ የእንስሳትና የእፅዋት ተዋፅኦዎች ለምግብነት እንዲውሉ ሰፊ ውይይቶች ይካሄዳሉ፡፡ በተለይም የአገራችን አንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ ካሎሪ ያላቸው አገር በቀልና የተሻለ የምርታማነት ደረጃ ያላቸው የሰብል ዓይነቶችን በሁሉም የሃገሪቱ ከተሞች በአግባቡ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 5.4 ዘመናዊ የምግብ የአቅርቦትና የግብይት ስርዓት በአስተማማኝ ሁኔታ መፍጠር

ከብራዚል ተሞክሮ ለመረዳት እንደሚቻለው በከተሞች የምግብ ዋጋ ለማረጋጋትና ተከታታይነት ባለው መልኩ እንዲቀርብ ለማስቻል በከተማ ዙሪያ ያሉ የአትክልትና ፍራፍሬ አቅራቢ አርሶ አደሮች ሳምንቱን ሙሉ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የገበያ ቦታ ተመቻችቶላቸው ምርቶቻቸው በቀጥታ (ያለ ደላላ) የመሸጥ ዕድል አላቸው፡፡ በየሣምንቱ በከተሞች ዙሪያ ባሉ አምራቾች የግብርና

ምርቶች ለከተማው በተከለለው የገበያ ማዕከል የሚያቀርቡ ሲሆን ምርቶቹም ለምግብ አቅርቦትና ግብይት አዎንታዊ አስተዋጽኦ በማድረግ ገበያውን ከማረጋጋት ባሻገር አምራቾች በቀጥታ ለተጠቃሚው የሚሸጡበት አማራጭ መፈጠሩ ለምርት አቅርቦቱ ቀጣይነት መሰረት ጥሏል፡፡

በከተሞች ከሚመረቱ የከተማ ግብርና ምርቶች በተጨማሪ በከተማው ዙሪያ የሚመረቱት አትክልትና ፍራፍሬ በተወሰነላቸው ዋጋ በተከታታይነት በአንዱ ክፍለ ከተማ በተዘጋጀው የመሸጫ ቦታ ይሸጣሉ፡፡ በተሽከርካሪዎች በመታገዝ በመንገድ ዳርቻዎች የሚሸጡ ትኩስ ምግቦች በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ በመቻላቸው በከተማ ውስጥ የሚኖረው ዝቅተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል የምግብ እቅርቦቱን ለማሻሻልና የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ የበኩሉን ሚና ተጫውቷል፡፡

በሃገራችንም ዘመናዊና ፍትሃዊ የንግድና ሽመታ አሰራርን ለማጎልበትና የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ ምርቶች ግብይት በተወዳዳሪ ዋጋ እንዲገኝ ለማድረግ በዘርፉ የሚሰማሩ የሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲበዙና ያሉትም እንዲጠናከሩ የማድረግ ስራው በተጀመረው አኳኋን በቀጣይም የሚሰራ ስራ ይሆናል፡፡

የግብይት ሥርዓቱን ግልፅ፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ በማድረግ የምርትና ሽመታ ቅብብሎሽና ቅንብር ለማዋሀድና በገበያው ፍሰት ላይ የሚታየውን የመረጃ ጥራት መጓደል ለማስተካከል በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ መረጃ ፍሰት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

በነፃ ገበያ ሥርዓቱ ውስጥ የተሰማሩና በቀጣይ የሚሰማሩ ተዋንያን ትስስርና ቅንጅት በማሳለጥ በአምራቾችና ሸማቾች መካከል ድልድይ በመሆን ምርቶችን በማቀባበል የተረጋጋ የገበያ ዋጋን ለመፍጠር ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ በተጨማሪም የንግድ ህግን የሚጥሱ ህገ-ወጥ ነጋዴዎችና ምንም እሴት ሳይጨምሩ በዋጋ ንረት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ በሚፈጥሩ ደላሎች የአቅርቦት ሰንሰለቱን በማስተካከል ወደ ህጋዊ ስርዓት እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

## 5.5 የአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ

በ2013-2014 በወጣው ብሔራዊ የአደጋ ተጋላጭነት ቅነሳ ፖሊሲ እና ስትራቴጅ እንደተቀመጠው አደጋዎች ከደረሱ በኋላ አደጋው የደረሰበትን የህብረተሰብ ክፍል ለማቋቋም ከመረባረብ ይልቅ አደጋው እንዳይደርስ መከላከል የተሻለና የዘመኑ አማራጭ ስትራቴጂ እየሆነ የመጣ አጀንዳ ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች እንዳይከሰቱ ከማድረግ አንፃር የተቀናጀ የቤት ልማት ፕሮግራም፣ የከተሞች የአካባቢ አስተዳደር ልማት ፕሮግራም፣ የከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት

ኘሮግራም፣ የከተሞች አቅም ግንባታና የመልካም አስተዳደር ስራዎች ማሳካት በከተሞች ልማት ዘርፍ ላይ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓላማ ተደርጎ ተቀምጧል፡፡

ይህንንም ዕውን ለማድረግ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ የአደጋ ስጋት ቅነሳና ዝግጁነት ዕቅድ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የተቀናጀ የዕድገት ፕላን ይዘጋጃል፡፡ የህብረተሰብ በተለይም የአደጋ ተጋላጮች ተሳትፎ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና መሻሻል ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የከባቢያዊ ብክለት ሥጋት ቅነሳና ጥበቃ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር አጋርነትና ትስስር ይፈጠራል፡፡ እንዲሁም የተደራጀ መረጃና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ስራ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

## 5.6 ግልፅነት፣ ተጠያቂነት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በመተግበር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ

በከተሞች የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ ለመቀየር እየተደረገ ያለው ጥረት አጠናክሮ በመቀጠል እና በምትኩም ልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ለማረጋገጥ የሚቻለው የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር እና ጠንካራ የልማት ሰራዊት በመገንባትና ህዝቡን ከዳር እስከ ዳር በማሳተፍ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮችን በመለየት ግልጽ የፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ፍልሚያ በመደረግ ላይ ሲሆን ህዝቡ የልማትና የልማታዊ መልካም አስተዳደር እቅዶቻችንን እንዲያሳካ ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ ከመሆኑም ባሻገር ቅሬታ የሚነሳባቸው የአፈጻጸም ችግሮችን በራሱ ተሳትፎ ለይቶ እንዲፈታቸው እንዲሁም የልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችሉ ውጤታማ ስራዎች በስፋት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ጉዳይም ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለበት የአሰራር ስርዓትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ከተሞች ካላቸው የአስተዳደር ባህሪይና የነዋሪዎቻቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶች የተነሳ ችግሮቻቸዉ ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ናቸው፡፡ በተለይ ተዓማኒነት ያለው ትክክለኛ መረጃ ባለመደራጀቱ እና ኪራይ ሰብሳቢነት የሰፈነበት፣ ግልጽነት የሌለውና ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ ነባራዊ ሁኔታ በመኖሩ የዜጎች ችግር የመረዳትና በቅርብ ለመፍታት የራሱ ማነቆ መፍጠሩ የማይቀር ነው፡፡ በመሆኑም የፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል ከሕዝቡ ጋር ሆኖ በማቀጣጠል፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ከላይ እስከ ታች ድረስ በመዘርጋት ለዜጎች ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎቶች የሚሰጥበት ሁኔታ በማመቻቸት  የልማታዊ መልካም አስተዳደር የማስፈን ስራዎች ይሰራሉ፡፡

ለኘሮግራሙ ስኬትና ዘላቂነት ተጠቃሚዎችን በትክክል መለየት ግልጽነት ስለሚፈጥር እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ የኘሮግራሙ ተጠቃሚዎች እስከ አሁን ባሉ የከተማ ልማት ኘሮግራሞች ተጠቃሚ መሆን ያልቻሉና የድሃ ድሃ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መሆን አለባቸው፡፡ በአንጻሩ በከተሞች በአለው የኪራይ ሰብሳቢነት የበላይነት በኘሮግራሙ በትክክል ተጠቃሚ መሆን ያለባቸው በከፍተኛ ድህነት ውስጥ የሉ የድሃ ድሃ የህብረተሰብ ክፍሎች በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ በትክክል መለየትና መንግስት በሚወስነው መሠረት ሀብቱን ማስተዳደር ፈታኝ ጉዳይ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ችግር ለመፍታት የህዝቡ የተደራጀ እንቅስቃሴ በሠራዊት አግባብ ማስፈጸም ወሳኝ መሆኑ የጋር ግንዛቤ ተይዞበት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

ወደ ስራ ስምሪት መግባት የማይችሉ ዜጎች ህብረተሰቡ ውስጥ ሆነው የቀጥታ ድጋፍ እንዲያገኙ ይህ ካልተቻለ ደግሞ የተቋም አገልግሎት እንደመጨረሻ አማራጭ የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በተጨማሪም በከተሞች ብዛት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በኢመደበኛ ንግድና የማምረት ስራ ተሰማርተው የሚገኙ በመሆኑ ለመሸጫና ለማምረቻ የሚሆን በቂ ቦታ በማዘጋጀት የንግድና የማምረት እንቅስቃሴያቸው ሕጋዊ ሥርዓት ተከትሎ እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ ለበርካታ ዜጎች የመስሪያና መሸጫ ቦታ በማዘጋጀት በየአደባባይና አስፋልቱ በጥቃቅን ንግዶች ላይ ተሰማርተው በከተሞች የትራፊክ መጨናነቅ መንስኤ የሆኑትን ሥርዓት እንዲይዙ ይደረጋል፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ የከተማ አስተዳዳር የሚጠበቅበትን የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ከላይ እስከ ታች ያለውን የህዝብ አደረጃጀቶች አንቀሳቅሶ የምግብ ዋስትናን ችግር ስር-ነቀል በሆነ አኳኋን የመፍታት አቅም በማጎልበት በነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳው የምግብ ዋስትና ክፍተት ተጋላጮች ተብለው የተዘረዘሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሀብት ጥሪት እንዲፈጥሩ በማድረግ ከድህነት አዙሪት እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

## 5.7 ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር ተልዕኮውን በቅንጅት ማስፈጸም

በሃገራችን ሁለንተናዊ ልማት ለማምጣትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መንግስት ውጤታማነታቸው በተግባር ያረጋገጡ የተለያዩ የልማት ፓሊሲዎች፣ ስትራትራቴጂዎችና ፕሮግራሞችን በመንደፍ በዘርፎቹ ለሚንቀሳቀሱ ተቋማትና የልማት አጋሮች ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሮ ለተግባራዊነታቸው እርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በከተሞች እየታየ ያለውን የምግብ ዋስትና ክፍተት ዘርፈ ብዙና ውስብስብ በመሆኑ የመከላከልና የመቋቋም ስራው ብዙ አቅምና

ቅንጅት የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑ በተበታተነ መልኩ በተለያዩ አካላት የሚሰጡ ድጋፎችና የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ጥረቶች ተቀናጅተው የሚተገበሩበት ሥርዓት እና አደረጃጀት ተጠንቶ ይፈጽማል፡፡

ይህ ተቋም በዋነኛነት በከተሞች የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የወጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እንዲሁም ፕሮግራሞችን አፈጻጸም የሚከታተል፣ የሚደግፍ፣ የባለሚናዎች ምክር ቤት እንዲቋቋም የሚከታተል ሀብት የማሳባሰብ ሥራ የሚያከናውን ሲሆን በተጨማሪም የሀገራችን ከተሞችና የሌሎች ሃገሮችን ተሞክሮ በመቀመር ልምዶቹ እንዲስፋፉ የሚያመቻች ይሆናል፡፡

ከፌደራል ጀምሮ በየደረጃው የሚደራጅ የከተሞች ምግብ ዋስትና ተቋም ሆኖ የትምህርትና ስልጠና፣ ድጋፍና ክትትል፣ ሰፊ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የትብብርና ሀብት ማሰባሰብ፣ ጥናትና ምርምር፣ የተሃድሶና መከላከል እና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ የስራ ሂደቶች የሚኖሩት መሆን ይኖርበታል፡፡

ተቋሙ ከባለድርሻና ተባባሪ አካላት ጋር አጋርነት በመፍጠር እና የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በስትራቴጂው የተቀመጡ የልዩ ሥራ ዕድል ፈጠራ ፓኬጆች፣ የመከላከልና የተሃድሶ ስራዎች እንዲሰሩ በማድረግ በከተሞች እየታየ ያለውን ከፍተኛ ድህነት፣ የስራ አጥነት እና የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ተጋላጭነት ደረጃ በደረጃ እንዲቀንስ እና በሂደትም እንዲወገድ የማድረግ ተልዕኮ ይኖረዋል፡፡

## 5.8. የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ

በከተሞች ያለውን ከፍተኛ ድህነት ለመቀነስና ብሎም ለማስወገድ፣ የስራ አጥነት ችግር ለመፍታትና የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት አጠናክሮ ለመቀጠል በመንግስት፣ በዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች፣ በሃገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣በሐይማኖት ተቋማት ወዘተ እንዲሁም በህብረተሰቡ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች በተደራጀ እና ተዓማኒነት ባለው ትክክለኛና እውነተኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በተለያዩ አካላት ለዚህ ተግባር የሚውለው የፋይናንስና የሰው ኃይል አቅም በማቀናጀት እና በማጠናከር በዘርፉ ተጨባጭና ዘላቂነት ያለው ለውጥ እንዲመጣ ይደረጋል፡፡

በፌዴራልና በክልል መንግስታት፣ በከተማ አስተዳደሮች፣ በህዝባዊ ማህበራት፣ በልማት አጋሮች፣ በሃገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣ በህብረተሰቡና አጠቃላይ የችግሩ ሰለባዎች ዋነኛ

ባለድርሻና ተባባሪዎች ሆነው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ የፌዴራል፣ የክልል መንግስታት እና የከተማ አስተዳደሮች በዜጎች ላይ የሚታየውን ከፍተኛ ድህነት፣ የምግብ ዋስትና ክፍተት ለማጥበብ በሂደትም ለማስወገድ በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ ዝርዝርና ግልጽ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ ይህንን ተልዕኮ የሚወጣ አደረጃጀት በመፍጠር፣ በጀት በመመደብ፣ ጥናትና ምርምር በማካሄድና ሀብት በማሰባሰብ ዘላቂ የምግብ ዋስትና ፓኬጅ እያዘጋጁ ችግሩን በሚፈታ አኳኋን ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ህብረተሰቡና አደረጃጀቶቻቸው የህዝብ ንቅናቄውን ስራ ለመስራት የሚያስችል ትክክለኛና እውነተኛ መረጃ በመሰብሰብና የአቻ ለአቻ ውይይት በማድረግ በህብረተሰቡ በተለይም በወጣቱ አካባቢ የሚታየውን የተዛባ የስራ ስምሪት እና የሥራ ማማረጥ ባህል የመለወጥ ስራ ይሰራል፡፡ በተገኘው ስራ የመሰማራት የዝግጁነት ባሕል እንዲዳብር ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በግለሰቡና በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረገዉ ርብርብ ከዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ ሂደት ተገቢውን ህዝቡ በየአደረጃጀቱና በየሠፈሩ ተሳትፎና ወሳኝ ሚና መጫወት የሚችልበት አሰራር በመዘርጋት በችግሩ እና በመፍትሔው ላይ የጋራ መግባባት በመፍጠር በባለቤትነት ስሜት የበኩሉን አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ይደረጋል፡፡ የብራዚል ስኬታማና በዓለም ምርጥ የተባለው ተሞክሮም የሚያሳየን ይህንኑ እውነታ ነው፡፡ በርካታ ሚኒስቴር መ/ቤቶች በመቀናጀት ከ30 በላይ ኘሮግራም በሁሉም የመንግስት መዋቅር በማቀናጀት ተግባራዊ በማድረጋቸው ነው፡፡ ለምሳሌ በቦልሳ ፋሚልያ ፕሮግራም የስራ ዕድል ፈጠራና የገቢ ማሳደጊያ ድጋፎች፣ የጎልማሶች ትምህርት፣ የተለያዩ የክህሎት ስልጠናዎች፣ የምግብ አቅርቦትና የቤተሰብ ግብርና ኘሮግራም፣ የወተት ኘሮግራም፣ የህዝብ ምግብ ቤት አገልግሎት፣ ብሄራዊ የቤተሰብ ግብርና ኘሮግራም፣ የትምህርት ቤት የምሳ ኘሮግራም እና የተቀናጀ የቤተሰብ እንክብካቤ ኘሮግራም ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ከፌዴራል የመንግስት ተቋማት በተጨማሪ 65 ሲቪል ተቋማት የዜሮ ረሃብ ራዕይ ስትራቴጂ አጋሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት አገልግሎት በመሥጠት፣ ምግብ በማቅረብ የተለያዩ ቁሳቁሶች በማቅረብ የስራ እድል በመፍጠር ሁሉም ተጠቃሚ በማድረግ ያግዛሉ፡፡ ይህን ስትራቴጂ በበላይነት የሚመራ ሚኒስቴር መ/ቤት ያለ ሲሆን ከታክስ ነጻ መሆን ያለባቸው የስትራቴጂው ማስፈፀሚያ ዕቃዎችና መገልገያዎች (ፍሪጅ፣ ስቶቭ…ወዘተ)፣ የኢንዱስትሪው ውጤቶች፣ ለኘሮግራሙ የሚሰጡ ቁሳቁሶችና እርዳታዎች ማስተባበር እና ለሌሎች ተመሳሳይ ስራዎች በመተባበር ይሰራል፡፡ በዚህ መንገድም ውጤታማ የሆነው የብራዚልያን ስትራቴጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሸላሚ ሆኗል፡፡ ይህንን ተሞክሮ ከሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 5.9 የማስፈጸም አቅም መገንባት

በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ የሚስተዋለውን ከፍተኛ ድህነት ለመቀነስና ብሎም ለማስወገድ የከተሞችን ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚደረገዉን እንቅስቃሴ በተመለከተ በፖለቲካ አመራሩ፣ በአስፈፃሚዉና በፈፃሚዉ አካላት በኩል የዘርፉን ሚናና ዘላቂነት ላይ ጠንካራ ግንዛቤና እምነት በመፍጠር የሚደረገውን እንቅስቃሴ እንደ መሠረታዊ ሥራ ተደርጎ መሠራት ያለበት ነው፡፡ ተልዕኮውንም የሚወጣ ተቋም የመፍጠር፣ የተቋሙ ዓላማ፣ ግብና ግልጽ አሰራር ማስቀመጥና በተገቢው ሰው ኃይል ማደራጀት ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል፡፡

በተጨማሪም በየደረጃዉ ለሚገኙ የአስፈፃሚና የፈፃሚ አካላት በዘርፉ የሚደረገዉን እንቅስቃሴ አስመልክቶ አስፈላጊዉ ስልጠናና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እንዲሰራና ወደ ተግባር ከተገባ በኋላም ቀጣይነት ባለው መልኩ የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃው ለመመዘን የሚያስችል አስፈላጊውን የድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

ከገጠር ምግብ ዋስትና የሚወሰደው አንዱ እና ወደ ከተሞች መስፋፋት ያለበት ምርጥ ተሞክሮ ኘሮግራሙ ባልተማከለ አግባብና በህዝብ አደረጃጀት የነቃ ተሳትፎ የማድረግ ጉዳይ ነው፡፡ የከተሞች ምግብ ዋስትና ኘሮግራምም ያለውን የከተማ አስተዳደሮች ያልተማከለ አስተዳዳር እና የህዝቡ የተደራጀ ተሳትፎ በሠፈር ደረጃ የማረጋገጥ ጉዳይ ማዕከል በማድረግ የሚፈጸምበት ሥርዓት መዘርጋት ለኘሮግራም መሳካት ወሳኝ ስለሆነ በዚሁ አግባብ እንዲፈጸም የቅርብ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 5.10 የሀብት ምንጭና አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት

በፌደራል ደረጃ የሚቋቋመው የከተሞች የምግብ ዋስትና ፈንድ ከማህበራዊ ጥበቃና ሌሎች መሰል ፈንዶች ጋር በማይጣረስ መልኩ በማደራጀት፣ በሀገሪቱ ከተሞች ላይ የተጠናከረ መረጃ ስርዓት እና የግንኙነት መረብ እንዲኖረው በማድረግ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት የመከላከልና ለተጠቂዎችም የተሃድሶ አገልግሎት የመስጠት ሚና መጫወት ይኖርበታል፡፡ ከምግብ ዋስትና ክፍተቱ ጋር በተጣጠመ አኳኋን የተቀረፀውን ስትራቴጂ ወደ ተግባር ለማሸጋገር የሚያስችሉ ለዚህ ኘሮግራም ተስማሚ የሚሆኑ ፓኬጆች ማዘጋጀት እንዲሁም የሀብት ምንጩን በግልጽ አስቀምጦ ለውጤታማ አፈጻጸም የባለሚናዎች የጋራ እርብርብ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በከተሞች እየታየ ያለው የምግብ ዋስትና ችግር በመንግስት አቅም ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ የህብረተሰቡን በጎ የመረዳዳት ልምድ እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በተናጠል የሚሰጠውን ድጋፍ ወደ አንድ የተደራጀና የተናበበ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የልማት አጋር ተቋማትና የመንግስት አደረጃጀቶች በጋራ በመሆን የህብረተሰቡን አመለካከት የመለወጥ ስራ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሀብት ምንጮቹ የመንግስት ትሬዠሪ፣ ህብረተሰቡና መረዳጃ እድሮች፣ ሃገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የግል ባለሀብቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች እና ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች እና ሌሎችም ይሆናሉ፡፡

የሀብት አሰባሰቡ የብዙ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ያለበት እንዲሆንና አስተዳደሩ ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ሀብቱን ለታለመለት ስራ እንዲያውል በማድረግ ተዓማኒነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ስርዓት በመዘርጋት ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡ አሰራሩን የተሳለጠ ለማድረግም በመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መሰረት ከልማት አጋሮች ወደ ፕሮግራም አስፈጻሚው መ/ቤት የብድር ወይም የእርዳታ ገንዘብ በመንግስት ውሳኔ መሰረት በማሰባሰብ ወደ ስራ የሚገባ ሲሆን የአሰራር ሥርዓቱም በሀገራችን የገጠር ምግብ ዋስትና በተተገበረበት አካሄድ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ከዚህ አኳያ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልዩ ትኩረት በመስጠት በዘመናዊ የአሰራር ስርዓት የተደገፈ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ክፍያዎችም ከሚመለከታቸው ባንኮች ጋር በማስተሳሰር የሚፈጸምበት ሥርዓትም ተገንብቶ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

## 5.11. ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ማስፋፋት

ከገጠር ወደ ከተማ ሊፈልስ የሚችለውን የህብረተሰብ ክፍል ሁለንተናዊ ምርታማነቱን የሚጨምር ድጋፍ በማስቀጠል ባለበት አምራች እንዲሆን ማድረግ እንደ አንድ መፍትሔ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ በከተሞች ምርታማነትን ለማሳደግ ዘመናዊ የከተማ ግብርናን ማጠናከርና ማስፋፋት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችል አንድ ተግባር መሆኑን ከበርካታ አገሮች ተሞክሮ መረዳት ይቻላል፡፡

በከተሞች የከተማ ግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አዳዲስ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ዜጎችን በማሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የከተማ ግብርናን ምርታማነት በበለጠ ለማሳደግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂና አዳዲስ ምርታማነትን የሚያሳድጉ አሰራሮችን መከተል ወሳኝ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ምርታማነትን ለመጨመርና ከክረምት ዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ

የገጠርና የከተማ አምራቾች በአካባቢያቸው የሚገኙትን ወንዞች ተጠቅመው እና የጎርፍ ውሃ አቁረው የምግብ ዋስትና ችግራቸው የሚቀርፉበት መንገድ ላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡ ምርታማነትን ለማሳደግና ከህዝብ ቁጥር ጋር ለማጣጣም እንዲቻል በዘርፉ ጥናትና ምርምር እንዲሁም በከተሞች የሰርቶ ማሳያ ማዕከላት ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ረገድ የአገራችን ከተሞች ካላቸው ያልለማ ሰፊ መሬት፣ ውሃ፣ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከፍተኛ የሰው ጉልበት፣ ተስማሚ የአየር ንብረት፣ ሊያሰሩ የሚችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች…ወዘተ እንደ መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም እንደ እንጉዳይ፣ ሞሪንጋ፣ ሰላጣ፣ ቆስጣ፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ጉመን፣ ማንጎ፣ አቡካዶ…ወዘተ የመሳሰሉትን ጨምሮ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት፣ የዶሮ እርባታ፣ የአሳማ ዕርባታ፣ የከብት ማድለብ…ወዘተ ስራዎችን በማጠናከር በከተማ ግብርና የምግብ ዋስትና ክፍተት እንዲጠብ ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚህ ዘርፍ ምርጥ ልምድ ያላቸው አገሮች በመለየት ተሞክሮዎቻቸውን በመቀመር እና እንደየከተሞቹ ሁኔታ በማጣጣም እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

የከተሞች የምግብ ዋስትና ችግር ለማቃለል እንዲሁም በዘላቂነት ለማስወገድ ከሚያስችሉ ስትራቴጂዎች አንዱና ዋነኛው በተዛባ የስራ የአመለካከት ላይ ጠንካራ የልማታዊ አስተሳሰብ ግንባታ ሥራዎችን በመስራት ህብረተሰቡ፣ ባለድርሻና ተባባሪ አካላት ወደ አንድ የጋራ አገራዊ መግባባት መፍጠር ይገባል፡፡ የችግሩን ጥልቀትና አሳሳቢነት በማስረዳትና በማስረፅ ህብረተሰቡን የመፍትሔው አካል የማድረግ ስትራቴጂ መከተል ወሳኝ ከመሆኑም ባሻገር ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ያስችላል፡፡ ስለዚህ አመለካከትን በመቀየር፣ የከተማ ነዋሪውን በሰፊው በማሳተፍ እና የምግብ ዋስትና ክፍተት በማጥበብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስኬታማ የሆኑ አገሮችን በተለየው አኳኋን ተሞክሮዎቻቸውን ወደ ሀገራችን በማምጣትና ከራሳችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥመን ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከተሞች የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ እንዲችሉ የአመለካከት ግንባታ ስራዎችን ከስራ ፈጠራ ጋር በማስተሳሰር በከተሞች ፅዳትና ውበት፣ አረንጓዴ ልማት፣ በከተሞች የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት፣ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ፣ የጎርፍ መሄጃ ግንባታ እና ሌሎች የመሠረተ-ልማት ሥራዎች ዙሪያ በሀገራችን ያሉ ጥሩ ተሞክሮዎች በልዩ ሁኔታ ተቀምረውና የራሳቸው ፓኬጅ ተቀርጾላቸው ይተገበራሉ፡፡ ለምግብ እጦት ችግር የተጋለጡ እና በከፋ ድህነት ውስጥ ያሉ የከተማ ነዋሪዎችን በማስተባበር ልማታዊ በሆነ መንገድ አካባቢያቸውን በማሻሻልና በማልማት በዘላቂነት የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ ሀገሮች ተሞክሮዎች ተቀምረው ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

በተጨማሪም ከዜጎች የገቢ ማሻሻል ጋር በተያያዘ በከተሞች የሚታየውን የምግብ ዋስትና ችግር ለማቃለል የተጠናከረ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት መዘርጋት እንደ አንድ አማራጭ ሲወሰድ ይስተዋላል፡፡ የተጠናከረ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግልት በተለያዩ መንገዶች የሚካሄድ ሲሆን የተቋም አገልግሎት፣ የጥሬ ገንዘብ ማስተላለፍ ዘዴ፣ የመሰረታዊ ፍጆታ ድጎማ፣ የትምህርት ቤቶች እና የምግብ አቅርቦት ዋና ዋናዎቹ አገልግሎቶች ናቸው፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች የድሃ ድሃ የሆኑ ግለሰቦችና ቤተሰቦች እና መስራት የማይችሉ ዜጎች በከፍተኛ ጥንቃቄ ተለይተው ውጤታማና ቀጣይነት ባለው መልኩ ተጠቃሚ ማድረግ እንዲቻል በዚህ ዘርፍ የተሻለ ተሞክሮ ካላቸው አገሮች በመቀመር ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 5.12 የአህዝቦትና የተግባቦት ዝርዝር እቅድ አዘጋጅቶ የማስፈጸም አቅጣጫ መከተል

የልማታዊ ኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ የጠራ ዓላማና ግብ ያለው ነው፣ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የሚያርም፣ የህብረተሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ሁለንተናዊ ተሳትፎ በአግባቡ የሚያረጋግጥ የሁለትዮሽ የተግባቦት ዘዴ ነው፡፡ ይህ የኮሚኒኬሽን ዘዴ በህበረተሰቡ ውስጥ የልማታዊ አስተሳሰብ የበላይነት እንዲያገኝ፣ የዜጎች ፍትሃዊና ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ከማድረጉም በላይ የተመዘገቡ ፈጣንና ተከታታይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስቀጠል በእጅጉ የሚያግዝ መሳሪያ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የከተሞች ምግብ ዋስትና ሰትራቴጂን ተግባረዊ ለማድረግ የበርካታ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና አጋርነት የሚያስፈልገው በመሆኑ እነዚህ አካላት በከተሞች ያለውን የድህነት ሽክርክሪት የሀገርና የዜጎች ችግር መሆኑን ተገንዝበው በጋራ እንዲረባረቡ የማያቋርጥ የአህዝቦትና ተግባቦት ስራ የመስራት አቅጣጫ እንከተላለን፡፡

# ክፍል ሶስት፡- የባለድርሻ አካላት ሚናና የአፈጻጸም ስልቶች

## 6. የአስፈጻሚዎች የተዋረድ ተልዕኮ

የፌዴራልና የክልል መንግሥታት፣ የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻና ተባባሪ አካላት በቅንጅትና በመናበብ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነቶች በብቃት መወጣት የሚኖርባቸው ሲሆን የእያንዳንዱ አካል የተናጠልና የጋር ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 6.1 ተጠቃሚዎች

1) በከፋ ድህነት ውስጥ ያሉ የድሃ ድሃ የሆኑ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ሠርቶ መለወጥ የሚቻል መሆኑን አምኖ በመቀበል እና ባሉ የስራ አማራጭ መስኮች በመሰማራት ራስን ለመርዳት፣ ከሌሎች ጋር ለመስራትና ሀገርን ለማልማት ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፣
2) የቁጠባ ባህላቸውን ማዳበርና የተሰጣቸዉን ብድር በአግባቡ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፣
3) ምርትን በጥራት፣ በወቅቱ እና በተሻለ ዋጋ በማቅረብ ተወዳዳሪ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡
4) ከጠባቂነት ስሜት ተላቀው የውስጥ ችግሮቻቸውን በራሳቸው አቅም መፍታት፣ ራስን በክህሎትና ኢንተርፕሪነርሺፕ ማብቃት ይጠበቅባቸዋል፣
5) የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትንና ድርጊት አጥብቆ በመቃወም ልማታዊ አስተሳሰብ የበላይነት እንዲይዝ አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 6.2. ህብረተሰቡ

1) ከኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጋር ተያይዞ የመጣውን የሥራ ትጉህነት ክፍተት በማውገዝ ስራ ወዳድ እና ራዕይ ያለዉ መልካም ዜጋ መፈጠር እንዳለበት አምኖ ለተግባራዊነቱ ይንቀሳቀሳል፣
2) የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ያወግዛል፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለዉ አሰራር እንዲሰፍን የድርሻውን ይወጣል፣
3) በልመና ያደገ ትውልድም ሆነ ሀገር የሌለ መሆኑን ተገንዝቦ በተበጣጠሰ መልኩ የሚያደርገውን ድጋፍ ተቀናጅቶ ቢሰራበት ዘላቂ ለውጥ እንደሚመጣ ተረድቶ ድጋፉን በየደረጃው ለሚዋቀረው የከተሞች ምግብ ዋስትና አደረጃጀት ያደርጋል፣
4) ህብረተሰቡ በየዕለቱ ከዕምነት ወይም ከሰብአዊነት በመነሳት የሚያደርገውን ተረጂውን በአግባቡ ያለየ ምጽዋዕት አምራች ሊሆን የሚችለውን ሀይል ጥገኛ እንዲሆን በማድረግ

በሀገር ኢኮኖሚና ገጽታ እንዲሁም በዜጎች ስብዕና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያስከተለ መሆኑን መገንዘብ፣ በመንግስት የሚቀረፁ የልማትና የልማታዊ መልካም አስተዳደር አጀንዳዎች ከዕቅድ እስከ አፈፃፀም ያሉ ተግባራትን በባለቤትነት በመሳተፍ በንቅናቄ ይተገበራል፡፡

5) የህዝብ አደረጃጀቶች በተለይም ሴቶችና ወጣቶች ማህበራት፣ እድሮች፣ በተጠቃሚዎች መረጣና ምልመላ እንዲሁም ለፕሮግራሙ አፈፃፀም የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 6.3 የመንግስት ሚና

የመንግስት ድርሻ ሲባል የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደሮችንና ስትራቴጂው ተግባራዊ የሚሆንባቸው በየደረጃው ያሉ መንግስታዊ የአስተዳደር እርከኖችና መዋቅሮችን ይመለከታል፡፡ ይህንን ስትራቴጂ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ባለድርሻ እና ተባባሪ አካላትን የሚያስተባብር ተቋም በፌደራል ደረጃ ይለያል፡፡ በየደረጃውም የሚመለከተው አካል ተለይቶ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የከተሞች ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ለማስፈፀም የሚረዱ አስፈላጊ የሆኑ ስትራቴጂዎች፣ የልማት ፓኬጅ፣ የህግ ማዕቀፎችና የማስፈጸም አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ በማድረግ ለትግበራው አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠት ስራ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም የፕሮግራሙን ችግሮች ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶች ያከናውናል፡፡ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጩ ይደረጋል፡፡ ተልዕኮው የተሰጠው ተቋም አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡ ጉድለቶች በቀጣይ እንዲስተካከሉ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

በተበታተነ መልኩ ሲሰጥ የነበረውን የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት በተደራጀና በተቀናጀ እንዲሁም በመረጃ ላይ ተመስርቶ ተግባራዊ እንዲሆን የሚያስችል አጋርነትና ትስስር በመፍጠር ፍትሃዊ የሀብት ተጠቃሚነት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር በመዘርጋት ተአማኒነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት እንዲገነባ ይደረጋል፡፡ የተለያዩ የልማት አጋሮች፣ የሃይማኖት ተቋማት እና ህብረተሰቡ በማስተባበር ለፕሮግራሙ ዘላቂነት መረጋገጥ የሚረዳ የሀብት ማሰባሰብ ሥራ ይሰራል፡፡ በሥራና በአመጋገብ ባህላችን ዙሪያ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ያልተስተካከለ አመለካከት ለመቀየር የሚያስችል ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥራ ይሰራል፡፡ በዚህ ዘርፍ ሊከሰት የሚችለውን የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር በመድፈቅ የልማታዊ መልካም አስተዳደር ለማስፈን የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙ ውጤታማ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል፡፡ የእያንዳንዱ የመንግስት ተቋማት ዝርዝር ኃላፊነትና ተግባር በአባሪነት ተያይዟል፡፡

## 6.4 የልማት አጋሮች

የሃይማኖት ተቋማት፣ ሃገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የልማት አጋሮች፣ ወዘተ ሲሆኑ የእነዚህ አካላት ዋና ዋና ኃላፊነቶችም የሥራ ታታሪነት አመለካከትን በማጎልበት የአመጋገብ ባህል በማሻሻል፣ሀብት በማሰባሰብ፣ የልማታዊ መልካም አስተዳደር በማስፈንና በፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል፣ እና ሌሎች ስትራቴጂውን ለማስፈፀም የሚያስችሉ ድጋፎችን በማድረግ ተጠቃሚዎቹ ከገቡበት የከፋ ድህነት እንዲወጡ ዘላቂ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

### 6.4.1 የአካል ጉዳተኞች ማህበራትና ፌዴሬሽኖች

1) የአባሎቻቸውን ቁጥር እና አይነት በመለየት ሊሰማሩባቸዉ የሚችሉ የስራ መስኮች አጥንተው ያቀርባሉ፣
2) እንደ የአካል ጉዳታቸዉ አይነት መጠን ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራሉ፣
3) አካል ጉዳተኞች ስለራሳቸውና በህብረተሰቡ እንዲሁም ህብረተሰቡ ስለ አካል ጉዳተኞች ያላቸውን የተሳሳተ አመለካከት ለመለወጥ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማጎልበቻ ስራዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይሰራሉ፡፡

### 6.4.2 ሃገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

1) በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በማቋቋምና በመከላከል ሂደት ውስጥ የስነ ልቦናና የክህሎት ስልጠና በመስጠት ድጋፍ ያደርጋሉ፣
2) ለስትራቴጂው ማስፈጸሚያ የሚሆን የፋይናንስና የማቴሪያል ድጋፍ ያደርጋሉ፤ የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

### 6.4.3 የሃይማኖት ተቋማት ፎረም እና አባላቱ

1) የሃይማኖት ተቋማት በእርዳታ አሰጣጥ ላይ ያላቸው አመለካከት ላይ የጋራ መግባባት እንዲኖራቸው ያደርጋል፣
2) ተቋማት የተከታዮቻቸው እርዳታ አሰጣጥ ላይ ያለው አመለካከት ለመለወጥ ተከታታይነት ያለው ሥራ ያከናውናል፣
3) ከተከታዮቻቸው ለስትራቴጂው ማስፈጸሚያ ሃብት ሰብስበው ገቢ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

### 6.4.4 የዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች

1) ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ በመንግስት ለሚቀርቡላቸው ፕሮጀክቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ፣
2) የሚሰጡት ድጋፍ በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ይከታተላሉ፡፡

## 6.5 የግሉ ዘርፍ ሚና

በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መንግስት ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የበኩሉን ተሳትፎ ያደርጋል፡፡ በዚህም መሰረት ለስራው ጠቃሚ የሆኑ መለስተኛ ባለሙያዎች ሰልጥነው ሲቀርቡለት በሚፈልገው መጠን ለመውሰድ ይተባበራል፡፡ በከተሞች ፅዳትና ውበት፣ አረንጓዴ ልማት፣ ከተማ ግብርና፣ …ወዘተ ሥራዎች ላይ ይሳተፋል፡፡ የምርት አቅርቦትና የገበያ ሰንሰለት እንዲስተካከል ከመንግስት ጋር በቅንጅት ይሠራል፡፡ ሌሎች ስትራቴጂውን ለማስፈፀም የሚያስችሉ ድጋፎችን በማድረግ የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡ መንግስትም የግሉ ዘርፍ በስራ ሰዓት ለሰራተኞች ምግብ በማቅረብ እያደረገ ያለውን የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ በጎ ጅምሮች አስፈላጊውን እውቅና ይሰጣል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በጎ አድራጊ ግለሰቦችም በምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ሂደት የጎላ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

## 6.6 የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች

1) የአመለካከት ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ አዝናኝና አስተማሪ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች እና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በማቅረብ ለአስተሳሰብ ለውጥ ስራ አስተዋስኦ ያደርጋሉ፡፡
2) በፌደራል ደረጃ ለሚደረገው የሀብት ማሰባሰብ ስራዎች ለሚዘጋጁ ኮንሰርቶች በመሳተፍ አጋርነታቸውን ያሳያሉ፡፡

# 7. የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

## 7.1 የከተማ ምግብ ዋስትና ለማስፈጸም የልማት ሰራዊት ግንባታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት አቅጣጫ መከተል

የልማት ሰራዊት ተልዕኮው በከተሞች ፈጣንና ተከታታይነት ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ እና የልማታዊ መልካም አስተዳደር ለመገንባት ከተማ ማዕከል በማድረግ ታቅደው በሚሰሩ ስራዎቻችን ላይ መረባረብ ነው፡፡ የከተማ ልማት ሰራዊት ኃይል የሚገነባውም በከተማ ልማት ስራዎቻችን ዙሪያ አፈፃፀም ሂደት ይሆናል፡፡ የከተማ ልማት ሰራዊት ግንባታ ያለ ትክክለኛ የፖለቲካ አመራርና የአፈፃፀም ጥበብ ሊፈፀም የሚችል ተግባር አይደለም፡፡ ምክንያቱም የከተማ የፓለቲካ አመራር አቅም የሚገነባው በተግባር የልማት ማነቆዎችን በመፍታት ሂደት በመሆኑ ነው፡፡ እየተጠናከረ የሚሄድ ሰራዊት በብቃት ማነቃነቅ የሚችል የፖለቲካ አመራር በየደረጃው መፍጠር የሚቻለውም በዚህ ሂደት ነው፡፡ ስለዚህ የከተሞች ምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ሥራችን የአመራር ጥበብ የሰራዊቱ በተግባር ሂደት ውስጥ የመፍጠርና ይህን ትኩረት አድርጎ የሚፈፀም በመሆኑ ከኘሮግራሙ ትግበራ መርሆዎች አንዱ እና መሠረታዊው ይሆናል፡፡

ሁለተኛው የሰራዊት ግንባታ ክንፍ የሕዝብ አደረጃጀት ነው፡፡ በፌዴራል ከመ/ቤታችን ጋር ግንኙነት ካላቸው የህዝብ አደረጃጀቶች እና ማህበራት ጋር የሚኖረው ሥራ ግንኙነት ትኩረት የምንሰጠው ይሆናል፡፡ ይህ በሰራዊት ግንባታ መልክ ብቻ ሣይሆን ማህበራቶቹ ልማታዊ አስተሳሰብ ለመገንባት የከተሞች ምግብ ዋስትና ኘሮግራሙ በተፋጠነ መንገድ ለማስፈጸምና ድጋፋዊ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው የሚሰራ ስራ ይሆናል፡፡ ለሕዝብ ተሳትፎ ከወረዳ በታች ባለው አደረጀጀት ማለትም በቀጠና እና በሰፈር የሚፈጠረው የሴቶች፣ የወጣቶችና የነዋሪዎች አደረጃጀት ለሰራዊት ግንባታው ዋናው የትኩረት መድረክ ተደርጎ ተለይቷል፡፡ የወጣቶችና የሴቶች ሊግ ከፌዴራል ጀምሮ በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በጋራ የሚረባረቡበት ሥርዓትም መዘርጋት ይኖርብናል፡፡ የታሰበውን የከተሞች ምግብ ዋስትና ኘሮግራም ዓላማዎቹና ግቦቹን በዘላቂነት ማሳካት የልማታዊ ሠራዊት አስተዋፅኦ የማይተካ ነው፡፡ የድሃ ድሃ ግለሰቦችና ቤተሰቦች በትክክለኛና በእውነተኛ መንገድ እንዲለዩ እና ባልተገባ መንገድ መጠቀም የመፈለግ አዝማሚያ ሲኖር ታግሎ የማስተካከል ከሠራዊቱ አባላት ይጠበቃል፡፡

በመሆኑም የከተሞች ምግብ ዋስትና ፕሮግራም አማካይነት የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ስራዎቻችን በህዝብ ንቅናቄ ለመፈፀም እንዲቻል የፖለቲካ አመራር የሚሰጠውን አደረጃጀት፣

አስፈጻሚው መንግስትና ግንባር ቀደም ፈጻሚው እንዲሁም የከተማ ህዝብ ባለቤት ሆኖ በጋራ መግባባት፣ በቅንጅት እና ወጥ በሆነ አደረጃጀት እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በህብረተሰቡ መካከል ቀጣይነት ያለው ውይይትና የአስተሳሰብ ትግል የሚደረግበት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በንቅናቄው ሂደት የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮችን ለይቶ በጋራ መታገልና ከምንጩ ማድረቅ በማስፈለጉ የለውጥና የልማት ሰራዊት ግንባታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል፡፡

## 7.2 የሚመለከታቸው ባለ ሚናዎች በተሟላ አኳኃን የማሳተፍ አቅጣጫ መከተል

የከተሞች ምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ሥራችን በከተማ ነዋሪው ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ መሆን ስላለበት ስትራቴጂውን ከማስተዋወቅ ጀምሮ ህዝቡ በየደረጃው ተሳታፊ የሚሆንበት፣ የስትራቴጂው ትግበራ ከተጀመረ በኋላም ህዝቡ ከስትራቴጂው በስተጀርባ ስላሉ መሰረታዊ የአመለካከትና የልማታዊ መልካም አስተዳደር ችግሮች የተሟላ ግንዛቤ በመያዝ ለአፈፃፀማቸው የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማድረግ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡

የከተማ የፓለቲካ አመራሮችና አስፈጻሚ አካላት ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት በከተሞች ያለውን የምግብ ዋስትና ዕጦት ለመቅረፍ የኪራይ ሰብሳቢነትን አስተሳሰብና ድርጊት አምርሮ በመታገል ለልማትና የልማታዊ መልካም አስተዳደር ግንባታ የሚኖራቸው ቁርጠኝነት እንዲጠናከር የሚያስችል የማስፈጸም አቅምና የአመለካከት ግንባታ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ በየደረጃው ያለው የከተማ አስተዳደር የሚሰጠውን የከተሞች ምግብ ዋስትና ኘሮግራም ማረጋገጥ ተልዕኮ አፈጻጸም በሚመለከት ዝርዝር ፕሮጀክት እንዲያዘጋጅና ይህንን ዝርዝር ዕቅድ ለምልዓተ ህዝቡና ለተጠቃሚው እንዲያሳውቅ የሚያደርግ አሰራር በአጣዳፊነት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ ይህ አሰራር ከመንግስታዊና ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ቅልጥፍና አኳያና የልማታዊ መልካም አስተዳደር ግንባታ ከማጣናከር እንዲሁም የህብረተሰቡን አመለካከት በመለወጥ የልማታዊ መልካም ዴሞክራሲያዊ መንግስታችን መሰረታዊ መርህ የሆነውን የዜጎች ፍትሃዊ የሀብት ተጠቃሚነት ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል፡፡

ከፌዴራል እስከ ከተማ የመንግስትና የሕዝብ ክንፉ ተናበውና ተቀናጅተው መሄድ አለባቸው፡፡ ለተለያዩ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችና ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የስነ ልቦናና ክህሎት ትምህርት በመስጠት እራሳቸውን እንዲያደራጁ ማነሳሳት ያስፈልጋል፡፡ በቀጣይም በጋራ በሚሰሩ ሥራዎች ዙሪያ መደበኛ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ማስፈጸም ተገቢ ይሆናል፡፡ ዕቅዱን

በማስፈጸም በኩል ፈርጀ ብዙ ሚና ያላቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ሌሎች ባለድርሻና ተባባሪ አካላት በዕቅዱ እና በአፈጻጸም ዙሪያ በጋራ ተናቦና ተቀናጅቶ የመስራት ተነሳሽነትና ዝግጁነት እንዲፈጠር አቅዶ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በየደረጃው ካሉ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤትም ጋር በቅንጅት መሠራት ያለባቸው ሥራዎች በቅድሚያ ለይቶ ተደማሪ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ አቅዶ መስራት ይጠይቃል፡፡ ከሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከሊጎች፣ ከመገናኛ ብዙኃን፣ ከመንግስት የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት፣ ከህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች፣ አርቲስቶች፣ ከልማት አጋሮች እና ሌሎች ባለድርሻና ተባባሪ አካላት ጋር ተናቦ የመስራት አቅጣጫ እንከተላለን፡፡

## 7.3 የሥራ ውጤትን የሁሉም ነገር ማጠንጠኛ የማድረግ አቅጣጫ መከተል

ይህ የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ በከፋ ድህነት ውስጥ ያሉ የከተማ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ የተጠቃሚዎች ምልመላ አስቀድሞ በሚታወቅ ግልጽ መስፈርት መፈጸም ይኖርበታል፡፡ በሂደቱም የሠፈር ነዋሪው የድሃ ድሃ የተመረጠ መሆኑን በተሳትፎው ማረጋገጥ አለበት፡፡ ምልመላውም በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ በስምና በአድራሻ ተለይቶ መታወቅና ግልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡፡ ተጠቃሚዎቹ መቼና ምን፣ ምን ሲሟላ ከኘሮግራሙ እንደሚመረቁ ግልጽ መስፈርት ተዘጋጅቶ ለኘሮግራሙ ስኬት መረባረብ ያስፈልጋል፡፡

ስትራቴጂውን ለማስፈጸም በየደረጃው የተቀመጡ እነዚህ ግቦች ሊመዘኑ የሚችሉ፣ የጊዜ ገደብ የተቀመጠላቸው፣ ፈጻሚ የተለየላቸው ተግባራት እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ከስራችን ጋር አግባብነት ካላቸው ባለሚናዎች ጋር የምንሰራቸውና በተናጠል የምንሰራቸውን ሥራዎች በወጉ በመለየት መግባባት ላይ እንዲደረስባቸው ይደረጋል፡፡ በተጠቃሚዎችና በሕዝቡም እንዲፈጸሙ የምንፈልጋቸውን ተግባራት በአግባቡና በወቅቱ ለይተን ለሕዝቡ ቀርበው ውይይት ከተካሄደባቸው በኂላ ስምምነት ላይ እንዲደረስባቸው መደረግ አለበት፡፡

በሴክተራችን የሚዘጋጀው ዕቅድ ወጥነት ያለውና የተናበበ እንዲሆን የላይኛው መዋቅር ለታችኛው መዋቅር የራሱን መሪ ዕቅድና በየደረጃው ደግሞ ሞዴል ዕቅድ አዘጋጅቶ እንዲሰጥና የታችኛው መዋቅር የራሱን ዕቅድ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም አዘጋጅቶ ለላይኛው መዋቅር ሲያቀርብለት ዕቅዱን በዝርዝር ገምግሞ የጽሑፍ ግብረ መልስ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ በአፈጻጸም ሪፖርትም ላይ በተመሳሳይ የውጤት አመላካች ነጥቦችን መሠረት ያደረገ ክትትል ይደረጋል፡፡ ከሪፖርቶች በተጨማሪም የመስክ ኢንስፔክሽን ተካሄዶ የተደራጀ የሱፐርቪዥን ሪፖርት ይቀርባል፡፡ የመስክ ቅኝትና የአፈጻጸም ሪፖርቱን መነሻ በማድረግ ዝርዝር ግምገማ ተካሄዶ የተሻሉ ተሞክሮዎች

ትምህርት ይወሰድባቸዋል፤ እንዲሁም ድክመቶች የሚስተካከሉበት አቅጣጫና መስማማት ይፈጠራል፡፡ በዚህ ሁሉ ሂደት ማጠንጠኛው የሥራ ውጤት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 7.4 በግልጽ ቅደም ተከተል የመምራት አቅጣጫ መከተል

የከተሞች ምግብ ዋስትና ግቦች ለማሳካት በስትራቴጅው የተቀመጡ የማስፈፀሚያ ስልቶች በቅደም ተከተል የሚፈፀሙ ይሆናል፡፡

1) የድሃ ድሃ የተጠቃሚ ልየታ በግልጽ መመዘኛና የህብረተሰብ ተሳትፎ በማረጋገጥ የመረጃ ቋት እንዲኖር ማድረግ ፣
2) የአመለካከት ለውጥ የማምጣት እና በራስ መተማመን የመፍጠር ሥራ መስራት
3) የክህሎት ስልጠና መስጠት፣
4) የልዩ ፓኬጅ ትግበራና በከፋ ድህነት ውስጥ ያሉ ዜጎች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣
5) ተጠቃሚዎች በወጣው መርሃግብር መሠረት ግልጽ መመዘኛ አስቀምጦ እንዲመረቁ ማድረግ፣

ስራዎችን በግልጽ ቅደም ተከተል መምራት ማለት በቅድሚያ ቁልፍ እና ዋና ዋና ተግባራትን ለይቶ በማውጣት በቁልፍ ሥራው ላይ መረባረብ ዋና ዋና ተግባራትን እንደምንሰጣቸው ክብደት አቀዳድሞ ማከናወን እና ለክንውናቸው የሚሆን ሀብት እንደ ቅደም ተከተላቸው መመደብ ማለት ነው፡፡ የከተሞች ምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ሥራችን በቅደም ተከተል የምንሰራቸውን የለውጥና የልማት ስራዎች ለይተን ያለንን ሀብት ምደባ በማድረግ መስራት ይጠበቅብናል፡፡ በቀጣይ ስራችን የሚያስፈልገን የሀብት መጠን ሥራው በሚጠይቀው ደረጃ በመዘርዘር ፍላጎታችን የማስቀመጥ ሥራ መስራት ይጠበቅብናል፡፡

ይህ ኘሮግራም በፍጥነት እንዳይከናወን እንቅፋት ይሆንብናል ብለን ከምንጠብቃቸው ማነቆዎች አንዱ የተስተካከለ የታታሪነት አመለካከት ላይ የሚታየውን ክፍተት ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ የክህሎት ችግር መሆኑን በመገንዘብ እነዚህ ማነቆዎች ለዘለቄታው ለመፍታት ወይም ትርጉም ባለው መልኩ ለመቅረፍ የሚያስችል ስልት በመንደፍ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ ከክህሎት አንፃር ወሳኙ የሰው ሀይል ምርታማነት በመሆኑ ያለንን አቅም በቅደም ተከተል በለየናቸው ስራዎች መሰረት መድበን በተግባር እንቅስቃሴ ውስጥ ገብቶ እየበቃ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለሥራ ወሳኝ የሆኑ መሳሪያዎችና ግብዓቶችን ለይቶ በመረባረብ ማሟላት እና ከስራችን ዕድገት ፍላጎት ጋር የሚያስፈልገውን በጀት በተመለከተ በቂ ዝግጅት በማድረግና አሳማኝ የሆኑትን ለይቶ በምክንያት በመደገፍ ለሚመለከታቸው አቅርቦ ማስወሰን ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ጊዜ፣ የሰው ኃይል እና ሀብት እንደቅደም ተከተሉ ለቁልፍና ዋና ዋና ሥራችን ቅድሚያ በመስጠት ማሟላት

ያስፈልጋል፡፡ የአመራር ጥበብ ግንባታ ስራችን አንዱ መርህ ስራን በቅደም ተከተል መምራት የሚሆነው ለዚህ ነው፡፡

## 7.5 የእርሰ በእርስ የመማማር ሥርዓት የመዘርጋትና የመተግባር አቅጣጫ መከተል

የከተሞች ምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ሥርዓትን በብቃት የሚመራና የሚፈጽም አመራርና ፈጻሚ ለመፍጠር በተግባር አፈጻጸም ወቅት የሚታዩ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶችን በመለየት ክፍተቶችንም ለመሙላት የእርስ በርስ የመማማር ሥርዓት ቀጣይነትና ውጤታማ በሆነ መንገድ ይፈጸማል፡፡

የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ የፖለቲካ አመራሮችና ግንባር ቀደም ፈጻሚዎችን የማበረታትና ዝቅተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡትን ደግሞ በመደገፍ እንዲሁም የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችንም ቀምሮ የማስፋት አቅጣጫ በመከተል የእርስ በርስ ውድድር በማጎልበት የተጣሉ የከተሞች ምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ግቦች በላቀ ደረጃ እንዲፈፀሙ ይደረጋል፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን እንዲሁም ሌሎች የልማታዊ መልካም አስተዳደር ችግሮችን ከምንጩ ለማድረቅ ባለድርሻ አካላትን በንቃት በማሣተፍ ተከታታይ የሆኑ ግምገማዎችንና የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን በማካሄድ ወቅታዊ ማስተካከያዎች ይደርጋሉ፡፡ በየጊዜው ለሚፈጠሩ አዳዲስና ውጤታማ አሠራሮችን ከከተሞች ምግብ ዋስትና ሥራዎች ጋር በማጣጣም ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

# 8. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

## 8.1 የገጠር ምግብ ዋስትና ተሞክሮችን ወደ ከተማ ማስፋፋት

የኘሮግራሙ ባህሪ እና በከተሞች ያለው የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር የበላይነት መኖር ኘሮግራሙን ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ ሊያደርገው እንደሚችል በማሰብ ይህንን መከላከል የሚያስችል ጠንካራ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት በሠራዊት ግንባታ አግባብ እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ ውጤታማ የሆነው የገጠር ምግብ ዋስትና ኘሮግራም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተሞክሮ ተቀምሮ እና ከከተማ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ እንዲተገበር ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

## 8.2 ለክትትልና ግምገማው ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን መጠቀም

ክትትልና ግምገማው እና የፋይናንስ አስተዳዳር ሥርዓቱን አስማማኝ ለማድረግ በከተሞች ያለውን ምቹ ሁኔታ መጠቀም ይጠበቅብናል፡፡ ተጠቃሚዎችን በትክክለኛ የግለሰብና የቤተሰብ ስም በህብረተሰቡ አማካይነት መለየት እና ይህንንም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካይነት መደራጀት ይኖርበታል፡፡ ተጠቃሚዎች ከእነሱ የሚጠበቀውን ሲፈጽሙ ገንዘቡን ማስተላለፍ፣ የፋይናንስ ሪፖርቶች በጊዜና በጥራት ለማዘጋጀት፣ …ወዘተ ሥራውን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በከተሞች ያለውን ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን የባንክ አገልግሎቶች በዘመናዊ መንገድ በመጠቀም የአገልግሎት አቅርቦቱ፣ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ማቀላጠፍ ይገባናል፡፡

በሌላ መልኩ የፕሮግራሙ አፈጻጸም ከልማት አጋሮች፣ ከክልልና ከተማ አስተዳደሮች፣ ከተጠቃሚዎች እንዲሁም ከህበረተሰቡ ጋር በመሆን በስምምነት በሚቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የጋራ ግምገማ ስርዓትና የተገኙትንም ውጤቶች በኮንፈረንሱ ይፋ የሚደረጉበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

## 8.3 የተጠናከረ የፋይናንስ ሥርዓት ከጅምሩ መገንባት

በከተሞች የተጠቃሚዎች ተጠጋግቶ መስፈር፣ ከገጠሩ ጋር ሲነፃጻር መጠኑ ያነሱ መሆን፣ ለቴክኖሎጂና ደጋፊ መሠረተ ልማቶች የተመቸ መሆኑ ዘመናዊ አሠራር ከጅምሩ መገንባት ያስችላል፡፡ የሰው ኃይልም በተሻለ ማግኘት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የከተሞች ምግብ ዋስትና ኘሮግራም የፋይናንስ አስተዳዳር ጠንካራና አስማማኝ በሆነ አሠራር የታገዘ ለማድረግ ከጅምሩ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡

# 9. ማጠቃለያ

ሃገራችን ባለፉት አስርት ዓመታት ባስመዘገበችው ፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎች ቁጥር ወደ 29 በመቶ እንዲወርድ አስችሏል፡፡ በዚህም ሂደት በሚቀጥሉት ከሁለት አስርት ዓመታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሃገራችን የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ እንደምትሰለፍ ይታመናል፡፡ ይህን ለማረጋገጥም መንግስት ሀገራዊ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ነደፎ ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ከፍ ብሎ ለተገለጸው ውጤት መገኘት ትልቁን አስተዋፅኦ ያደረገዉ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው፡፡ በገጠር ምርትን ለማሳደግ የተሰሩት አመርቂ ስራዎችና የምግብ ዋስትና ችግሮች ቅነሳ ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳን በከተሞች እየተከናወነ ያለው የስራ ዕድል ፈጠራ አበረታች ውጤት እያስመዘገበ ቢሆንም ከችግሩ ስፋትና ውስብስብነት አንፃር በከተሞች አካባቢ የሚታየውን የምግብ ዋስትና ችግር ሙሉ ለሙሉ መቅረፍ አልተቻለም፡፡

ለከተሞች የምግብ ዋስትና ክፍተት እንደ መንስኤነት የሚወሰዱት በሥራ ስምሪት ያለው የዝግጁነት መጓደል፣ በቂ የስራ ዕድል ያለመስፋፋት፣ ዝቀተኛና አሰተማማኝ ያልሆነ የገቢ መጠን፣ የመኖሪያ፣ የማምረቻና የመሸጫ ቤቶች እጥረት፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ የህዝብ ፍልሰት፣ የልማታዊ መልካም አስተዳደር ክፍተት፣ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓት ያለመጠናከር፣ የተቀናጀ ድጋፍ ያለመኖር፣ የከተማ-ከተማ እና የከተማ-ገጠር ትስስር የላላ መሆን፣ በቂ የመረጃና የገበያ ትስስር ያለመኖር፣ ለከተማ ግብርና ልማት በቂ ትኩረት ያለመስጠት፣ የአመጋገብ ባህላችን ያስከተለው ተጽዕኖ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች እንዲሁም የቤተሰብ መፍረስ…ወዘተ ናቸው፡፡

ችግሮቹና የመንስኤዎቹ ነጸብራቅ የሆኑት የተለያዩ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች እየተከሰቱ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም ለመጥቀስ ያህል፥ ጎዳና ተዳዳሪነት፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ ለምኖ አዳሪነት፣ ወጣት ጥፋተኛነት፣ የአዕምሮ ጤና ህመምተኝነት፣ የህጻናት መቀንጨር፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ ስደትና ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ሌሎችም ናቸው፡፡ እነዚህ ክስተቶች ከህዝብ እና ከከተሞች ዕድገት ጋር እየጨመሩ የሚሄዱ በመሆናቸው በከተሞች የሚታየውን የምግብ ዋስትና ችግር የበለጠ እንዲባባስ አድርገውታል፡፡

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በማቃለል የከተሞች ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንዲቻል የከተሞች ምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡ የከተሞች ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችና የማስፈፀም አቅጣጫዎች ተለይተው የተቀመጡ ሲሆን ለተግባራዊነታቸው የሁሉም ባለድርሻና ተባባሪ አካላት የተቀናጀ እንቅስቃሴ ይጠይቃል፡፡

በአጠቃላይ በሃገራችን በተለይም በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የመጀመሪያው ቁልፍ ተግባር ሊሆን የሚገባው በየደረጃው ያለው የህብረተሰብ ክፍል በስራ ላይ ያለውን አመለካከት በተለያዩ የህዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ስራዎች ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማነቃነቅ የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ለሁሉም ዜጋ ምቹ የስራ ሁኔታ በመፍጠር የከተሞችን የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ጉዳይ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ሃገራዊ አጀንዳ ነው፡፡

……………………….//…………………………

## አባሪዎች፡- የሴክተር መ/ቤቶች የተግባርና ሃላፊነት መግለጫ

### 1. የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

1) ስትራቴጂውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አስፈላጊ የህግ ማዕቀፎችን፣ የልማት ፓኬጅ እና ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ በማድረግ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣
2) በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የሥራ ታታሪነት ጉድለት መቀየር የሚያስችሉ የትምህርትና ስልጠና ስራዎችን በስፋት በመስራት የህዝብ ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፣
3) ስትራቴጂውን ለማስፈጸም የተጠሪ ተቋማትን እና የዘርፉን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ግብረ-መልስም ይሰጣል፡፡
4) የከተሞች የምግብ ዋስትና ችግሮችን ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናውናል፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ጉድለቶች በቀጣይ እንዲስተካከሉ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
5) የባለድርሻ እና ተባባሪ አካላት የሚያስተባብር ተቋም እንዲሰየም ተከታትሎ ያስፈጽማል፡፡ በየደረጃውም እንዲቋቋም አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣
6) የስትራቴጂውን አፈጻጸም በተመለከተ ለምግብ ዋስትና ብሄራዊ ፎረም ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣ በፎረሙ በሚሰጠው ግብዓት መሰረት በፕሮግራሙ መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ ለመንግስት የመነሻ ሃሳብ አቅርቦ ያስወስናል፡፡
7) ስትራቴጂውን ለማሳካት የሚያስችል ዘላቂነት ያለው ሀብት ለማሰባሰብ ከባለድርሻ እና ተባባሪ አካላት ጋር በመቀናጀት ሀብት ያሰባስባል፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
8) በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ ሀገር አቀፍ የከተሞች የልማታዊ ሴፍቲኔት የመረጃ ቋት ያደራጃል፣ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
9) ለክልል ከተሞች የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ይሰጣል፣
10) የመኖሪያ፣ የማምረቻ እና የመሸጫ ቦታዎች ግንባታ ሲከናወኑ አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ እንዲሆኑ ይከታተላል፣
11) ፕሮግራሙ ፈርጀ ብዙ ጉዳዮችን አካቶ እንዲዘጋጅ የቅርብ ክትትል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

## 2. የፌደራል የከተሞች የምግብ ዋስትና እና ሥራ ዕድል ፈጠራ ኤጀንሲ

1) ስትራቴጂ፣ የህግ እና የድጋፍ ማዕቀፎች፣ የስልጠና ማንዋሎች ያዘጋጃል፤ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች የስነ ልቦናና የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ተከታታይ የሆነ የአቅም ግንባታ ሥራ እንዲከናወን ያደርጋል።
2) በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ የስራ አመለካከት መቀየር የሚያስችሉ የትምህርትና ስልጠና ስራዎችን በስፋት እንዲሠሩ የሚያግዝ የህዝብ ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፣
3) የሥራ አጦች፣ ሥራ ፈቶች፣ መስራት የሚችሉና የማይችሉ ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ ዜጎችን መረጃ በጥናት በመለየት ያደራጃል፣ በተለያዩ የሥራ መስኮች መሰማራት ለሚችሉት ወገኖች በየደረጃው ያሉ የጥ/አ/ኢንተርፕራይዝ ልማት ተቋማትን በማስተባበር ወደ ሥራ እንዲሰማሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል። በከፋ ድህነት ውስጥ ላሉት የተለየ ፓኬጅ ቀርጾ ያሠማራል በጊዜ ገደብ እንዲመርቁም ያደርጋል።
4) የማምረቻና የመሸጫ፣ የብድርና ስልጠና፣ የገበያ ትስስርና ሌሎች ድጋፎችን ተከታታይና ዘላቂ በሆነ መልኩ በማመቻቸት ውጤታማ ሆነዉ በምግብ እራሳቸዉን ከማስቻል አልፎ ለኢንዱስትሪዉ ሽግግር የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ያደርጋል።
5) የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የማህበራዊ ኑሮ ችግርና ጠንቅ እንዲሁም ለህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና ፍልሰት ተጋላጮች የመከላከልና የተሃድሶ ሥራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል።
6) ለተለያዩ የተሃድሶና መከላከል ስራዎች ሀብት እንዲሰባሰብና ለሚመለከታቸው እንዲተላለፍ ያደርጋል።
7) ከሚዲያ ጋር በመቀናጀት፣ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የተለያዩ የህዝብ መድረኮች፣ ዶክዩሜንታሪ ፊልሞች፣ የህትመት ውጤቶችን በማዘጋጀት በአመጋገብ ባህል መሻሻል፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ በአረንጓዴነት ልማት፣ በከተማ ግብርና የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በታታሪነት የሥራ ባህል ...ወዘተ ላይ የተለያዩ የህዝብ አጀረጃጀቶችን በመጠቀም የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ የህዝብ ንቅናቄዎች እንዲፈጠሩ ይሰራል፣
8) የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር የተሻሉ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

9) ከፌደራል እስከ ከተሞች የተናበበ አደረጃጀትና አሰራር ሥርዓቶችን በማዘጋጀት እና አጋርነት በመፍጠር የስትራቴጂው ማስፈጸሚያ ስልቶች እንዲፈፀሙ ያደርጋል፡፡ የልማታው ሴፍትኔት ኘሮግራም በትክክለኛና እውነተኛ መረጃ የተመሠረተ የአፈጻጸም ክትትል ይኖረው ዘንድ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሥርዓት ተዘርግቶ እንዲተገበር ያደርጋል፡፡

10) በማንኛውም የከተሞች የልማትና ሌሎች ማወዳደሪያ መስፈርቶች ላይ የከተሞችን የልማታዊ ሴፍቲኔት ጉዳይ እንደ አንድ መስፈርት መካተቱን ይከታተላል፣

11) ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር ህብረተሰቡን ያሳተፉ የዘርፍ ዕቅዶች በማዘጋጀት ለተፈፃሚነቱ የስምምነት ሰነድ ይፈራረማል፣ አፈፃፀሞችን ይከታተላል፣ አፈፃፀሞችን በባለሚናዎች ምክር ቤት እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

## 3. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

1) በከፋ ድህነትና በአስቸጋሪ ሁኔታ ዉስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ የአእምሮ ጤና ህመምተኞች፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎች፣ ወጣት ጥፋተኞች…ወዘተ መረጃ ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣

2) የማህበራዊ ኑሮ ችግርና ጠንቅ ሰለባ ለሆኑ ግለሰቦችና ቤተሰቦች በስም በመለየት ወደ ስራ ሊያስገባ የሚችል የስነ-ልቦና እና የክህሎት ስልጠና እንዲሰጣቸዉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

3) እነዚህ ወገኖች እንደየ ባህሪያቸዉ አደራጅቶ ወደ ስራ ለመሰማራት የሚያስችላቸው የዝግጅቱነት ስልጠና እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡ ዝግጁ መሆናቸው ሲረጋገጥ በስም እና በቤተሰብ የተለየ ትክክለኛ ዝርዝራቸውን ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፡፡

4) በከፋ ድህነት ውስጥ የሚገኙ፣ ወደ ስራ ሊሰማሩ የማይችሉና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት ሊያገኙ የሚገባቸውን የድሃ ድሃ ግለሰቦችና ቤተሰቦች በመለየት የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ይህ ካልተቻለ የተቋም አገልግሎት እንደ መጨረሻ አማራጭ ይሰጣል፡፡

5) ህገ-ወጥ ፍልሰትን ለመከላከል የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲከናወኑ ያደርጋል፣

6) ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመሆን ከቤተሰቦቻቸዉ እና ከአካባቢያቸው ተለይተው ለማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ሰለባ የሆኑ ዜጎችን ከቤተሰብና ከህብረተሰብ በማቀላቀል አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ሁኔታዎች ያመቻቻል፡፡

7) በሀገሪቱ ያለዉን የስራ ገበያ ጥናት በማካሄድ እና ከባለሀብቶች ጋር በመቀናጀት ለስራ አጥ ወገኖች የስራ ስምሪት አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

8) ለተሀድሶና መከላከል ንዑስ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት ይመድባል፣ አፈፃጸሙን ይከታተላል፡፡

9) አካል ጉዳተኞች አምራች እንዲሆኑ የሚያግዙ የሰው ሰራሽ አካል እና የአካል ድጋፍ በጥናትና ምርምር ላይ ተመርኩዞ በሀገር ውስጥ እንዲመረቱና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

10) ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡

## 4. የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር

1) በከተሞች ያለውን የሴቶችና ህፃናትን ዝርዝር መረጃ ይሰበስባል፣ ያደራጃል እንዲሁም ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ያደርጋል፣

2) አሳዳጊ የሌላቸዉ ህፃናት በሀገር ውስጥና በውጭ የጉዲፈቻ አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

3) ለተለያዩ ማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ሰለባና ተጋላጭ ለሆኑ አሳዳጊ ለሌላቸዉ ህፃናትና ሴተኛ አዳሪዎች፣ ጎዳና ተዳዳሪዎች መረጃ በማደራጀት አስፈላጊዉን ድጋፍ እንዲያገኙ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፡

4) በየደረጃዉ ካሉ ሴቶች አደረጃጀቶች ጋር በጋራ በመሆን በስራ ስምሪት ዝግጁነትና ታታሪነት ላይ ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ መስጫ እና የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡ መድረኮች እንዲካሄዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

5) ከባለድርሻና ተባባሪ አካላት ጋር በመሆን ሴቶች የስነ-ልቦናና የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ይደግፋል አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣

6) የድሃ ድሃ የሆኑ ቤተሰቦች በስም በመለየት የተቋም አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው ህጻናትና ሴቶች አገልግሎቱን ያመቻቻል፣ በተጨማሪም ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት እንዲስፋፉ በትጋት ይሰራል፡፡

## 5. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

1) የተሀድሶ ፕሮግራሙ ሲተገበር በአስቸጋሪ የጤና ችግር ዉስጥ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን የህክምና አገልግሎት ይሰጣል፣

2) የተሀድሶ ፕሮግራሙ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት ለሚከሰቱ የጤና መታወኮች ባለሙያና መድሀኒት በመመደብ አስፈላጊዉን የህክምና አገልግሎት ይሰጣል፣
3) የጎዳና ተዳዳሪዎችን በማቋቋም ሂደት የፀጉር፣ የልብስ እና በሌሎች የንፅህና ችግሮች ምክንያት ወረርሽኝ በማያስከትል መልኩ እንዲወገዱ ያደርጋል፣
4) የአዕምሮ ጤና ህመም ችግር ያለባቸውን ግለሰቦች መረጃ ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣
5) የአዕምሮ ጤና ህመምን አስመልክቶ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለውን አመለካከት ለመለወጥ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፣
6) የአዕምሮ ጤና ህመም ያለባቸው ግለሰቦች ተገቢውን የህክምናና ሌሎች የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ሁኔታዎች ያመቻቻል፡፡

## 6. የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር

1) በጥናት ላይ በተመሰረተ መረጃ የከተማ ግብርና እምቅ ሀብት የከተማ ነዋሪዉን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ አጋዥ እንዲሆን ለማድረግ ይንቀሳቀሳል፣
2) የከተማ እና ገጠር ትስስርን ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ ለማድረግ የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ስራዎች ላይ ከሚመለከተዉ የከተማ መዋቅር ጋር በቅንጅት ይሠራል፣

## 7. የፍትህ ሚኒስቴር

1) የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎችና ወጣት ጥፋተኞችን መረጃ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀትና በማደራጀት ወደ ስራ እንዲሰማሩ አስፈላጊውን ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል፣
2) የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸው ወደ ስራ መሰማራት ባለመፈለግ ጎዳና ላይ መኖርንና በልመና መሰማራት ለሚመረጡ ዜጎች ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የሚከለክል የህግ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
3) በንዑስ ዘርፉ የሚዘጋጁ የህግ ማዕቀፎች በስራ ላይ እንዲዉሉ ትምህርት ይሰጣል፣ ህግ እንዳይጣስ ይከላከላል፣ የህግ ጥሰት ሲገጥም አስፈላጊዉን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣
4) በተሃድሶና መከላከል አፈጻጸም ሂደት ላይ አስፈላጊውን ጥበቃና የህግ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 8. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

1) ከልማቱ ጋር በተገናኘ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚደረጉ የእርዳታ ስምምነቶች ይፈራረማል፣ አፈፃፀማቸዉን ይከታተላል፣

2) ለስትራቴጂው ዓላማ ማሳኪያ ከዉጭ ሀገር የሚገቡ ግብዓቶች ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ብቻ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣
3) ለስትራቴጂው ማስፈፀሚያ መደበኛ በጀት ይመድባል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣
4) በየደረጃው ላሉ የፋይናንስ ተቋማት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ይሰጣል፣
5) መንግስታዊ ድርጅቶች ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የሚሆን ድጋፍ ለማድረግ ፍቃደኛ ሲሆኑ አዎንታዊ ምላሽ ይሰጣል፡፡

## 9. የትምህርት ሚኒስቴር

1) ትውልዱ ስራ ወዳድና መልካም ዜጋ እንዲሆን ከታችኛዉ የትምህርት እርከን ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ ትኩረት ተሰጥቶት በካሪኩለም እንዲካተት ያደርጋል፣
2) ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመረቁ ተማሪዎች ስለስራ ፈጠራ ክህሎትና ታታሪነት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፣
3) የስልጠናና የቴክኖሎጂ ልማት ማዕቀፎች ያዘጋጃል፣ የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መምህራንን አቅም ይገነባል፣ የኢንተርፐሪነር ስልጠናዎች እንዲሰጡ ያደርጋል፣ የተረጋገጠ ቴክኖሎጂ የዲዛይንና ናሙና ምርት ስራዎችን በመለየት ያሰራጫል፣
4) በኢንተርፕራይዞች የእድገት ደረጃን መሰረት በማድረግ ተፈላጊነት፣ ጥልቀትና ስፋት ያለው ምርምር እንዲካሄድ ያደርጋል፣
5) የዩኒቨርስቲዎችና የቴክኖሎጆ ኢንስቲትዩቶች የመደበኛ ሰልጣኞች የመመረቂያ የጥናት ፕሮጀክት አንዱ ትኩረት የስራ ዕድል ፈጠራ ላይ እና ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ያደረጋል፣
6) ተስማሚ የሆኑ የማምረቻ መሳሪያዎች በአካባቢና በቀላል ጥሬ ዕቃ እንዲመረቱ የሚያስችል ጥናትና ምርምር በማድረግ ውጤቱን ለተለያዩ ተቋማት ያሰራጫል፣
7) የፊርጀ ብዙ ጉዳዮች ትምህርት በየደረጃው ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ ህብረተሰቡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ያለውን ግንዛቤ እንዲያጎለብት ያደርጋል፡፡

## 10. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

1) በሃገሪቱ ያሉ ኢንዱስትሪዎች የሠው ሀይል ፍላጎቶቻቸውን ዝርዝር መረጃ ለከተሞች በልማታዊ ሴፍቲኔት መረጃ መረብ በየወቅቱ እንዲያሳውቁ ያደርጋል፣ እና
2) እንዳስፈላጊነቱ የግንዛቤ ማስጨበጥ ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም የቴክኒክ ድጋፎችን ያደርጋል፣

## 11. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

1) የማህበራዊ ኑሮ  ጠንቅ ሰለባ ሆነው ልዩ ተሠጥዖ ላላቸው ዜጎች በተሰጥዖዋቸው እንዲሳተፉ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣
2) ለስትራቴጂው ማስፈጸሚያ የሚሆን ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚረዳ የቲያትርና፣ የፊልም፣ የሙዚቃ ፕሮግራሞችና ፌስቲቫሎች ያስተባብራል፣
3) በስትራቴጂው የተሃድሶ ትግበራ ወቅት ልዩ ልዩ የመዝናኛ ፕሮግራሞች እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡

## 12. የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር

1) የሃይማኖት ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት በከተሞች የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ዙሪያ የራሳቸውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ያወያያል፣ ያስተባብራል፣
2) በከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚመጣውን የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ስለሚቀነሱበትና በሂደትም ስለሚወገዱበት ሁኔታ ከሀይማኖት ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ማህበራት  እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካት ጋር በመሆን ህብረተሰቡን የማስተማር ስራ ይሰራል፣
3) ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር በሚደረገው ትብብርና አጋርነት ምስረታ እና ትግበራ ላይ ይሳተፋል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

## 13. የአካባቢ እና ደን ሚኒስቴር

1) በአረንጓዴ ልማት፣ በደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የህብረተሰቡን አስተሳሰብና ዝንባሌ በማስተካከልና ባለቤትነትን ለመፍጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ድጋፍ ያደርጋል፣
2) የሚፈጠሩ የስራ መስኮች ለአረንጓዴ ልማት አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ እና በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ እንዳይፈጥሩ  አስፈላጊ ድጋፍ ይሰጣል፣
3) የአካባቢ ተጽኖ ግምገማ እንዲካሄድና እንዲጠና በማድረግ የተቀናጀ የከተማ ግብርናና የአረንጓዴ ልማት እንዲስፋፋ፣ ምቹ የአየር ንብረት እንዲፈጠር፣ወዘተ ስራዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ያከናውናል፡፡

## 14. የንግድ ሚኒስቴር

1) ወደ ንግድ ዘርፍ ለሚገቡ አንቃሳቃሾች፣ ኢንተርፕራይዞችና የሸማቾች ማህበራት የንግድ ፈቃድ ይሰጣል፣
2) በአምራቾችና ሸማቾች መካከል ጤናማና ቀጥተኛ የግብይት ሰንሰለት እንዲኖር የንግድ ህጎችና አሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ያስከብራል፣

3) ለሸማቾች ወደ ገበያ የሚገቡና ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችና ምግቦች ላይ የጥራት ደረጃ መቆጣጠሪያ ህግና ደንቦች እንዲጠበቁ ይሰራል፣

4) በህገ ወጥ የንግድ ሥራ ላይ የሚሰማሩትን በመከታተል ወደ ህጋዊ የንግድ ስርዓቱ እንዲገቡ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፣

## 15. የፋይናንስ ተቋማት

1) በከፋ ድህነት ውስጥ ያሉና የድሃ ድሃ ለሆነ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ለተቀረጸው ፓኬጅ አፈጻጸም በአይቲ የተደገፈ ሥርዓት ገንብቶ ያስፈፀማል፡፡

2) ለተጠቃሚዎች የቁጠባ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ሁሉ ይሰጣሉ፣ ቁጠባም ይሰበስባሉ፣

3) መነሻ ካፒታል ለሚፈልጉ ዘርፎችና የስራ መስኮችን አቅምን ባገናዘበ መልኩ ብድር ያመቻቻሉ፣

4) የተበዳሪዎችን የመመለሻ ጊዜ፣ የብድር ጣርያና የእፎይታ ጊዜ አጥንቶ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋሉ፣

5) ተበዳሪዎች የወሰዱትን ብድር በአግባቡ ስራ ላይ ማዋላቸውን፣ ብድሩን በወቅቱ መመለሳቸውን በየደረጃዉ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፡፡

## 16. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር

1) የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ሰለባ ለሆኑ በአትሌቲክስና በሌሎች ስፖርቶች ለመሳተፍ ፍቃደኝነትና ዝግጁነት ላላቸው ዜጎች አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

2) በተሃድሶ ወቅት ሊያገለግሉ የሚችሉ የስፖርት ትጥቆችን ይሰጣል፣

## 17. ሚዲያ

1) በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ለመቀየር ተከታታይነት ያላቸዉን ፕሮግራሞች፣ ቶክሸዉ፣ የቀጥታ ስርጭት ፕሮግራሞች ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን ይሰራል፣

2) ስትራቴጂውን ለማሳካት በሚደረግ ጥረት ሁለገብ ተሳትፎ ለማድረግ መልካም ተሞክሮዎችን ለህብረተሰቡ ያስታውቃል፣

3) የልማታዊ ኮሚዩኒኬሽን የተለያዩ ተነሳሽነቶችና ስራዎችን በበላይነት ይመራል፡፡